ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ሐሙስ

83ኛ ዓመት ቁጥር 017 መስከረም 17 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




ፎቶ ፡- እዮብ ተፈራ

# ሁሉም ዜጋ ለሀገር ሰላምና አንድነት ሊሠራ እንደሚገባ ተገለጸ

## - 1498ኛው የነብዩ መሐመድ ልደት በዓል በድምቀት ተከበረ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ሁሉም ዜጋ ለሀገር ሰላም፣ አንድነትና ብልጽግና ሊሠራ ይገባል ሲሉ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ሼህ አብዱልከሪም በድረዲን ገለጹ።1498ኛው የነብዩ መሐመድ ልደት (መውሊድ) በዓል በአዲስ አበባ በታላቁ አንዋር መስጅድ ተከብሯል።

በአዲስ አበባ ታላቁ አንዋር መስጂድ ትናንት በተከበረው የ1498ኛ የነብዩ መሐመድ ልደት (መውሊድ) በዓል ላይ መልዕክት ያስተላለፉት ምክትል ፕሬዚዳንቱ፤ ሰላም ከሌለ ሀገር አትኖርምና ለሀገራችን ሰላም ልንሠራ ይገባል ብለዋል።

ምክትል ፕሬዚዳንቱ መተዛዘንንና መቻቻልን ያስተማሩንን ነብይ ልደት ስናከብር የእሳቸውን ፈለግ ተከትለን መሆን አለበት ሲሉ መልዕክት አስተላልፈዋል።

ሁሉም ዜጋ ለሀገር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





# “ደመራ ለሀገራችን እድገትና ብልጽግና በአንድነት የመቆም ምሳሌያችን ነው”

-ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር)

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ደመራ ለሀገራችን እድገትና ብልጽግና በአንድነት የመቆም ምሳሌያችን ነው ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ገለጹ፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር) ትናንት የደመራ በዓልን አስመልክቶ ለመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፤ደመራ እውነተኛው መስቀል የተገኘበት ጠቋሚ ኮምፓስ፣ ለሀገራችን እድገትና ብልጽግና በአንድነት የመቆም

“ደመራ ለሀገራችን እድገትና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

“መስቀል ደቅር ባይነት የሚሰበክበት በዓል ስለሆነ ትርጉሙን ባገናዘበ መልኩ ሊከበር ይገባል“

ገጽ 2

“በጎንደር ከተማ ያለውን የፀጥታ ሁኔታ አስመልክቶ በማኅበራዊ ሚዲያ የሚናፈሰው መረጃ ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ነው”

ገጽ 3















ግብርና ሚኒስቴር
MINISTRY OF AGRICULTURE

# በ2015/16 የምርት ዘመን 513 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ይጠበቃል

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በ2015/16 ምርት ዘመን በመኸር እርሻ 17 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሔክታር መሬት በማልማት 513 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ለማምረት ከክልሎች ጋር በቅንጀት እየተሠራ መሆኑን ግብርና ሚኒስቴር አስታወቀ።

ወቅታዊ የመኸር እርሻ ሥራ ሁኔታን በተመለከተ በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ኢሳያስ ለማ እንደገለጹት፤ የ2015/16 የምርት ዘመን አበረታች ውጤት ይገኝበታል ተብሎ ይጠበቃል።

በአማራ፣ ኦሮሚያ፣ ደቡብ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ አፋር፣ ሶማሌ፣ ሲዳማ፣ ትግራይ እና ሐረሪ ክልሎች እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር 17 ሚሊዮን 390 ሺህ 818 ሔክታር መሬት ለማረስ መታቀዱን አስታውሰው፤ እስከ አሁን በባህላዊ 14 ሚሊዮን 137 ሺህ 156 ሔክታር እና በትራክተር ሦስት ሚሊዮን 960 ሺህ 990 ሔክታር፤ በድምሩ 18 ሚሊዮን 98 ሺህ 146 ሔክታር መሬት መታረሱን አስታውቀዋል።

ከታረሰው እርሻ መሬት 16 ሚሊዮን 578 ሺህ 415 ሔክታር (95%) በዘር መሸፈኑን አቶ ኢሳያስ አመላክተዋል።

በዘር ከተሸፈነው 16 ሚሊዮን 578 ሺህ 415 ሔክታር መሬት ውስጥ 8 ሚሊዮን 280 ሺህ 741 ሔክታር በኩታ ገጠም እርሻ የተሸፈነ ነው ብለዋል።

ስንዴ፣ ጤፍ፣ ማሽላ፣ በቆሎና የተለያዩ ሰብሎች በመኸር እርሻው እየለሙ የሚገኙ ምርቶች መሆናቸውን አመላክተዋል።

በቀጣይም በሰብል ላይ ሊከሰቱ የሚችሉ በሽታዎችን ለመከላከል አርሶ አደሩ በቀበሌው ካሉ የልማት ጣቢያ ሠራተኞች ጋር በቅርበት በመሥራት የመከላከል እና የመቆጣጠር ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ አመላክተዋል።

የበልግ እርሻ እንቅስቃሴን ሥራን በተመለከተ እስከ መስከረም ሰባት ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከሁለት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ላይ የሚገኝ 43 ሚሊዮን 459 ሺህ 709 ኩንታል ምርት መገኘቱ ታውቋል።

በግብርና ሚኒስቴር መረጃ መሠረት፤ በ2014/2015 ዓ.ም የምርት ዘመን በአነስተኛ አርሶ አደሮች የአዝርዕት ሰብል 13 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት ለማልማት ታቅዶ 14 ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በዘር ተሸፍኗል። ከዚህም 393.3 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ማግኘት ተችሏል።

# “መስቀል ይቅር ባይነት የሚሰበክበት በዓል ስለሆነ ትርጉሙን ባገናዘበ መልኩ ሊከበር ይገባል”

**ሔርሞን ፍቃዱ**



ሊቀ ትጉኃን ደረጀ ነጋሽ



ዲያቆን አቤል ካሳሁን

አዲስ አበባ፡- መስቀል ስምምነትና ይቅር ባይነት የሚሰበክበት በዓል ስለሆነ ትርጉሙን ባገናዘበ መልኩ ማክበር እንደሚገባ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የሥነ መለኮት መምህራን ተናገሩ፡፡

ሊቀ ትጉኃን ደረጀ ነጋሽ ዘወይንዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ የመስቀል ትርጉም ትልቅ ነው፡፡ ስምምነትና ይቅር ባይነትን የሚሰበክ ነው፡፡ ከዚህ መነሻነት መስቀል በዓሉን ስናከብር ትርጉሙን ባገናዘበ መልኩ ሊሆን ይገባል፡፡

ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትታወቀው በይቅርታ ነው ያሉት ሊቀ ትጉኃን፤ እርስ በርስ ግጭትን አቁመን ወደ ፈጣሪ በመመለስ በይቅርታ ችግሮችን የምንፈታበት፤ ተበዳይ የሚካስበት ሁኔታ መፍጠር አለብን ብለዋል፡፡

ሰው ከፈጣሪ ጋር ከመታረቁ በፊት ከራሱና ከሰው ጋር መታረቅ እንዳለበት ገልጸው፤ ሰው ይህን ሲያደርግ ለሀገሬ ምን አድርጌያለሁ? ለሕዝቤና ለሃይማኖቴ ምን ሠርቻለሁ? ብሎ ራሱን ሊጠይቅና ይቅር ባይ መሆን እንዳለበት ገልጸዋል፡፡

በጎ ስንሆን ከበጎ ምግባር ጋር እንተባበራለን፤ ሰው ማለት አካላዊ ቅርፅ ያለው ብቻ ሳይሆን ሰብዓዊ አስተሳሰብ ሊኖረን ይገባል ብለዋል፡፡

ጠቢቡ ሰለሞንም «ልጄ ሆይ ሰው ሁን» ነበር ያለው፤ ዲዮጋ የተባለ ፈላስፋም በጠራራ ፀሐይ ገበያ መሐል ሲዞር ምን ትፈልጋለህ ሲሉት «ሰው» ነበር ያለው፤ እነሱም መልሰው ይህ ሁሉ ሰው አይደለም ወይ ሲሉት እኔ ምፈልገው ሰው ነው ሲል ደግሞ ተናግሯል፡፡ ለሀገራችን ሰው እንሁንላት መካን አናድርጋት ሲሉ ሊቀ ትጉኃን መክረዋል፡፡

ኢትዮጵያዊ መልኩን ነብር ዥንጉርጉርነቱን ሊለውጥ ይችላልን የተባለው ቀለሙን ሳይሆን ባህሉን፣ ማንነቱን፣ እሴቱንና ወጉን መሆኑን ተናግረው፤ ኢትዮጵያን ወደ ክብሯ ለመመለስ ሁላችንም ወደ ራሳችን እንመለስ፤ ለውጥ የሚጀምረው ከራስ ነው ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡

ዲያቆን አቤል ካሳሁን በበኩላቸው፤ የመስቀል በዓል ስናከብር በዋናነት የበዓሉን ዓላማ ተረድተን ከልማድ በመውጣት ትክክለኛውን ትርጉም መርምረን በማወቅ ሊሆን ይገባል ብለዋል፡፡

እንደ ዲያቆኑ ገለፃ፤ መስቀል ለክርስቲያኖች የዕርቅ ምልክት ነው፡፡ ከፀብ የራቅን ልንሆን ይገባል፡፡

# በመስቀል በዓል የጉራጌ ማንነትና መገለጫዎችን ከማስተዋወቅ ባለፈ በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ ይሠራል

**ማህሌት ብዙነህ**



ወይዘሮ መሠረት አመርጋ

አዲስ አበባ፡- በጉራጌ ዞን በደመቀ መልኩ የሚከበረውን የመስቀል በዓል የጉራጌ ማንነትና መገለጫዎችን ከማስተዋወቅ ባለፈ በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ እንደሚሠራ የዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ቢሮ አስታወቀ።

የጉራጌ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ ኃላፊ ወይዘሮ መሠረት አመርጋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የመስቀል በዓል በድምቀት ከሚከበርባቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች መካከል አንዱ የጉራጌ ዞን ነው። ይህም በዓል በዞኑ ከሃይማኖታዊ ገፅታው ባለፈ ባህላዊ ሥርዓቱን በጠበቀ መልኩ ለማክበር ቅድመ ዝግጅት ተጠናቋል።

የመስቀል በዓል እንደ ዞን በየዓመቱ በተመረጡ ቦታዎች የሚከበር መሆኑን አንስተው፤ ዘንድሮ በመንግሥት ደረጃ ከመስከረም 12 ጀምሮ ለ6ኛ ጊዜ በምሁር አክሊል ወረዳ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትና ቱሪስቶች በተገኙበት እሴቱን በጠበቀ መልኩ እንደሚከበርም አስታውቀዋል።

የዘንድሮ የመስቀል በዓል በደመቀ ሁኔታ ከማክበር ባለፈ እንደ ጉራጌ ዞን በጉራጌ የበዓሉ አከባበር በዓለም ቅርስነት እንዲመዘገቡ በትኩረት የሚሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

በበዓሉ አከባበር ላይም የጉራጌ ክትፎ አዘገጃጀትን ሙሉ ሂደቱን ማሳየት፣ የጉራጌ የመንደሮች አቀያየስ እና የባህላዊ ጎጆ ቤቶች አሠራርና መሰል የጥበብ ሥራዎች ለማሳየት በአውደ ርእይ ይካሄዳል ብለዋል። በተለይም ባህሉን የማያውቁና ሌላ አካባቢ ላይ ላሉ የማኅበረሰብ ክፍሎች፣ቱሪስቶች እና ለአስጎብኚ ማኅበራት የጉራጌን ባህልና የመስቀል አከባባር የማሳየትና የማስተዋወቅ ሥራን በትኩረት እንደሚሰሩ ወይዘሮ መሠረት አስታውቀዋል።

በጉራጌ ዞን የመስቀል በዓል ከመስከረም 12 ጀምሮ እስከ ጥቅምት 5 ድረስ በኅብረተሰቡ ዘንድ በስፋት የሚከበር መሆኑን ገልጸው፤ በእነዚህ ቀናትም የጎመን ክትፎ ፣የሴቶች መስቀል፣ ደመራ፣ የእርድ ሥነ ሥርዓት፣ አዳብና፣ መሰል የአከባበር ሥነ ሥርዓቶች እንደሚካሄዱ ጠቅሰዋል።

በዓሉን ለመታደም የብሔረሰቡ ተወላጆችም ሆነ ወደ አካባቢው የሚመጡ ጎብኚዎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ጠቁመው፤ቢሮው የጉራጌ ዞን ያለውን ሰፊ የመልክዓ ምድር እና ባህላዊ እሴቶች ለቱሪዝም መስህብነት በመጠቀም ከቱሪዝሙ ዘርፍ የሚገባውን ጥቅም ለማግኘት እየሠራ ነው ብለዋል። በዚህም የአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ ለማድረግ እንደሚሠራም ተናግረዋል።

በጉራጌ ብሔረሰብ ዘንድ የሚገኙትን ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ እሴቶች ይዘታቸው እንደተጠበቀ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍ በትኩረት እየተሠራ እንደሆነ ወይዘሮ መሠረት አስታውቀዋል።

# “በጎንደር ከተማ ያለውን የፀጥታ ሁኔታ አስመልክቶ በማኅበራዊ ሚዲያ የሚናፈሰው መረጃ ፈጽሞ ከእውነት የራቀ ነው”

- ብርጋዴር ጄኔራል ማርዬ በየነ



**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በጎንደር ከተማ ያለውን የፀጥታ ሁኔታ አስመልክቶ በማኅበራዊ ሚዲያ የሚናፈሰው መረጃ ፈጽሞ ከእውነት የራቀ መሆኑን የጎንደር ከተማ ኮማንድ ፖስት ሰብሳቢ ብርጋዴር ጄኔራል ማርዬ በየነ ገለጹ፡፡

ኮማንድ ፖስቱ ጽንፈኛ ቡድኑ ላይ እየወሰደ ካለው እርምጃ ባሻገር የከተማዋን ነዋሪዎች በማወያየት ባከናወነው ሥራ የከተማዋ የሰላም ሁኔታ መሻሻሉንም ነው የተናገሩት፡፡

ጽንፈኛ ቡድኑ የኢትዮጵያን ህልውና እና ሰላም ከማይፈልጉ አካላት የሚላክለትን ፍርፋሪ በመጠቀም ሰላማዊ ዜጎች ላይ ጥቃት የሚፈጽም የሕዝብ ጠላት መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ኮማንድ ፖስቱ ከሕዝብ ጋር ባደረገው ውይይትም፤ ኅብረተሰቡ የጽንፈኛ ቡድኑን እኩይ ድርጊት በግልጽ ማንሳቱን ጠቅሰዋል፡፡

ነገር ግን ከጽንፈኛ ቡድኑ ጎን የተሰለፉ አንዳንድ አካላት በማኅበራዊ ሚዲያ የሀሰት መረጃዎችን በማሰራጨት ሕዝብ ለማደናገር እየሠሩ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ለአብነትም ባለፉት ቀናት “ብርጋዴር ጄኔራል ማርዬ ተገድለዋል” በሚል በማኅበራዊ ሚዲያ የሀሰት መረጃ ሲያሰራጩ መቆየታቸውን አንስተዋል፡፡

በተጨማሪም “ክፍለ ጦር ደመሰስን፣ ታንክ ማረክን፣ አውሮፕላን ጣልን” የሚሉ የበሬ ወለደ መረጃዎችን ሲያሰራጩ መቆየታቸውን ጠቁመዋል፡፡

በመሆኑም ኅብረተሰቡ ሆነ ብለው የሀሰት መረጃ በሚያሰራጩ የጽንፈኛው ቡድን አባላት መደናገር የለበትም ነው ያሉት፡፡

ኮማንድ ፖስቱ በጽንፈኛ ቡድኑ ላይ ከሚወስደው እርምጃ ባሻገር ሕዝብን በማወያየት ዘላቂ ሰላም ለማስፈን እየሠራ መሆኑንም ብርጋዴር ጄኔራል ማርዬ ተናግረዋል፡፡

በዚህም የመከላከያ ሠራዊቱ የተሰጠውን ግዳጅ በብቃት እየተወጣ ነው ብለዋል፡፡

በቅርቡ በጎንደር ከተማ በአንድ ፖሊስ ጣቢያ ላይ ተኩስ በመክፈት ለማምለጥ በሞከሩ የጽንፈኛው ኃይል አባላት ላይ እርምጃ በመውሰድ የከተማዋን ሰላም ማስጠበቅ መቻሉንም ብርጋዴር ጄኔራል ማርዬ ገልጸዋል፡፡

ሠራዊቱ ከኅብረተሰቡ ጋር በመቀናጀት ውጤታማ ሥራ እያከናወነ ነው፤ ለዚህ ደግሞ ደጀኑ ሕዝባችን ምስክር ነው ብለዋል፡፡

# “የመስቀልና የኢሬቻ በዓላትን እሴት በጠበቀ መልኩ በአንድነት ማክበር ይገባል”

- ድምጻዊ ደመረ ለገሰ

**ሄለን ወንድምነው**



አዲስ አበባ፡- የመስቀልና የኢሬቻ በዓላትን እሴታቸውን በጠበቀ መልኩ በአንድነትና በመተሳሰብ ማክበር ይገባል ሲል ድምጻዊ ደመረ ለገሰ ተናገረ።

ድምጻዊ ደመረ ለገሰ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጸው፤ የኢትዮጵያን አንድነት፣ ባህልና ትውፊት አጠናክሮ ለማስቀጠልና ለሌሎች ሀገራት ለማስተዋወቅ የመስቀልና የኢሬቻ በዓላት የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። እነዚህ በዓላት እሴታቸውን በጠበቀ መልኩ በአንድነትና በመተሳሰብ ማክበር ይገባል፡፡፡

በኢትዮጵያ የሚከበሩ በዓላት የበርካታ ብሔረሰቦችን ባህል፣ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች፣ ትውፊት፣ አለባበስና ቋንቋ የያዙ በመሆናቸው በዓላቱን እሴታቸውን በጠበቀ መልኩ በማክበር ኢትዮጵያን ለተቀረው ዓለም በተገቢው መንገድ ማስተዋወቅ እንደሚገባ ተናግሯል፡፡

በመስከረም ወር የሚከበረውን የመስቀል በዓል ከሃይማኖታዊ ሥርዓቱ ሳይወጣ የኢሬቻን በዓል ደግሞ ከገዳ ሥርዓቱ ሳይርቅ ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ወንድማማችነት በተሞላበት ስሜት በአንድነት ሊያከብሩ እንደሚገባም መልዕክቱን አስተላልፏል።

እንደ ድምጻዊ ደመረ ገለጻ፤ የመስቀልና የኢሬቻ በዓላት የኢትዮጵያን ባህል ለሌሎች ሀገራት ለማስተዋወቅ፣ ትውፊታችንን ጠብቆ ለማኖር፣ የበዓላቱን እሴት አስጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍና አንድነታችንን ለማጠናከር ከፍተኛ ሚና አላቸው፡፡

የኪነ ጥበብ ባለሙያዎች፣ የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያዎች እና የሁሉም ኢትዮጵያውያን በዓለም ቅርስነት የተመዘገቡት የመስቀልና የኢሬቻን በዓላት ትውፊት አስጠብቆ ለቀጣይ ትውልድ ለማስተላለፍና ይበልጥ ለዓለም ሕዝብ ለማስተዋወቅ ጥረት ሊያደርጉ ይገባል ብሏል።

እየተዳከመ የመጣውን የአንድነትና የመተሳሰብ ልምዳችንን አስጠብቆ ማስቀጠል ይገባል ያለው ድምጻዊ ደመረ፤ የኢትዮጵያዊያንን የቀደመ ባህልና አኗኗር በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ በማካተት ትውልዱ ከልጅነት ጀምሮ አውቆት እንዲያድግ ማድረግ ይገባል ሲል ገልጿል።

በሌላ በኩል አንድነትን የሚሸረሽሩ ጉዳዮች በመራቅ ኅብረታችንን ማጠናከር ይገባል፤ በተለይ የኢትዮጵያን አንድነት፣ ባህልና ትውፊት አጉልተው የሚያሳዩ የኪነ ጥበብ ሥራዎችን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል ሲል አስገንዝቧል።

ድምጻዊ ደመረ እንደገለጸው፤ ኢትዮጵያ ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች የሚኖሩባት ሀገር እንደመሆኗ አንዱ የአንዱን ባህል፣ ሃይማኖት፣ ቋንቋ እና አኗኗር በማክበር ተሳስቦ መኖር ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ የበዓላት አከባበር፣ የቱሪስት ቦታዎች፣ የማኅበረሰቡን እሴቶች ለመጎብኘት ከተለያዩ ሀገራት የሚመጡ ቱሪስቶችን በአግባቡ መቀበልና ማስተዋወቅ ያስፈልጋል ያለው ድምጻዊው፤ ለሀገሪቱ ትልቅ የገቢ ምንጭ መፍጠርና በቱሪዝም እንቅስቃሴው የተሻለ ሥራ ማከናወን እንደሚገባ አመልክቷል።

የመስቀል ደመራ በዓል መስከረም 16 የሚከበር ሲሆን፤ የኢሬቻ በዓል ደግሞ መስከረም 26ና 27 ቀን 2016 ዓ.ም በአዲስ አበባና በቢሾፍቱ እንደሚከበር ታውቋል።

# በአዲስ አበባ የዓለም የቱሪዝም ቀን ከመጪው ጥቅምት ስምንት ቀን ጀምሮ ይከበራል

**ማህሌት ብዙነህ**



**ወይዘሮ ፍሬህይወት ገብረመድህን**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ደረጃ የዓለም የቱሪዝም ቀን ከመጪው ጥቅምት 8 እስከ 14 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በተለያዩ ዝግጅቶች እንደሚከበር የአዲስ አበባ ባህል፣ ኪነጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ አስታወቀ። ቀኑ መከበሩ መዲናዋ ከቱሪዝም የሚገባትን ጥቅም ዕድታገኝ ምቹ ሁኔታ እንደሚፈጥርም ተጠቁሟል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ባህል፣ ኪነ ጥበብ እና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም ልማት እና ፕሮሞሽን ዳይሬክተር ወይዘሮ ፍሬህይወት ገብረመድህን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ዘንድሮ በዓለም ለ44 ጊዜ በኢትዮጵያ ለ36ኛ ጊዜ የሚከበረው የዓለም የቱሪዝም ቀን በመስከረም ወር ባሉት ተደራራቢ በዓላት ምክንያት በአዲስ አበባ ደረጃ የንቅናቄ መርሀ ግብሩ ከጥቅምት 8 ጀምሮ እስከ ጥቅምት 14 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ይከበራል።

የዓለም ቱሪዝም ቀን በዓለም አቀፍ ደረጃ መስከረም 17 የሚከበር መሆኑን አውስተው፤ በመርሀ ግብሩ ኅብረተሰቡ ስለ ቱሪዝም ያለው ግንዛቤ የማጎልበት ዓላማ ያለው መሆኑን ገልጸዋል። በአዲስ አበባ ደረጃም ከጥቅምት 8 ጀምሮ እስከ ጥቅምት 14 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ በሚከበረው በዓል ከሁለት ሚሊዮን በላይ የኅብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉ መሆኑን ገልጸዋል።

የዘንድሮ የዓለም የቱሪዝም ቀን በኢትዮጵያ “ቱሪዝም ለአረንጓዴ ልማት፣አረንጓዴ ልማት ለቱሪዝም ” በሚል መሪ ቃል የሚከበር መሆኑን አስታውቀው፤ ይህም እንደ ሀገር እየተተገበረ ያለው የአረንጓዴ አሻራ ለቱሪዝም ዘርፉ ዕድገት ያለውን ተጨባጭ ለውጥ ለማሳየት ያለመ እንደሆነ ገልጸዋል።

የዓለም የቱሪዝም ቀን በመዲናዋ በርካታ የኅብረተሰብ ክፍሎችን በማሳተፍ የሚከበር መሆኑን ገልጸው፤የቱሪዝም ዘርፍን በተመለከተ ሰፊ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ ይሠራል፤ የማኅበረሰባዊ እና ኢኮኖሚያዊ ትስስርን ለማሳደግ የሚረዱ የተለያዩ የንቅናቄ መርሀ ግብሮችም ይካሄዳሉ ብለዋል።

የዓለም ቱሪዝም ቀን ሲከበር የሚከናወን ተግባራት ውስጥ የቱሪስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ምርትና አገልግሎታቸውን እንዲያስተዋውቁ፣ ከደንበኛው ጋር እንዲገናኙ እና የንግድ ትስስር እንዲፈጥሩ የማድረግ ሥራ ይሠራል፣ በቱሪዝም ሙያ ተምረው ሥራ የሌላቸውን ዜጎች ከተቋማት ጋር የማገናኘት እና የሥራ እድል የማመቻቸት ተግባር ይከናወናል ነው ያሉት።

እንዲሁም መሪ ቃሉን መሠረት ያደረገ ጥናታዊ ጽሑፍ ቀርቦ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል ያካተተ የውይይት መድረክ የሚከናወን መሆኑን አስታውቀዋል።

በከተማው የሚገኙ የቱሪዝም መስህቦችን አውቆ ለሌሎች የሚያሳይበትን ሁኔታ ለመፍጠርም ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ያሳተፈ የቱሪስት መስህብ ቦታዎች ጉብኝት መርሀ ግብር እንደሚኖር አመልክተው፤ በቀጣይ አዲስ አበባን ከማስተዋወቅ አኳያ የራሷን ሚና ትወጣለች በሚል ‹የሚስ ቱሪዝም አዲስ 2016› የቁንጅና ውድድር የሚካሄድ መሆኑን ወይዘሮ ፍሬህይወት ተናግረዋል።

የጎዳና ትርኢት፣ የበጎ አድራጎት ሥራዎች፣ ቱሪዝምን በተመለከተ የጥያቄና መልስ ውድድር፣ መዳረሻዎችን የማጽዳት የማስተዋወቅ ተግባራትም የሚተገበር መሆኑን አስታውቀው፤ በከተማዋ የቱሪዝሙን ዘርፍ ለማስፋፋትና ለማሳደግ ብሎም ከተማዋን ተመራጭ የቱሪዝም መዳረሻ ለማድረግ እንደሚሠራ ጠቁመዋል።

የዓለም ቱሪዝም ቀን መከበሩም ሴክተሩን የሚያነቃቃ እና ወደነበረበት ለመመለስም የሚረዳ መሆኑን ወይዘሮ ፍሬህይወት አንስተው፤ከተማዋን ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ገቢ እና ጥቅም ከፍ በማድረግ ረገድም ያስችላል ነው ያሉት።

ዜና

# ቢሮው በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት መስጠት ሊጀምር ነው

**መስከረም ሰይፋ**

አዲስ አበባ፡- የተዛዛውን አሠራር የተቀላጠፈ ለማድረግ የይዞታ ዘርፍ ሙሉ በሙሉ በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት መስጠት ሊጀምር መሆኑን የአዲስ አበባ መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ አስታወቀ፡፡

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር መሬት ልማትና አስተዳደር ቢሮ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ካሊድ ነስረዲን ከኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት፤ቢሮው በይዞታ ዘርፍ የአገልግሎት አሰጣጡን እስከ መጪው ጥቅምት ወር 2016 ዓ.ም አጋማሽ ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ ተገልጋዮች ባሉበት ቦታ ሆነው ጉዳያቸውን በቴክኖሎጂ (በሲስተም) የሚከታተሉበትና የሚያስፈጽሙበት የአሰራር ሥርዓት ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ ለዚህም ሁሉም ክፍለ ከተሞችና ወረዳዎችን በማናበብ ሠራተኞችን የማሰልጠን ሥራ ተጀምሯል፡፡

በቴክኖሎጂ የተደገፈው የአሠራር ሥርዓት መሬትና ተያያዥ አገልግሎቶችን ፈልገው ለሚመጡ ተገልጋዮች የተቀላጠፈ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል ነው ያሉት አቶ ካሊድ፤ በአሁኑ ጊዜም የተገልጋዮች ምልልስ በሚበዛበት የይዞታ አገልግሎት ተግባራዊ መደረጉን ተናግረዋል፡፡

በይዞታ አገልግሎት ዘርፍ አገልግሎቱን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ለማድረግ በተሠሩ ሥራዎችም አራት ክፍለ ከተሞች ወደ ሥራ የገቡ ቢሆንም ቀሪ ክፍለ ከተሞችን በቴክኖሎጂ የማስደገፍ ሥራ እየተሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

ቢሮው አገልግሎት አሰጣጡን በቴክኖሎጂ የተደገፈ ከማድረግ ጎን ለጎንም መመሪያዎችን የማሻሻል ሥራ እየሠራ መሆኑን ጠቁመው፤ በ2016 በጀት ዓመት አገልግሎቶችን ለማሻሻል ተቋማዊ የሪፎርም ዶክመንት መዘጋጀቱንም ተናግረዋል፡፡

አቶ ካሊድ አሁን ያሉ 11 መመሪያዎች ከጊዜው ጋር የሚሄዱ በመሆናቸው መሻሻል የሚፈልጉ ናቸው፡፡ መመሪያዎቹን የማሻሻል ሥራ ተጀምሯል ያሉ ሲሆን፤ መመሪያዎቹ የሚሻሻሉት የሥነምግባር ብልሽትና ለተገልጋይ እንግልት መፍጠራቸው በከተማ አስተዳደሩ የተገመገሙ መሆናቸውን ጠቅሰዋል፡፡

መመሪያዎቹ አገልግሎቶችን በሚያሳልጡና ችግሮችን በሚያቃልሉ መልኩ እየተቀረጹ መሆኑን ገልጸው፣በረቂቅ መመሪያዎቹ ላይ ባለሙያዎች፣ የሕግ አካላትና ተገልጋዮች የተወያዩባቸው መሆኑን ነው የተናገሩት፡፡



ከሚሻሻሉት መመሪያዎች መካከልም በከተማ አስተዳደሩ ካቢኔ የሚወጡት መመሪያዎች በተያዘው በጀት ዓመት ተግባር ላይ የሚውሉ መሆኑን ጠቁመው፤ በፌዴራል ደረጃ የሚሻሻሉ አዋጆችንና መመሪያዎች ጊዜ ሊወስዱ ስለሚችሉ ኅብረተሰቡ ይህን ተገንዝቦ በትዕግስት እንዲጠብቅ ጠይቀዋል፡፡

አሁን አገልግሎት እየሰጡ ያሉ 11 መመሪያዎች በተበታተነ መልኩ ያሉ በመሆናቸው በቀላሉ ለማግኘት አዳጋች ነው ያሉት አቶ ካሊድ፤ የሚዘጋጁት መመሪያዎችም በቀላሉ ተደራሽ በሚሆን መልኩ አንድ ላይ ተሰባስበው እንደሚሻሻሉ ተናግረዋል፡፡

አቶ ካሊድ ተቋሙ ከማዕከል እስከ ወረዳ ድረስ መሻሻል አለበት የሚል ግምገማ በመኖሩ በበጀት ዓመቱ ተቋማዊ አደረጃጀትን በማስተካከልና በቴክኖሎጂ የተደገፈ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችሉ አሰራሮች ለመፍጠር ሥራዎች መጀመራቸውን ተናግረዋል፡፡

ከአደረጃጀት ጋር በተያያዘ ያለአግባብ አገልግሎቶች በአንድ ቦታ የመሰብሰብ ሁኔታ ሲታይ ማስተካከል እንደሚያስፈልግ አመልክተው፤ ባለሙያዎች ሊኖራቸው የሚገባ የሥነ ምግባር መተዳደሪያ ደንብ በማዘጋጀት አገልግሎት ፈልጎ የሚመጣ ማንኛውም ሰው በአግባቡ አገልግሎቱን አግኝቶ የሚመለስበት አሠራር ለመፍጠር በትኩረት ይሠራል ብለዋል፡፡

## "በመቀራረብ፣ በአንድነት፣ በእኩልነት፣ በሰላም እና በፍቅር ልንኖር ይገባል»

- ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በመስቀሉ ቃል መሠረት በመቀራረብ፣ በመስማማት፣ ይቅር በመባባል ፣በአንድነት፣ በእኩልነት፣ በሰላም እና በፍቅር ልንኖር ይገባል ሲሉ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ቀዳማዊ ፓትርያርክ ርዕሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ዘአክሱም ወዕጬጌ ዘመንበረ ተክለ ሃይማኖት ገለጹ። የመስቀል ደመራ በዓል ትናንት በመስቀል አደባባይ በደማቅ ሁኔታ ተከብሯል።

በበዓሉ ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ፓትርያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስን የበዓል መልዕክት የቤተክርስቲያኗ የመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ዋና ሥራ አስኪያጅና የባህር ዳር ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ አብርሃም አቅርበዋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ በመልዕክታቸው፤ ነገረ መስቀል ለእምነት፣ ለሰላም፣ ለአንድነት፣ ለእኩልነት፤ ለነጻነት እና ለሰው ልጆች ደህንነት የሚከፈል የሰላም መስዋዕት መሆኑን ጠቁመዋል። በመስቀሉ ቃል መሠረት በመቀራረብ፣ በመስማማት፣ ይቅር በመባባል ፣በአንድነት፣ በእኩልነት፣ በሰላም እና በፍቅር ልንኖር ይገባል ብለዋል።

መስቀል ሌላውን ማክበር ራስን ዝቅ ማድረግን የሚያስተምር ነው እንጂ ራስ ወዳድነትን አያስተናግድም ያሉት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ፤ ሰው ይከበር፣ የተበደለ ይካስ፣ እግዚአብሔር ይደመጥ፣ መስቀል ማክበር ማለት ይህ ነው ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ በመልዕክታቸው፤ በምድር ፍትህ እና ርትዕ፣ ፍቅር እና ሰላም ይንገስ ይቅርታ እና መከባበር ይስፈን። ይህ ሲሆን ሀገር በመንፈሳዊና በቁሳዊ በረከት ትባረካለች፣ ትለማለች፤ ታድጋለችም ነው ያሉት።

«የመስቀሉ ነገር ለሚጠፉት ሞኝነት ነው፣ ለእኛ ለምንድነው ግን የእግዚአብሔር ኃይል ነው» ተብሎ ተጽፏል። መስቀሉን የምንሰብከው በቃል ብቻ ሳይሆን በተግባራዊ ሕይወትም ጭምር ነው ሲሉም ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ አመልክተዋል።

የመስቀሉ ቃል ይህ ሆኖ ሳለ፤ በተቃራኒው እየተተረጎመ ነው ያሉት ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ፤ አንድ ሁኑ ሲባል መለያየትን እንመርጣለን፣ ሰላም ሁኑ ስንባል መጣላትን እንፈልጋለን፣ ታረቁ ስንባል አንቀበልም እንላለን፣ ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ ስንባል በክንዳችን መመካትን እንመርጣለን ብለዋል።

«የመስቀሉን ቃል ከልብ ብንቀበለውና ብናዳምጠው ይበጀናል። በመስቀሉ ቃል በመቀራረብ፣ በመስማማት፣ ይቅር በመባባል በአንድነት፣ በእኩልነት፣ በሰላም እና በፍቅር ልንኖር ይገባል» ሲሉም ነው ያሳሰቡት።

የባህልና የስፖርት ሚኒስትር አቶ ቀጄላ መርዳሳ በደመራው በዓል ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት፤ የመስቀል በዓል ፍቅር፣ አብሮነት፣ መረዳዳት፣ አንድነትና ሰላምን የሚያስተምር እንደመሆኑ፤ የበዓሉን አስተምህሮ መከተል እንደሚገባ አመልክተዋል።

በደመራ ሥነ ሥርዓቱ ላይም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ብጹዓን አባቶች፣ የሰንበት ትምህርት ቤት መዘምራን፣ የእምነቱ ተከታዮች እንዲሁም ዲፕሎማቶች እና ከተለያዩ ሀገራት የመጡ ጎብኚዎች ተገኝተዋል።የሰንበት ትምህርት ቤት ተማሪዎች በዝማሬ፣ ዲያቆናትና ካህናት በያሬዳዊ ዝማሬ፣ በወረብና መወድሶች አድምቀው አክብረውታል።

## ሁሉም ዜጋ ለሀገር ሰላምና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

የዘንድሮ መውሊድ በዓል ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ 4ኛ ዙር ውሃ ሙሌት በተከናወነበት ማግስት መሆኑ ልዩ ያደርገዋል ሲሉም ተናግረዋል። ሁሉም ዜጋ ለሀገር ሰላም፣ አንድነትና ብልጽግና ሊሠራ እንደሚገባም ሼህ አብዱልከሪም በድረዲን አሳስበዋል።

በበዓሉ አከባበር ላይ ተገኝተው የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት ያስተላለፉት የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ ዋና ፀሐፊ ሊቀ ትጉሀን ቀሲስ ታጋይ ታደለ እንዳሉት፣ ኢትዮጵያዊያንም ሰውን የመውደድ፣የማክበርና የማፍቀር የምንኮራበት እሴት አለን፡፡ ይህን ጠንካራ እሴት ጠንቅቀው የማያውቁ አካላት ግን ሊከፋፍሉን የተለያዩ ሙከራዎችን ሲያደርጉ ይስተዋላል ብለዋል፡፡

ሊቀ ትጉሃን ታጋይ እንዳሉት፣ ነብዩ መሐመድ (ሰዐወ) ከዛሬ 1 ሺህ 400 ዓመት በፊት ተከታዮቻቸውን ወደ ኢትዮጵያ ሲልኩ ኢትዮጵያውያን ፍትሕ እና ርትዕ ያላቸው እንዲሁም ሁሉንም የሚያከብሩ መሆናቸውን በማወቃቸው ነው።

ይህ የነብዩ መልዕክት እኛ ኢትዮጵያውያን የምንኮራበት የአብሮነት እሴታችን ስለሆነ ይህንን የሚያኮራ ታሪካችንን ይዘን መከባበራችንን፣ መዋደዳችንን እና አንድነታችንን ማጠናከር አለብን ብለዋል።

የባህልና ስፖርት ሚኒስትሩ አቶ ቀጀላ መርዳሳ በዓሉ ላይ ተገኝተው ባስተላለፉት መልዕክት፤ በዓላትን ስናከብር ሰላምና ፍቅር ልንሰብከባቸው ይገባል ብለዋል።

## "ደመራ ለሀገራችን እድገትና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ምሳሌያችን፤ እውነተኛው መስቀል የተለየበት፤ኢትዮጵያም ልጆቿ የሚቆሙበትና የሚሄዱበት እውነተኛ አቅጣጫ ለተስፋዋ ብርሃን፣ ለጥንካሬዋም ፈለግ ይሆናታል።

ልክ መስቀሉን ፈልጎ ማግኘት እጅግ ከባድ ሆኖ ጊዜ እንደወሰደው ብልጽግናን መሻትም እንዲሁ ብዙ ድካምና ጥረት ይፈልጋል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር)፤ መስቀሉን ማግኘት የብዙዎችን መተባበርና ምክር እንደመፈለጉ በሀገራችን ብልጽግናን ማረጋገጥም በዚሁ ልክ መተባበርና አብሮነትን መፈለጉ ከልቦናችን ይቀመጥ ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ(ዶ/ር) በመልዕክታቸው እንደገለጹት፤ ደመራ የመለወጥ ምልክትነት ነው። ለወንጀለኞች ስቅላት ይውል የነበረ መስቀል ዋጋና ምልክቱ የተለወጠበት ነው። ብዙ ሰዎችን ሰብስቦ በኅብረት የሚያቆም ነው። ባነሰው ላይ መጨመር ነው። የተበተነውን መሰብሰብ ነው። የተዘረዘረ ነገርን የሚደምርና የሚያገናኝ ነው።

ደመራ ለበዓለ መስቀል ዋዜማ እንጨቶች የሚደመሩበት ነው። እንጨቶች ተሰብስበው ችቦ፤ ችቦዎች ተሰብስበው ደመራ የሚሆኑበት ነው። የችቦ እንጨቶችና ጭራሮዎች ምን ቢበዙ ወደ አንድ ካልመጡ ችቦ አይሆኑም። እንጨቶቹን የሚያስተሳስራቸው የማሠሪያ ልጥ አለ። ችቦዎቹም በጋራ ተደጋግፈው ካልቆሙ ደመራ አይሆኑም። ችቦዎቹን አንድ አድርጎ የሚያቆማቸው የመሐሉ እንጨት አለ። ይህ እንጨት ጠንካራና በዙሪያው የተሰባሰቡትን ችቦዎች መሸከም የሚችል ነው። ይህ ምሰሶ ኢትዮጵያን የሚወክልም ነው ብለዋል።

የችቦው ሁሉም ጭራሮዎች አንድ ዓይነት አይደሉም። ከአንድ ቦታም አይለቀሙም። ሁሉም ችቦዎችም ተመሳሳይ አይደሉም፤ ከአንድ ቤት አይመጡም። ሁሉም እንጨቶች በየራሳቸው ይቆማሉ፤ ግን ደግሞ ብርታትና ጥንካሬ፣ አቅምና ጉልበት እንዲኖራቸው ችቦ ሆነው ይደመራሉ። እንጨቶቹን እንደሚያስተሳስረው ልጥ፣ ኢትዮጵያውያንን የሚያስተሳስሩ ልዩ ልዩ ማንነቶች አሉ። ደመራ በመሰባሰብ የሀገራችንን ከፍታ እውን ለማድረግ የምንሰባሰብበት ተምሳሌታችን ነው ሲሉም አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ እንደ ችቦ እንጨቶች ብዙ ባህሎች፣ እምነቶች፣ ሀብቶች፣ ዕሴቶች፣ አመለካከቶች፣ ታሪኮች አሏት። ሁላችንም የግድ አንድ ዓይነት ማሰብ አይጠበቅብንም፤ የግድ ከአንድ ባህል፣ ከአንድ ቋንቋና ከአንድ ማንነት መገኘት አይኖርብንም። እነዚህን ሁሉ ጸጋዎች ከደመርናቸው፣ መጀመሪያ እንደ ችቦው አካባቢያዊ አቅም ይሆኑናል። ቀጥሎ ደግሞ እንደ ደመራው አስተሳስረን በአንድ ዓምድ ላይ ካቆምናቸው ትልቅ ሀገር እንገነባለን ብለዋል ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በመልዕክታቸው።

ይህ ችቦዎቹን አንድ አድርጎ የሚያቆመው የመሐል እንጨት አንድ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማኅበረሰብ የምንፈጥርበት የፌዴራል ሥርዓት ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ኅብረ ብሔራዊ አንድነታችን ነው። ኢትዮጵያዊነታችን ነው። በዚህ የኢትዮጵያዊነትና የኅብረ ብሔራዊ አንድነት ደመራ፣ ግርማዋ የሚያስፈራ፣ የበለጸገች፣ ጠንካራ፣ ታላቅ የጋራ ሀገር መገንባት እንችላለን። የዚህ ሁሉ ቀመሩ ግን- እንደ ደመራው፣ መደመር ነው ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ እንደገለጹት፤ ችቦውን በየግልና በየአካባቢያችን ልንሠራው እንችላለን። ደመራውን ግን በጋራ ካልሆነ አንደምረውም። የመጣንበት መንገድ ለየቅል ሊሆን ይችላል። እምነታችን፣ ምርጫችንና ምኞታችንም የየብቻችን ችቦ ሊሆን ይችላል። ሀገራችን ግን የጋራችን ደመራ ናት። ያለሁላችን አትኖርም። ምን ብንጓጓ ደመራውን ቾኩለን ለብቻችን አንለኩሰውም። የግድ ሌላውን እንጠብቃለን። እንደ ሀገር እንጂ እንደ ንዑስ አካባቢ፣ ወይም እንደ ሠፈር እኔና የኔ ብቻ ማለት አንችልም። ደመራው ለሁላችን በሚሆን ሥርዓት የሚመራ የሁላችንም ሀገር መስታወት ነው።

ደመራው በኔ ችቦ በኩል ቀድሞ ይለኮስልኝ አንልም። ደመራው ሲለኮስም ‹የኔ ችቦ ትቀጣጠል› ይሆን ብለን አንሠጋም። ከየትም ይጀመር ከየት፣ ሙቀትና ብርሃኑ ለሁሉም እንጨቶችና ችቦዎች በሂደት ይዳረሳል። የኢትዮጵያ ሠናይ እሳት የሆነው የኢትዮጵያ ዕድገት፣ የትም መንደድ ቢጀምር፣ በጊዜ ሂደት ለሁላችን ይደርሳል። አንዱ እንጨት ለሌላው፣ አንዱ ችቦ ለሌላው ብርሃን እንዲሆን በማጋራቱ ከእርሱ የሚጎድልበት ነገር የለም። ነገር ግን የሚጨምረው አቅም አለ። ሁሉም እየተለኮሱ በሄዱ ቁጥር፣ የብርሃኑ አቅም እየጨመረ ይሄዳል ሲሉም አብራርተዋል።

እኛም ለሌላው ወገናችን ባካፈልን ቁጥር የሚጎድልብን ነገር የለም። የኢትዮጵያ አቅም ግን እየጨመረ፣ እየጠነከረ ይሄዳል። ትኩረታችን የገዛናት ወይም ሠርተን ያመጣናት ችቧችን ሳትሆን ትልቁ ደመራ ነው። የበዓሉ አመስጥሮ ያለውም ከዚሁ ነው ብለዋል።

ችቦውን ልንገዛውና ልንሸጠው እንችላለን። ደመራው ግን ልክ እንደ ኢትዮጵያ ነው። አይሸጥም አይለወጥም። ሁሉም በግል ይዤው ልሂድ አይልም። እዚያው በጋራ ደምረን፣ በጋራ ልቦናችን ይዘነው የምንሄደው - የወል እውነታችን ነው። የኛነታችን ካስማችንም ጭምር ነው። የዘንድሮውን የደመራ በዓል እነዚህን ታላላቅ ዕሳቤዎች እያሰላሰልን እንደምናከብረው ተስፋ አደርጋለሁ ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የመስቀል በዓልን ስናከብር የመስቀሉን እሴት በመረዳት ይሁን!

ኢትዮጵያ ለዓለም ቅርስነት ካበረከተቻቸው ዘርፈ ብዙ ሀብቶቿ መካከል የመስቀል ደመራ በዓል አንዱ ነው። ይሄ በዓል መሠረቱን የክርስትና እምነት አውድ ሥር ያድርግ እንጂ፤ በእሴትና ሀብትነቱ ግን የመላው ኢትዮጵያውያን፣ አልፎም የዓለም ሕዝቦች ነው። በመሆኑም የመስቀል በዓል እንደ ኢትዮጵያ ከፍ ብለን ከምንገለጽባቸው የበዙ እሴቶቻችን መካከል አንዱ እንደመሆኑ፤ በዚሁ እሴቱ ልክ ከፍ ብለን ልናከብረው የተገባ ነው።

ምክንያቱም የመስቀል በዓል፣ ከኃይማኖታዊ ይዘቱ ባሻገር፤ እኛ ኢትዮጵያውያንን የሚያስተሳስርበት እንዲሁም የዓለምን ሕዝብ ቀልብና ልብ የሚይዝበት የጋራ እሴት አለውና። ይሄ እሴቱ ደግሞ፣ ስለ ሕዝብ ራስን ማስገዛትን፤ ስለ ክቡሩ የሰው ልጅ ራስን አሳልፎ መስጠትን፤ ስለ ትውልድ ተስፋና መዳን ዋጋ መክፈልን፤ ስለ ፍቅር ሲባል መተናነስን፤ ስለ ኅብረት ሲባል በፍቅር መተሳሰር፤ ስለ ሕልምና ስኬት ሲባል ለፈተና እና ድካም እጅ አለመስጠትን፤... በውስጡ አምቆ የያዘ፤ ይሄውም አሰናስሎ የሚገለጽበት ነው።

የመስቀልን በዓል ስናከብር ልናስባቸው ከሚገቡን ጉዳዮች መካከል አንዱና ዐቢዩ ቁም ነገር፤ አይሁድ ክርስቶስ የተሰቀለበትን መስቀል በተራሮች መካከል በመቅበርና እላዩ ላይ ቆሻሻ በመከመር እንዳይገኝና እንዲረሳ ማድረጋቸው ነበር። ነገር ግን ሁሉም በጊዜው ይሆን ዘንድ ግድ ነበርና ይሄን እንድታደርግ የተፈቀደላት ንግሥት ዕሌኒ በጥበብና ተስፋ ባለመቁረጥ የተቀበረው መስቀል እንዲወጣ አድርጋለች።

ዛሬም ይሄንን በዓል ስናከብር እንደ ሀገር በሰላማችን፣ በልማታችን፣ በአብሮነትና ኅብረታችን ላይ እንደ ቋጥኝ ተጭነው የሚያንገታግቱን አያሌ ችግሮች አሉ። እነዚህ ችግሮች ግን የእኛን ዝለት፣ ትዕግስትና ማስተዋል አልባነት፣ ጊዜና ሁኔታን አለማገናዘብ፣ ተገን አድርገው የተጫኑን ናቸው። በመሆኑም ከእነዚህ ያልተገቡ የዝለት፣ የትዕግስትና ማስተዋል አልባነት፣ የጊዜና ሁኔታን አለማገናዘብ ችግሮቻችን እልፍ ብለን፤ ጽናት፣ ብልሃት፣ ትዕግስት፣ ማስተዋልና ማገናዘብን ሀብታችን በማድረግ ልንሻገራቸው የተገባ ነው።

ይሄን የምናደርገው ግን የመስቀሉን በዓል የማክበራችንን እሴት ስንረዳ ነው። የመስቀሉ በዓል ያጎናጸፈንን ማህበራዊ እና ሰብዓዊ ልዕልና በልኩ ስንገነዘብ ነው። ይሄንን ስንገነዘብ እንጸናለን። ይሄንን ስንገነዘብ ለሰብዓዊነት ዝቅ እንላለን፤ ይሄንን ስንገነዘብ ስለ ሌሎች መኖር ራሳችንን እናስገዛለን፤ ይሄንን ስንገነዘብ አጠቃላይ ስለ ሰው ልጅ እና ሀገር ልዕልና እንተጋለን። እንደ አጠቃላይም ስለ ሕዝቦች አብሮነት፣ ስለ ሀገር ብልጽግናና ልዕልና ከችግሮቻችን ልቀን እንገኛለን።

እንዳይገኝ፣ እንዳይገለጥ፣ ለሕዝቦች የመዳን ምክንያት እንዳይሆን፣ በጥቅሉ ከፍ ያለው የሰው ልጅ አበርክቶው እንዳይገለጥ በጉድጓድ የተቀበረው እና በቆሻሻ ክምር ውስጥ እንዲሸሽግ የሆነው መስቀሉ፤ ከብዙ ድካም በኋላ እንዲገኝና እንዲወጣ የሆነውም ለፈተና አለመንበርከክን፣ ለችግር እጅ ያለመስጠትን፣ ለማደናገሪያ ሃሳቦች ቦታ መንፈግን ገንዘቧ ባደረገችው ንግሥት ዕሌኒ እንዲወጣ ከመደረጉም የምንማረውም ይሄንኑ ነው።

ምክንያቱም፣ ታሪኩ እንደሚያስረዳን፤ በ326 ዓ.ም የንጉሥ ቆስጠንጢኖስ እናት ንግሥት ዕሌኒ ቅዱስ መስቀሉን ለመፈለግ ወደ ኢየሩሳሌም ተጉዛ ጉብታ የሆነውን ሁሉ ብታስቆፍርም መስቀሉ ያለበትን ቦታ ማግኘት አልቻለችም። ሰውም ብትጠይቅ የሚያውቅ አልተገኘም። ነገር ግን የመስቀሉ መገኘት የእግዚአብሔር ፈቃድ ስለነበር አንድ የታሪክ አዋቂና ሽማግሌ አግኝታ ቅዱስ መስቀሉ የተቀበረበትን አካባቢ ጠየቀችው።

ሽማግሌውም፣ እሷም በከንቱ ከምትደክም፣ ሰውንም ከምታደክም ይልቅ እንጨት ሰብስባና ዕጣን አድርጋበት በእሳት እንድትለኩሰው ነገሯት። የዕጣኑ ጢስ ወደ ላይ ወጥቶ ሲመለስ አቅጣጫውን አይታ እንድታስቆፍርም መከሯት። እሷም የአረጋዊውን ምክር ሰምታ ያሏትን አደረገች፤ እናም ጢሱ ወደላይ ወጥቶ ወደታች ሲመለስ መስቀሉ ያለበትን ቦታ የመጠቆም ያህል አመለከተ።

ንግሥት ዕሌኒም ጢሱ ያረፈበት ቦታ መስቀሉ ያለበት ስለመሆኑ አምና አስቆፈረች፤ መስከረም 17 አስጀምራ እስከ መጋቢት 10 ሌሊትና ቀን ለሰባት ወራት ያህል በማስቆፈር መስቀሉ እንዲወጣ አደረገች።

ዛሬ እኛ የምናከብረው የመስቀል በዓልም አስተምህሮው፣ እኛ ኢትዮጵያውያን የንግስቲቱን ሕልምና መሻት፤ የንግሥቲቱን ጽናት፤ የንግሥቲቱን ማስተዋል፤ የንግሥቲቱን ብልሃት፤ የንግሥቲቱን ምክር ሰሚነት፤ የንግስቲቱን ትዕዛዝ ፈጻሚነት ገንዘባችን እንድናደርግ ነው። ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ዛሬ የሚያስፈልገንም ይሄው ነው።

ከዛሬ የተሻገረ የሩቅ ሕልም ስለመያዝ፤ ከዕለት ያለፈ ለብዙዎች መሻገሪያ የሚሆን አቅምን ሃብት ስለማድረግ፤ ስለ ፍቅርና አንድነት፣ ስለ ይቅርታና ዕርቅ፣ ስለ ሰላምና ብልጽግና በጋራ ቆሞ ስለ መመካከር፤ በጥቅሉ ከበዙ ፈተናዎቻችን መረብ ልቀን ለመገኘታችን አቅም ስለሚሆኑን ጉዳዮች ቅድሚያ በመስጠት ስለመምከር እያሰብን ሊሆን ይገባል።

የመስቀሉ በዓል አስተምህሮም፤ የመስቀሉ አጠቃላይ እሴትም ይሄንኑ እንድናደርግ የሚያስገድደን ነው። ስለሆነም የመስቀሉን በዓል ስናከብር እነዚህንና ሌሎች አያሌ የመስቀሉን እሴቶች በመረዳትና በመላበስ ሊሆን ይገባል!

**አዲስ ዘመን**
ኢፕድ
ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው።በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።

## ባህላዊ እሴቶቻችንን ጠብቀን ለቀጣይ ትውልድ ማስተላለፍ የሁላችንም ሃላፊነት ነው

ብርሃን ፈይሳ

በዓለም ላይ ታዋቂ ከሆኑ ተጓዦችና ይህንንም በተንቀሳቃሽ ምስል አማካይነት በማህበራዊ ድረገጾች ለተቀረው ዓለም በማጋራት ከሚታወቁት መካከል አንዱ የሆነው ዊሊያም ሶንባችነር (ሶኒ) የቅርብ ጊዜ መዳረሻው ኢትዮጵያ ነበረች። ይህ አሜሪካዊ የቀድሞ ፊልም ባለሙያ ትኩረቱን በምግብ፣ በመጠጥና አዘገጃጀቱ ላይ ያደረገ «ቤስት ኤቨር ፉድ ሪቪው ሾው» በሚል የሚጠራ ድረገጽ አለው ፤ በዩቲዩብ ገጹ 10 ሚሊዮን የሚሆኑ ተከታዮች አሉት።

በመላው ዓለም ባሉ ሀገራት በመዘዋወር ባህልን እና የባህል አመጋገብን ለሌሎች ያጋራል። በዚህም በአጠቃላይ 2 ነጥብ 29 ቢሊዮን እይታ ሲኖረው፤ እአአ በ2020 ከኢንተርኔት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ላይ ዕውቅና በሚሰጠው «ዌብ አዋርድስ» የክብር ሽልማት ተበርክቶለታል። ታዲያ ይህ ተጓዥ ከሰሞኑ በአዲስ አበባ እንዲሁም በደቡብ ክልሎች (ዶርዜ እና ኦሞ አካባቢዎች) በመዘዋወር የመልከዓምድር አቀማመጡን በወፍ በረር እያስቃኘ፤ በተገኘባቸው ሥፍራዎች ያለውን የምግብና መጠጥ አዘገጃጀት፣ አቀራረብ፣ አመጋገብ እንዲሁም የጉርሻ ባህላችንን ሳይቀር ተመልክቷል፣ ለተቀረው ዓለምም አስመልክቷል።

እንደዚህ ያሉና ትኩረታቸውን በመሰል ጉዳዮች ላይ ያደረጉ የባህል ተጓዦች (ጎብኚዎች) በተለያዩ ሀገራት በመገኘት መንፈሳዊም ሆኑ ሌሎች ባህላዊ በዓላትንና አከባበሮች ላይ ይታደማሉ። ማህበረሰቡ ውስጥ በመግባትም የአኗኗር ሥርዓቱንና ባህላዊ ክዋኔዎች ላይ ተሳትፎ በማድረግም ጭምር ዳሰሳ ያደርጋሉ፤ የተመለከቱንም ለሌሎች ያጋራሉ።

ሶኒ በሚል ቅጽል የሚታወቀው ይህ ተጓዥ በዩቲዩብ በመቶ ሺዎችና በሚሊዮኖች የሚቆጠር እይታ ያለው እንደመሆኑ፤ በመላው ዓለም ካለው ተደራሽነቱ አንጻር የኢትዮጵያ እና የኢትዮጵያውያን ባህል ምን ያህል ሊታይ እንደሚችል በቀላሉ መረዳት ይቻላል። ኢትዮጵያን ከማስተዋወቅና መረጃ ከመስጠት ባለፈም በርካቶችን ሊያነሳሳና ኮምፓሳቸውን ወደ ምስራቅ አፍሪካ እንዲያቀኑ ሊያደርግ እንደሚችልም ግልጽ ነው።

ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ወዲህ እጅግ እያደገ ያለ የቱሪዝም ዘርፍ ሀገርና ባህልን ከማስተዋወቅ ባለፈ ከጎብኚዎች የሚገኘው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም እንደ ኢትዮጵያ ያሉ የባህል መገኛ የሆኑ ሀገራት ባህላቸውን በመጎብኘት ለሚዝናኑ ጎብኚዎች ሳቢ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

ከሌላው ዓለም የተለየ የቀንና የዓመት አቆጣጠር ያላት ኢትዮጵያ አዲስ ዓመቷን ተከትሎ እንደ መስቀል እና ኢሬቻ ያሉ ባህሎች በድምቀት ይከበሩባታል። ታዲያ ይህ አከባበር እንዲሁም በዓሉን ተከትሎ የሚከወኑ ባህላዊ ጉዳዮች ለጎብኚዎች የስበት ማዕከላት ናቸው። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሳይንስ፣ የባህል እና የትምህርት ድርጅትም (ዩኔስኮ) በዚሁ ምክንያት በዓላቱና ሥነሥርዓታቸው የኢትዮጵያውዊያን ብቻም ሳይሆኑ የዓለምም ብርቅዬ ቅርሶች ናቸው በሚል እንደመዘገባቸው ይታወቃል።

እነዚህ በዓላት እሴቶቻቸውን ጠብቀው እንዲከበሩ ማለትም መስቀል ሃይማኖታዊ ሥርዓቱ በሚፈቅደው፤ ኢሬቻም የገዳ ሥርዓቱን ተከትሎ እንዲከበር የህብረተሰቡ አስተዋጽኦ ወሳኝ ነው። በዓላቱ የአንድ ዕለት አከባበሮች ብቻ ሆነው አያልፉም፤ ይልቁንም በርካታ ኢትዮጵያዊ ጉዳዮችን በተግባር የሚያስቃኙ አለፍ ሲልም በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ላይ የራሳቸውን አሻራ ማሳረፍ የሚችሉ ናቸው።

ሃይማኖታዊ በዓል የሆነው መስቀል የዳመራ ሥነሥርዓቱ በአደባባይና በአጥቢያዎች የሚከወን እንደመሆኑ ከሃይማኖታዊ ጉዳይ ባለፈ የኢትዮጵያውያን አንድነትና አብሮነት የሚንጸባረቅበት መስታወት ነው። ባህላዊ አለባበሱ፣ አመጋገቡ፣ ... ለጎብኚዎች አስደሳች የሆነ ትዕይንትም ነው። በዓሉ በተለይ በድምቀት በሚከበርባቸው የደቡብ፣ ሰሜንና ማዕከላዊ የሀገሪቷ ክፍሎች ቤተሰብ ተሰባስቦ ማክበሩ የግድ እንደመሆኑ ማህበረሰባዊ አብሮነትን ይፈጥራል። ይህንኑ ጊዜ

**ሃይማኖታዊ በዓል የሆነው መስቀል የዳመራ ሥነሥርዓቱ በአደባባይና በአጥቢያዎች የሚከወን እንደመሆኑ ከሃይማኖታዊ ጉዳይ ባለፈ የኢትዮጵያውያን አንድነትና አብሮነት የሚንጸባረቅበት መስታወት ነው። ባህላዊ አለባበሱ፣ አመጋገቡ፣ ... ለጎብኚዎች አስደሳች የሆነ ትዕይንትም ነው**

ጠብቆ እንደ እርቅ እና ጋብቻ ያሉ ሥርዓቶች በስፋት ይከናወናሉ። ይኸም በሌላው ዓለም የሌለ በኢትዮጵያውያን ዘንድ የተለመደ ባህላዊ ሁነት መሆኑ ጎብኚዎችን በእጅጉ ይስባል።

የአደባባይ በዓል የሆነው ኢሬቻም በተመሳሳይ፤ የኦሮሞ ህዝብን ብቻም ሳይሆን በርካቶችን ከሌሎች ብሄረሰቦችም ጭምር በማሰባሰብ አብሮነት በእጅጉ የሚንጸባረቅበት ነው። የገዳ ሥርዓት ከሚያዘው የበዓሉ አከባበር ባለፈ አንዱ ከሌላው የሚተዋወቅበት የባህል ፌስቲቫልም ጭምር ነው። በዓሉ በሚከወንበት ሥፍራ የሚገኝ የትኛውም ጎብኚ ኢትዮጵያ ያሏትንና በአዘቦት ጊዜያት ሊያገኛቸው የማችላቸውን ባህላዊ አለባበሶችን፣ ጌጦችን፣ የጸጉር አሠራርን፣ የባህል ቁሳቁስን፣ ሙዚቃ፣ አጨፋፈር፣... በስፋት ሊመለከት ይችላል። በሌላ አነጋገር ለዘመናት ሲገነቡ የኖሩትን የኢትዮጵያ ባህሎች በአንድ ቀን ለመመልከት ይችላል። ጎብኚዎችም ይህንን ዕድል ለመጠቀም እነዚህን ወቅቶች እንደሚመርጡ አስቀድሞ ስለበዓላቱ በቂ ግንዛቤ መያዝ ያስፈልጋል።

እነዚህን ባህላዊ ሁነቶች ኢኮኖሚ ፋይዳቸውን ከተመለከትንም ፤ የጎብኚዎች ማረፊያና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን የሚያቀርቡ ተቋማት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ሊገኝ እንደሚችል ማብራሪያ የማያሻው ጉዳይ ነው። ከዚህ ባለፈ ግን የበዓላቱ ታዳሚ ለመሆን ወደ ኢትዮጵያ የሚመጡት ጎብኚዎች የባህሉ አካል የመሆን ፍላጎት ስለሚያድርባቸው አልባሳቱን፣ ጎጣጌጦቹን እንዲሁም ሌሎች ኢትዮጵያን የሚያስታውሱ ቁሳቁሶችን የሚሸጡ አካላትም በገንዘብ ተጠቃሚ ያደርጋሉ። በዚህም ጎብኚዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚኖራቸውን ጠቀሜታ ከፍ ያለ ነው።

በመሆኑም መዳረሻቸው እንድንሆን ያደረጉትን እንዲሁም የዓለም ቅርስ በሚል ተመዝግበው በርካቶችን እንድንስብ ያስቻሉንን ባህሎቻችንን ከምንም በላይ ልንጠብቃቸው ይገባናል። ሌላው ዓለም ላይ የጠፋውንና እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት ግን አሁንም ድረስ ያሉ ባህሎችን ከዘመኑ ጋር ማስኬድ እንጂ መበረዝም ሆነ እርግፍ አድርጎ በመተው ዘመንኛውን መከተል ማንነትን የመካድ ያህል ነው።

“ባለቤቱ ያቀለለውን .....ባለእዳ” እንደሚባለው ሁሉ ዩኔስኮ የመዘገባቸው/በዓለም አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኙ / ቅርሶቻችን ከጠፉ ወይም የመበረዝ አደጋ ካጋጠማቸው ከ መዝገብ መሰረዛቸው የማይቀር ነው። ከዚህ የተነሳ ዘመናትን ተሻግረው እዚህ የደረሱ መገለጫዎቻችንን ለቀጣይ ትውልድ ጠብቀን ማስተላለፍ የሁላችንም ሃላፊነት ነው ። “በእነሱ ጊዜ ጠፉ” የሚል ጠባሳ በታሪካችን ላይ እንዲያርፍ መፍቀድ የለብንም። በተለይ ወጣቱ ትውልድ ባህሎቹን እንደ ዓይኑ ብሌን ሊጠብቃቸውና ሊንከባከባቸው ይገባል።

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ



በቀምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል። በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

# የመስቀል ደመራ በዓል ታሪክና አከባበር

**እንኳን ስብርሃነ መስቀሉ አደረሰን አደረሳችሁ! አሜን። እንዲሁም ስያሆዴ፣ መሰላ፣ ማሽቃሮ፣ ጊፋታ፣ ጋሪዎሮ፣ ሄቦ፣ ዮ መስቀላ እና ጋዜ መስቀላ የዘመን መለወጫ በዓላት በሰላም አደረሳችሁ !**

ግራ ቢገባኝና ቢቸግረኝ ዛሬ ደግሞ መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ በዓሎቻችን በሕይወታችን አልታይ አልገለጥ ያሉት መንፈሳዊ ትዕምርቶችንና አንድምታቸውን በውል ስላልጨበጥን ይሆን በሚል ስለመስቀል በዓል መንፈሳዊ አንድምታና አከባበር ይቺን መጣጥፍ ይዤ መጣሁ። ከ2000 ዓመታት በፊት በመስቀሉ ድል የተነሳው ጥል ፣ ልዩነት ፣ ዘረኝነት ፣ ወዘተረፈ እንዴት እንደ እባብ አፈር ልሶ ተነስቶ ሀገራችንን እንዴት በዚህ ደረጃ ሊንጣት ቻለ? የህልውናዋ ስጋት ሊሆን ቻለ? በነገራችን ላይ እንደ ክርስትና መንፈሳዊ በዓላት ኢሬቻንም ሆነ ረመዳንን ፣ አረፋንም ሆነ ጨምበለላን ፣ ወዘተረፈ ከማክበር ወጥተን በተግባር በሕይወታችችን እስካልኖርናቸው ድረስ እንዴት ከአዙሪቱ ልንወጣ እንችላለን? የሶስቱ አብርሃማዊ እምነቶች መገኛ ነን እያልን ከመታበይ ባለፍ ከቀውስ ቀለበት ሰብረን መውጣት ካልቻልን ምን ዋጋ አለው? መንግሥትም ፖለቲካዊ ቁርጠኝነት ወስዶ ልዩነትን መዋቅራዊና ተቋማዊ ያደረጉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በማሻሻል ሕዝብን ካላገዘ ከዚህ አዙሪት እንዴት መውጣት ይቻላል? ይሄን ለማድረግ ደግሞ የግድ የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽኑን መጠበቅ አያሻም ። ጊዜ የለንማ ። ወደ መስቀል በዓል አከባበር ስንመለስ ፤

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰውን ልጅ ከወደቀበት መርገም ያድነው ዘንድ ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ በ33 ዓመቱ በራሱ ፈቃድ በመስቀል ላይ ተሰቀለ።በመገረፉ ቁስል እኛ ተፈወስን (1ጴጥ 2፥24):: በስቅለቱም ዲያብሎስን ድል ነሥቶ በወህኒ /በሲዖል/ ለነበሩ ነፍሳት ነጻነትን ሰበከላቸው (1ጴጥ 3፥18-19):: የሰው ልጅ በሙሉ ከዲያብሎስ ባርነት ፍጹም ነጻ ወጣ።ሰላምንም ያደርግ ዘንድ ጥልንም በመስቀሉ ገድሎ ሕዝብና አሕዛብን በአንድ አካል ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ (ኤፌ 2፥16)።ከፍተኛ ወንጀል የሠሩ ሰዎች ብቻ ይሰቀሉበት የነበረው መስቀል ከጌታ ስቅለት በኋላ የመዳን ምልክት ሆነ፡፡

ዳሩ ግን ጌታ የተሰቀለበት መስቀል ተአምራትን በማድረጉ የታወኩ አይሁድ መስቀሉን ከሰዎች እይታ ለመሠወር ወሰኑ።ጉድጓድ ቆፍረው ቀበሩት።መስቀሉ የተቀበረበትን ቦታ ለ300 ዓመታት ያህል የቆሻሻ መጣያና ማከማቻም አደረጉት።ምንም እንኳን አይሁድ ለጊዜው መስቀሉን ከዓይን ለመሰወር ቢችሉም ከክርስቲያኖች ልቡና ግን ሊያወጡት አልቻሉም።የመስቀሉ ብርሃን በልቡናቸው የሚያበራ ክርስቲያኖች እየበዙ መጡ።መስቀሉንም መፈለግ ጀመሩ፡፡

> **ንግሥት እሌኒ ልጇን ቆስጠንጢኖስን ከልጅነቱ ጀምሮ ስለ ክርስትና ሃይማኖትና ስለ ክርስቲያኖች መከራ ታስተምረው ስለነበር በክርስቲያኖች ላይ የነበረው አመለካከት በሮም ከነገሡት ቄሣሮች ሁሉ የተሻለ ነበር**

ንግሥት እሌኒ ልጇን ቆስጠንጢኖስን ከልጅነቱ ጀምሮ ስለ ክርስትና ሃይማኖትና ስለ ክርስቲያኖች መከራ ታስተምረው ስለነበር በክርስቲያኖች ላይ የነበረው አመለካከት በሮም ከነገሡት ቄሣሮች ሁሉ የተሻለ ነበር።ቆስጠንጢኖስ የሮም ንጉሠ ነገሥት ከሆነ በኋላ በ300 ዓመታት ውስጥ ለመጀመርያ ጊዜ ለክርስቲያኖች የነጻነት አዋጅ አወጀ።ክርስትናም ብሔራዊ ሃይማኖት ሆነች።ንግሥት እሌኒም የተፈጠረውን አመች ሁኔታ በመጠቀም የጌታችንን መስቀል ከተቀበረበት ለማውጣት በ327 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም ሔደች፡፡

ንግሥት እሌኒ ልጇ ቆስጠንጢኖስ ክርስቲያን ከሆነላት ወደ ኢየሩሳሌም ሔዳ መስቀሉን ለመፈለግ እንዲሁም በኢየሩሳሌም ያሉ ቅዱሳት መካናትንና አብያተ ክርስቲያናትን ለማሳነፅ ለእግዚአብሔር ተሳለች።ከዚህ በኋላ ቆስጠንጢኖስ አምኖ በ337 ዓ.ም ተጠመቀ።ቅድስት እሌኒም ወደ ኢየሩሳሌም ሔደች እንደደረሰችም ስለ ክብረ መስቀል መረመረች ጠየቀች።ቦታውን የሚያስረዳት ግን አላገኘችም።አይሁድ የተቀበረበትን ቦታ ለማሳየት ባይፈልጉም በኋላ ባደረገችው ጥረት አረጋዊው ኪራኮስ የጎልጎታን ኮረብታ አመላከታት ዳሩ ግን ኪራኮስ ዘመኑ ከመርዘሙ ጋር ተያይዞ በአካባቢው ከነበሩት ከሦስቱ ተራሮች ውስጥ መስቀሉ የሚገኝበት የትኛው እንደሆነ ለይቶ ማወቅ አልቻለም፡፡

ንግሥት እሌኒ ከሦስቱ ተራሮች የቱ እንደሆነ ለመለየት በእግዚአብሔር መልአክ ርዳታ ደመራ አስደምራ ብዙ እጣንም በመጨመርና በማቃጠል ጸሎት ተያዘ።የእጣኑ ጢስ ወደ ሰማይ በመውጣት በቀጥታ ተመልሶ መስቀሉ ባለበት ተራራ ላይ በማረፍና በመስገድ መስቀሉ ያለበትን ትክክለኛ ስፍራ አመለከታት።ቅዱስ ያሬድም ጢሱ ሰገደ ብሎታል።ከዚያም መስከረም 16 ቀን ቁፋሮው እንዲጀመር አዘዘች።ሰባት ወር ያህል ከተቆፈረ በኋላ መጋቢት 10 ቀን ሦስት መስቀሎች በአንድነት ተገኙ፡፡

የክብር ባለቤት ጌታችን የተሰቀለበት የትኛው እንደሆነ ለማወቅ ተቸገሩ፡: መስቀሎቹን ወስደው በሞተ ሰው በተራ ቢያስቀምጡ ጌታችን የተሰቀለበትና በዕለተ ዐርብ ተሰቅሎ የዋለበትና በደሙ መፍሰስ የተቀደሰው መሰቀል የሞተውን ሰው በማስነሣት በሠራው ተአምር ሌሎቹ ሁለቱ ታምራት ባለማድረጋቸው የጌታን መስቀል ለይቶ ማወቅ ተችሏል። እሌኒና ክርስቲያኖች ሁሉ ለመስቀሉ ሰገዱለት።በየሀገሩ ያሉ ክርስትያኖች ሁሉ የመስቀሉን መገኘት በሰሙ ጊዜ መብራት አብርተው ደስታቸውን በመግለጥ ለዓለም እንዲታወቅ አደረጉ።ንግሥት እሌኒ ለመስቀሉ ቤተ መቅደስ ከሠራችለት ጊዜ ጀምሮ በመስከረም 17 ቀን አሁን በኢትዮጵያ እንደሚከበረው በክርስቲያኖች ዘንድ መስቀል ይከበር ነበር።

**ግማደ መስቀሉ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት መጣ?**

የጌታ መስቀል ለብዙ ዓመታት በኢየሩሳሌም ከቆየ በኋላ ነገሥታት መስቀሉን ለመውሰድ ጠብ ፈጠሩ።በዚህ ጊዜ የአንጾኪያ፣ የኤፌሶን፣ የአርማንያ፣ የግሪክ፣ የእስክንድርያ፣ የመሳሰሉት የሃይማኖት መሪዎች ጠቡን አበረዱት።ከዚያም አያይዘው በኢየሩሳሌም የሚገኘውን የክርስቶስን መስቀል ለአራት ከፍለው በስምምነት ተካፍለው ከሌሎች ታሪካዊ ንዋያተ ቅድሳት ጋር በየሀገራቸው ወስደው በክብር አስቀመጡት።የቀኝ ክንፉ የደረሰው ለአፍሪቃ ስለነበር ከታሪካዊ ንዋየ ቅድሳት ጋር በግብፅ የሚገኘው የእስክንድርያ ፓትርያርክ ተረክቦ ወስዶ በክብር አስቀመጠው፡፡

ኢትዮጵያዊው ንጉሥ ዳግማዊ ዳዊት የግብፅ ክርስቲያኖች በአማሌቃውያን ከሚደርስባቸው ተጽዕኖ ነጻ እንዲወጡ በማድረጋቸው የግብፅ ፓትርያርክ የከበሩ ስጦታዎችን ላኩላቸው።ንጉሥ ዳግማዊ ዳዊት ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የምትፈልገው ወርቅ ሳይሆን ጌታ የተሰቀለበትን መስቀሉን እንደሆነ ገለጹላቸው።በመሆኑም የግብፅ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ግማደ መስቀሉን ከሌሎች ንዋየ ቅድሳት ጋር ለኢትዮጵያ ሰጥታለች።ይህ ግማደ መስቀል በግሸን ማርያም ገዳም በእግዚአብሔር አብ ቤተ ክርስቲያን ሆኖ ኢትዮጵያን እየባረከ ይገኛል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መስቀልን ከሐዋርያት በተማረችው መሠረት የወርና የዓመት በዓል ሠርታ ታከብረዋለች።መስከረም 16 ቀን ደመራ ደምራ ጸሎትና ምሥጋና ታቀርባለች። ቅዱስ መስቀል ከተቀበረበት መሬት በእሌኒ አማካኝነት መገኘቱን ስታስብ በአሁኑ ዘመን ከብዙ ሰዎች ልቡና የተሠወረው መስቀል እንዲገለጥላቸው ትጸልያለች።በመስቀል የሚገኘውን በረከት እየተቀበለች በመስቀል የሚመሰለውን መከራ ሁሉ ትታገሣለች።መስቀል በካህናት በምእመናንና በምእመናት ልቡና ተስሏል።በአንገታቸውና ልብሳቸውም መስቀል አለ።ሥራ ሲጀመርና ምግብ ሲቀርብ በመስቀል አምሳያ ይማተባል።መስቀል ለሁሉም ነገር መጀመሪያና መጨረሻ ነው።"እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ" (ማቴ 16፡24) እንዳለ ጌታችን ቤተ ክርስቲያናችን ዕለት ዕለት መስቀሉን ትሸከማለች።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በየዓመቱ መስከረም 16 ቀን የምትደምረው ደመራ ሀገራዊ አንደምታም አለው።የመስቀል ደመራ በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፤ የሳይንስና የባህል ድርጅት (ዩኔስኮ) እውቅና ተሰጥቶት ዓለም አቀፋዊ ቅርስ ተብሎ ተመዝግቧል።

ግማደ መስቀሉ ወደ መካከለኛው ኢትዮጵያ ሳይደርስ በድንገት ዓጼ ዳዊት ስናር በሚባል በረሃ ላይአረፉ ።ግማደ መስቀሉም የግድ በዚያው በስናር መቆየት አስፈለገው።ከዚህ በኋላ የሚቹ የዳግማዊ ዳዊት ልጅ ዓጼ ዘርዓ ያዕቆብ እንደነገሡ ወደ ስናር ሔደው ግማደ መስቀሉን ከሌሎቹ ንዋያተ ቅዱሳት ጋር አምጥተው በመናገሻ ከተማቸው በደብረ ብርሃን ላይ ቤተመቅደስ ሠርተው ለማስቀመጥ ሲደክሙ በሕልማቸው "አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል" ወዳጄ ዘርዐ ያዕቆብ ሆይ መስቀሌን በመስቀለኛ ቦታ ላይ አስቀምጥ የሚል ሕልም አዩ፡፡

ከእስክንድርያ ሀገር ከመስቀሉ ጋር በልዩ ልዩ ሣጥን ተቆልፈው የመጡትም ዝርዝር ስማቸው ጌታ በዕለተ ዓርብ ለብሶት የነበረው ቀይ ልብስ፣ ከሮም የመጣው ከለሜዳው፣ ሐሙት የጠጣበት ሰፍነግ /ጽዋ/፣ ዮሐንስ የሳለው ኩርዓተ ርዕሱ ስዕል እንዲሁም የተለያዩ የቅዱሳን አጽም፣ ከግብጽ ታላላቅ ገዳማት የተቆነጠረ አፈር፣ የዮርዳኖስ ውሃ ይገኛል።ንጉሡም መስቀለኛ ቦታ እየፈለጉ በኢትዮጵያ አውራጃዎች ሁሉ በመፈለግ ከብዙ ቦታ አስቀምጠውት ነበር።ለምሳሌ በሸዋ በደብር ቅዱስ ደብረ ጽጌ ማርያም ገዳም፣ በመናገሻ ማርያም፣ በወጨጫ መስቀሉን አሳርፈውት ነበር።ነገር ግን የመጨረሻውን ቦታ ባለማግኘታቸው በራዕይ እየደጋገመ አንብር መስቅል የበዲበ መስቅል መስቀሌን በመስቀለኛ ሥፍራ አስቀምጥ እያለ ይነግራቸው ነበር።ዓጼ ዘርዓ ያዕቆብም ለሰባት ቀን ሱባዔ ገቡ፡፡

በዚያም የተገለጸላቸው መስቀለኛውን ቦታ የሚመራህ ዓምደ ብርሃን ይመጣል አላቸው።እርሳቸውም ከዚያ እንደወጡ መስቀለኛውን ቦታ የሚመራ የብርሃን ዓምድ ከፊታቸው መጥቶ ቆመ።በዚያ መሪነት ወደ ወሎ ክፍለ ሀገር አምባሰል አውራጃ ውስጥ ግሸን ከምትባል አምባ መርቶ መስከረም21 ቀን 1440 ዓ.ም አደረሳቸው።በእውነትም ይህች ግሸን የተባለችው አምባ ጥበበኛ ሰው እንደቀረጻት የተዋበች መስቀለኛ ቦታ ሆና ስላገኟት የልባቸው ስለደረሰ ደስ አላቸው።በዚያም አምባ ታላቅ ቤተመቅደስ ሰርተው መስቀሉንና ሌሎች ንዋየ ቅዱሳቱን በየመዓረጋቸው የክብር ቦታ መድበው አስቀመጡዋቸው።ዘመኑም በ14ኛው ክፍለ ዘመን ነው፡፡

በሀገራችን በኢትዮጵያ የመስቀል በዓል የሚከበረው አበቦች በሚፈኩበት የጥቢ ወራት መግቢያ በመሆኑ ጸሎቱም (መስቀል አብርሃ በከዋክብት አሠርገወ ሰማየ እምኵሉሰ ፀሐየ አርአየ) ሲሆን ሕዝባዊ ዜማውም (ኢዮሀ አበባዬ ፤ መስከረም ጠባዬ) በማለት የመስቀልን ክብር ሳይለቅ ነው፡፡

በተያያዘም በወሎ ክፍለ ሀገር በአንባሰል አውራጃ ውስጥ በዛሬው ደቡብ ወሎ ግሸን ማርያም የምትባል ደብር ትገኛለች።ግሸን አምባ ከአዲስ አበባ 480 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የምትገኝ ቅድስት ሥፍራ ናት። ይህች ደብር በሐይቅና በመቅደላ በደላንታ በየጁ መካከልና በበሽሎ ወንዝ አዋሳኝ በርዋ አንድ ዙርያውን በገድል የተከበበች አምባ ናት።በበርዋ ከተገባ በኋላ ግቢዋ፣ ከላይ ሜዳና መስቀለኛ ቦታ ነው።ወደዚህች ደብር ለመሔድ በረሃን አቋርጦ ተለያየን ወንዝና በሽሎን በመሻገር የተጠማዘዘ አስፈሪ ገደሉን ማለፍ ግድ ይላል።ግሸን የመጀመርያ ስሟ ደብረ እግዚአብሔር በመባል ይጠራ ነበር፡፡

ይህ ደብረ እግዚአብሔር የሚለው ስያሜም በጻድቁ ንጉሥ ላሊበላ እጅ ከቋጥኝ ድንጋይ ተፈልፍሎ የተሠራ ቤተመቅደስ በእግዚአብሔር አብ ስም ስለነበረ ደብረ እግዚአብሔር ተብሎ ይጠራ ነበር።ከዚያም በዓጼ ድግናዥን ዘመነ መንግሥት የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ሲመሠረት ሐይቅ ደብረ ነጐድጓድ ተብሎ ሲሰየም ግሸን የሐይቅ ግዛት ስለሆነች ደብረ እግዚአብሔር ተብላለች።ከዚያም በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ላይ በዓጼ ዘርአያዕቆብ ዘመነ መንግሥት ግማደ መስቀሉ ግሸን ገብቶ ሲቀመጥ ደብረ ነጐድጓድ የሚለው ደብረ ከርቤ በማለት ተቀይሮአል።በጊሸን ደብረ ከርቤ አምባ በሁሉም ማዕዘን አብያተ ክርስቲያናት የታነፁ ሲሆን ከመስቀሉ ራስጌ የእመቤታችን፣ ከመስቀሉ ግርጌ የቅዱስ ሚካኤል ከቀኝ ክንፉ ላይ ቅዱስ ገብርኤል ከግራ ክንፉ ደግሞ ቅዱስ ዑራኤል ሲሆኑ መካከሉ ላይ መስቀሉ የተቀበረበት የእግዚአብሔር አብ ቤተክርስቲያን ይገኛል፡፡

**ሻሎም !**

**አሜን ።**

# ወቅታዊ

# ‹‹የቱሪዝም ሥራ በመልካም ሥም ላይ የተመሠረተ ነው››

- አቶ ስለሺ ግርማ
የቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ

ስምስም መንግሥቱ

**አዲስ ዓመት የቱሪዝም ኢንዱስትሪውም የሚነቃቃበት ጊዜ ነው። የመስቀልና የኢሬቻ በዓላት ለቱሪዝም ኢንዱስትሪው ደግሞ መዳረሻዎች ናቸው። የአደባባይ በዓል በመሆናቸው በእነዚህ በዓላት ለመታደም ከተለያዩ ሀገራት ቱሪስቶች ወደ ሀገራችን የሚመጡበት ወቅት ነው። በሀገር ደረጃም ማህበረሰቡ በየአካባቢው በተለያየ ዝግጅት የሚያከብራቸው በመሆኑ የተለየ ድባብ አለው።**

**በበዓሉን ለመታደም ከሚመጣው ቱሪስትም የሚገኘው ገቢ በሀገር ምጣኔ ሀብት እድገት ላይ አስተዋጽኦ በማበርከት ዘርፉ ከፍ ያለ ሚና አለው። በየአመቱ በተለያየ መሪ ሃሳብና ዝግጅት በሚከበረው የዓለም ቱሪዝም ቀን ደግሞ ዘርፉን የማነቃቃት ሥራ ይሠራል። የማነቃቃቱ ሥራ የበለጠ ቱሪስቶችን ለመሳብ ያለው ፋይዳም ከፍ ያለ እንደሆነ የባለፉት እንቅስቃሴዎችና ተሞክሮዎች ያሳያሉ።**

**የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ሰላምና መረጋጋት የሚፈልግ እንደሆነ ይታወቃል። ያለፉት ጥቂት ዓመታት ግን ለዘርፉ ምቹ ሁኔታዎች አልነበሩም። የዓለም ሥጋት ሆኖ ያለፈው ኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝን ጨምሮ ሀገር ውስጥ ያጋጠመው ሰላምን የሚያደፈርሱ ክስተቶች ኢንዱስትሪውን ረብሾታል። በዚህ ውስጥም ሆኖ ግን የቱሪዝም ኢንዱስትሪው አልተስተጓጎለም። ጫናዎችን ተቋቁሞ ዘርፉ ተልእኮውን እንዲወጣ የማድረጉ ሥራ እንዴት እንደቀጠለና ከዚሁ ጎን ለጎን የዓለም ቱሪዝም ቀንን አስመልክተን ከቱሪዝም ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ስለሺ ግርማ ጋር ቆይታ አድርገናል። መልካም ንባብ።**



**አዲስ ዘመን፦ በሀገራችን ተከስቶ የነበረውን የፀጥታ መደፍረስ ችግር ጫና ተቋቁሞ የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን እንቅስቃሴ ለማስቀጠል ይደረጉ የነበሩ ጥረቶች እንዴት ይገለጻሉ?**

**አቶ ስለሺ፦** በቱሪዝም ኢንዱስትሪው ላይ ጫና መፈጠር የጀመረው ኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተከሰተ ጊዜ ጀምሮ ነው። በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ተካሂዶ የነበረው ጦርነት ደግሞ ችግሩን የከፋ አድርጎታል። እነዚህ ለተከታታይ ዓመታት የነበሩት ችግሮች ዘርፉ ላይ ጉዳት አስከትለዋል።

በተለይ በኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽ ወቅት የዓለም አቀፍ በረራዎች ባለመኖራቸው እንቅስቃሴዎች ተገትተው ነበር። ወረርሽኙ ንኪኪንም የሚከለክል ስለነበር ሰዎች ለመሰባሰብ ስጋት ውስጥ ነበሩ። በዚህ የተነሳ ሆቴል ቤቶችን ጨምሮ ለቱሪስቱ አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት ሥራው የተስተጓጎበት ጊዜ ነበር።የጉብኝት ሥፍራዎችም ያለፉት በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ነው።

የቱሪስት ቁጥር በመቀነሱ በዘርፉ ተፈጥሮ የነበረ የሥራ ዕድል ላይ መቀነስና መቀዛቀዝ አስከትሏል።ገቢ በማስገኘትም እንዲሁ በተመሳሳይ ተጽእኖ ፈጥሯል። በተለይ ከሥራ ዕድል ጋር በተያያዘ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሠራተኞችን ለመቀነስ በመገደዳቸው በርካቶች ከሥራ ውጭ ሆነዋል።

በጦርነቱ ወቅት ደግሞ አባዛኛዎቹ ኤምባሲዎች የጉዞ ክልከላዎች እንዲደረግና ሰዎችም ወደ ኢትዮጵያ እንዳይመጡ በየድረ-ገጾቻቸው መልእክት በማስተላለፍ ያደርጉት የነበረው እንቅስቃሴ ከፍተኛ ስለነበር የዘርፉ እንቅስቃሴ እንዲቀዛቀዝ አሉታዊ ጎን ነበረው።

የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ገቢ ጎብኚዎችን በመሳብ ብቻ ሳይሆን ለተለያየ ስብሰባ፣ ለኤግዚቢሽን ተሳትፎ፣ ዘመድ ጥየቃ፣ ለመዝናናትና ለጉብኝት፣ ወደ ሌላ ሀገር ለመሸጋገር ለተወሰነ ሰአት ወይም ጊዜ ቆይታ (ትራንዚት) ከሚያደርጉ ጭምር የሚገኝ ገቢ እንደሆነ ግንዛቤ ሊያዝ ይገባል። ከዚህ አንጻር በኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝና በፀጥታ ችግር ምክንያት ብቻ በትንሹ ከአንድ ቢሊን ዶላር ያላነሰ ገቢ አጥተናል።

በሥራ ዕድል በኩል ደግሞ በተለይ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ብቻ በዘርፉ 30 ከመቶ በላይ የሚሆን የሥራ እድል ተፈጥሮለት የነበረ ዜጋ ከሥራ ውጭ ሆኗል። ጦርነቱ አይሎ በነበረበት ወቅት ደግሞ ክፍተቱ የነበረው ሙሉ ለሙሉ በሚባል ደረጃ ነው። በኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያትም በረራዎች ባለመኖራቸው ትግራይ ክልል አክሱም፣ አማራ ክልል ላልይበላ፣ አፋር ዳሎል ኤርታሌ የቱሪስት መዳረሻዎች ሥራ አቁመው ነበር።

በወቅቱ ሙሉ ለሙሉ ዝግ የነበሩና በከፊልም የሚሰሩ ነበሩ። ምክንያቱም ክልከላውን አልፈው የሚመጡ ቱሪስቶች ነበሩ። ምንም አይነት ችግር ቢኖር ተቋቁመው መጥተው የሚያዩ ነበሩ። የማይሰረዝ ጉዞ ወይም ፕሮግራም ያላቸውም ነበሩ። ትውለደ ኢትዮጵያውያንም ዘመድ ለመጠየቅ እንዲሁም እንደሀገር ለዲያስፖራ የተደረገውን ጥሪ ተቀብለው የመጡ ነበሩ። ለመዝናናትም ቢሆን የመጡ ነበሩ።

ለመዝናናት ምቹ የሆኑ ወደ አምስት የቱሪዝም ቀጣናዎች አሉ። የታሪካዊ የመሥመር ጉዞ የምንለው አንዱ ሲሆን፣ ከአክሱም ላልይበላ፣ ጎንደር፣ ባህርዳር፣ ሸዋ አልፎ ወደ አዲስ አበባ የሚመጣ መስመር ነው። ሁለተኛው መስመር ነው። በጅማ፣ ቦንጋ፣ አጋሮ አድርጎ ነቀምት፣ጋምቤላ ድረስ የሚሄድ ነው። ሶስተኛው የምሥራቅ ኢትዮጵያ የጉዞ መሥመር ሲሆን፣ ይህም ከአዲስ አበባ ድሬዳዋ፣ ሐረር፣ጅግጅጋ ድረስ የሚሄድ ነው። አራተኛው አዲስ አበባ ከተማና በዙሪያው ያለው ነው። አምስተኛው ደቡብ ኢትዮጵያ ሲሆን፣ በአብጃታ ሻላ፣ በሐዋሳ፣ አርባምንጭ፣ ዶርዜን ይዞ የደቡብ አካባቢዎችን የሚነካካ የጉዞ መስመር ነው።

ከነዚህ የጉዞ መሥመሮች ውስጥ ሰላማዊ የጉዞ ቀጣናዎች ነበሩ። ለምሳሌ የምሥራቅ የጉዞ መሥመር በአውሮፕላንም በመጠቀም ወደ ስፍራው የሚሄዱበት እድል ነበር። በደቡብና በአዲስ አበባ ከተማም የነበረው በተመሳሳይ ምቹና ጥሩ እንቅስቃሴ ነው። የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ቱሪስቶች በተወሰነ የጉዞ መሥመር ላይ ተንቀሳቅሰዋል። ይህ እንዲሆንም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤታችን አምባሳደሮችን እነዚህ ቦታዎች ድረስ በመውሰድ ካዩ በኋላ የጉዞ ክልከላዎችን እንዲያነሱ የማድረግ ሥራ ተሠርቷል። በጥንቃቄ ቱሪስቶ እንዲጎበኙ ጥረት ተደርጓል።

**አዲስ ዘመን፦ የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ከደረሰበት ጉዳት እንዲያገግም ወይም እንዲነቃቃ የተሠሩት ሥራዎችን ለአብነት ቢጠቀሱ።**

**አቶ ስለሺ፦** ዘርፉን ለማነቃቃት ከተሠሩት ሰፊ ሥራዎች አንዱ ጉዳት የደረሰባቸውን አካባቢዎች ቶሎ ወደ ሥራ እንዲገቡ ማድረግ ነው። ለአብነትም ኮቪድ ተከስቶ በነበረ ጊዜ በዘርፉ ውስጥ ላሉ የንግድ ተቋማት በገንዘብ ሚኒስቴርና በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ በተመቻቸ በጀት ከሶስት ቢሊዮን ብር በላይ በአነስተኛ ብድር በመያዣ ድጋፍ እንዲያገኙ ተደርጓል። ተቋማቱ ሠራተኞቻቸውን ከሥራ እንዳያስወጡ፣ የሚሰጡት አገልግሎትም እንዳይቋረጥና የቱሪዝም ንግድ እንቅስቃሴውም እንዲኖር ታስቦ የተደረገ ድጋፍ ነው።

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ አጋር ድርጅቶችን በማስተባበርም፤ አገልግሎት ወደ ማቋረጥ ደረጃ ደርሰው ለነበሩ ተከታታይ ዘርፉን ሊያነቃቃና ወደ ሥራቸው ለመመለስ የሚያስችላቸው የተግባቦትና የሙያ ክህሎት የሚያስጨብጥ ሥልጠና በጎንደርና ላልይበላ፣ በቅርቡ ደግሞ በትግራይ ክልል ሰጥቷል።

ሶስተኛ በሚኒስቴሩ የተደረገው ጥረት ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ኤምባሲ አምባሳደሮች፣ በተለይም ለሀገራችን የቱሪዝም ኢንዱስትሪ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያላቸው ላይ ትኩረት በማድረግ የጉብኝት መርሃግብር በማዘጋጀት ወደ ተለያዩ የቱሪስት መዳረሻዎች በመውሰድ፣ በክብረበዓላት ጊዜም እንዲታደሙ በማድረግ በቱሪስት መዳረሻዎች ያለውን የፀጥታ ሁኔታ፣ ዘርፉም የሚገኝበትን ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለዚህም የጉዞ ክልከላ እንዲያነሱና በነርሱ በኩል ሊደረግ የሚችለውን ትብብር እንዲያደርጉ ሰፊ ሥራ ተሰርቷል።

ከመረጃ ጋር በተያያዘም በተለያዩ አካባቢዎች የቱሪስት መረጃ እንዲኖር የግንባታ ሥራዎችም ተከናውነዋል። ግንባታው የተከናወነው አዲስ አበባ ከተማን ጨምሮ በአየር መንገድና በሌሎችም ነው።በተጓዳኝም መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ የጥሪ ማዕከላት ተቋቁመዋል። በኮቪድ ጊዜ የነበሩ የንክኪና አስፈላጊ የጥንቃቄ ተግባራት እንዲከበሩ የማድረግ ሥራም ተሰርቷል።

ጦርነቱ በቅርሶችና በተለያዩ የዘርፉ እንቅስቃሴዎች ላይ የደረሰውን ጉዳትም በአማራ፣ በትግራይና በአፋር ክልች በጥናት ለመለየት ጥረት ተደርጓል። ጥናቱ በመሠረተ ልማት፣ በቅርሶች፣ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ የደረሰውን ጉዳት መሠረት ያደረገ ሲሆን፣ አጠቃላይ የደረሰውን ጉዳት በቁጥር ይህን ያህል ነው ብሎ ማስቀመጥ ባይቻልም ከፍተኛ እንደሆነ ግን መለየት ተችሏል። በተለይ ግን በትግራይ ክልል የደረሰው ጉዳት 70 በመቶ በሚባል ደረጃ ነው። ጥናቱን መሠረት በማድረግም ከክልሎቹ ጋር ውይይት አድርገናል። በቅርቡ የመጨረሻውን ውይይት ያደርግነው ከትግራይ ክልል ጋር ነው። በውይይቱ የዘርፉ ሥራ ኃላፊዎች፣ የግሉ ዘርፍ እንዲሁም ባለድርሻ አካላት ተሳትፈዋል። በእኔ እምነት መንግሥት በሚችለው ሁሉ ጥረት አድርጓል። መሠረታዊ የሆኑ ሥራዎችም ተሠርተዋል።

በዘርፉ ላይ የሚገኙትም ተስፋ ሳይቆርጡ ተንቀሳቅሰዋል። በአሁኑ ጊዜም ትግራይ ክልል በአክሱምና ሽሬ ለማስጎብኘት እንግዶች መቀበል ተጀምሯል። በመቀሌ በኩል አፋርንም መጎብኘት ተጀምሯል።ይሄ ትልቅ መነቃቃት ነው። በአማራ ክልልም በተመሳሳይ በኮቪድና በጦርነቱ ሙሉ ለሙ በሚባል ደረጃ የዘርፉ እንቅስቃሴ ቆሞ ነበር።

በሌሎቹ የኢትዮጵያ ክፍሎች ኮንሶና ሐረር አካባቢዎች እንዲሁም አዲስ አበባ ከተማ እንቅስቃሴዎች ነበሩ። በቱሪዝም ዘርፉ ከኮንፈረንስ ጋር የተያያዘው MICE Tourism (Meeting incentives conference and exhibition) የሚባለው ኮቪድና ጦርነት ስጋቶች ባልነበሩበት ወቅት ከነበረው በላይ ከፍተኛ ለውጥ አምጥቷል።

በውስን የስብሰባ ማዕከላት ውስጥ ተገድቦ የነበረው ዓለምአቀፍ ኮንፈረንሶች በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ሆቴሎች ውስጥም እየተስተናገደ ይገኛል። በአንድ ሆቴል ውስጥ እስከ ሁለት ኮንፈረንሶች የሚካሄዱበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው። የማይስ ቱሪዝም ተአምራዊ እድገት እያመጣ ነው ብዬ አምናለሁ።

ትልቁ ስጋት አዲስ አበባ ከተማ ላይ ባለው ምቹ ሁኔታ እንዳይገደብ ነው። ለማይንስ ቱሪዝም ባህርዳር፣ሐዋሳ፣ አዳማ፣ ወደፊት ደግሞ መቀሌ በሁለተኛ አማራጭ ተይዘዋል። ትልልቅ የስብሰባ ማዕከሎች እንዲሠሩ በማድረግ ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭም ማይንስ ቱሪዝም እንዲካሄድ መሥራት ይኖርብናል።

ሌላው ትኩረት ሰጥተን የሠራነው የሀገር ውስጥ ቱሪዝም ላይ ነው። ባለፉት ጊዜያት ዓለማዊም መንፈሳዊም ይዘቶች ያሏቸው በርካታ ኩነቶች ነበሩ። ብዛት ያለው የሀገር ውስጥ ነዋሪ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቅሷል። ተማሪዎች ጉብኝት የማድረክ ተሞክሮ የዳበረበት፣ ሀገርህን እወቅ ክበባትን በማቋቋም ሰዎች ከቦታ ቦታ እንዲንቀሳቀሱ ጥረት ተደርጓል።

በሀገር ውስጥ የቱሪዝም እንቅስቃሴ የአልባሳትና የጌጣጌጥ ግዥዎች በማካሄድ በግብይት ውስጥ የነበረውም ጥሩ የሚባል ነበር። የሀገር ውስጥ ቱሪዝም እንቅስቃሴው ከሌላው ዓለም ቱሪስት ለመሳብ ትልቅ ኃይል ሆኖ አገልግሎናል። በዚህ ረገድም መገናኛ ብዙሃን ዘርፉን በማነቃቃት ሚና ተጫውተዋል።በአጠቃላይ በዘርፉ ባለፈው ዓመት ጥሩ እንቅስቃሴ የነበረው ነው ማለት ይቻላል።

**አዲስ ዘመን፦ የመልሶ ማልማት ሥራ የሚፈልግ አለ? ካለ የሚሠራውንም ሥራ አብረው ይግለጹልን።**

**አቶ ስለሺ፦** መልሶ ማልማት በመንግሥትም በእቅድ ተይዟል። ቀደም ሲል የነበረን ሃሳብ የነበረንን አገልግሎት ማሳደግ ነው። ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ በጦርነቱ በቅርሶች፣አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ፣ የአየር ማረፊያዎችን ጨምሮ ጉዳት ደርሷል። ጉዳቱ በጥናት ተለይቶ ለመንግሥት ቀርቧል። መልሶ ማልማት ወይንም ማቋቋም ሥራ እንደሚያስፈልጋቸው ለውሳኔ ለመንግሥት የቀረበው ነው። የአየር ማረፊያዎችን መልሶ ማልማት የማይቀር ጉዳይ ነው።

የተጎዱ ቅርሶችን መጠገን ላይ በተመሳሳይ ሥራዎች ያስፈልጋሉ። የደሴ ሙዚየምን ከቅርስ ባላደራ ማህበር ጋር በመሆን ሙዚየሙን ወደነበረበት ለመመለስ ጥረት እየተደረገ ነው። በትግራይም በተመሳሳይ ጥገናዎች እንዲደረጉ እየተሠራ ነው። በአጠቃላይ ልማት የሚፈልጉት ላይ በአስቸኳይ እንቅስቃሴ እንዲደረግ አቅጣጫ ተቀምጦ እየተሠራ ነው።

የግሉ ዘርፍም በአቅሙ ሊሠራ የሚችለውን እንዲሠራ፣ ከቀረጥ ነጻ እድል ተሰጥቷቸው እቃዎችን ከውጭ እንዲያስመጡ፣ ከባንክ አዲስ ብድር እንዲያገኙና ቀደም ሲል የነበረባቸው ብድር እንዲራዘምላቸው በማመቻቸት በርብርብ ተሠርቷል። በዚህ ረገድም ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ከባንክና ከገንዘብ ሚኒስቴር ጋር በቅርበት እየሠራ ይገኛል። ሙሉ ለሙሉ ውድመት ለደረሰበት መፍትሄ ላይኖረን ይችል ይሆናል እንጂ ለአብዛኞቹ በተቻለ መጠን ድጋፍ እያደረግን እንገኛለን።

ቱሪስቶች በምንፈልገው ቁጥር ልክ መጥተው አገልግሎት ሰጪዎች ተከታታይ ገቢ እስካላገኙ ድረስ ከዘርፉ ይገኝ የነበረው ገቢ የሚጠበቀውን ያህል ላይሆን

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

# ወቅታዊ

## ‹‹የቱሪዝም ሥራ በመልካም ሥም...

ከገጽ 7 የዞረ



ይችላል። ይህን ታሳቢ በማድረግ በተለያዩ ዓለምአቀፍ መድረኮች ላይ እንደ ሀገር እየተሳተፍን ነው።

ጀርመን፣ ስፔንና በተለያዩ ላቲን አሜሪካን እንዲሁም በአፍሪካ በሚካሄዱ ትላልቅ መድረኮች ላይ መንግሥትም የግሉ ዘርፍም በጋራ በመሳተፍ ላይ እንገኛለን። ይሄ ትኩረትና እንቅስቃሴ የሀገር ገጽታንም ይገነባል። ቱሪስቶችንም ለመሳብ ያግዛል። በዚህ መልኩ ውጤት ማግኘት ከተቻለ በዘርፉ ላይ የሚገኘውን ገቢ ለማግኘትና ሠራተኞቹንም ለማስተዳደር ያስችለዋል። ተጨማሪ የማስፋፋትና በዘርፉ ኢንቨስትመንት የመሳብ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ።

የመጨረሻውና ዋናው መፍትሄ የሚሆነው ዘርፉ አሁንም ማመንጨት የሚችለውን ኢኮኖሚና ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታ ማስጠበቅ ነው። ይህ እስካልሆነ ድረስ በመንግሥት ድጎማና ድጋፍ ብቻ የቱሪዝም ዘርፍ ሊነቃቃ አይችልም። የቱሪዝም ዘርፍ መንግሥት የሚመራው ግን የግሉ ዘርፍ የሚያሽከረክረው ነው። በዋናነት የቱሪዝም እንቅስቃሴውን ሞተር ሆኖ የሚያገለግለው የግሉ ዘርፍ ነው። ከመንግሥት የሚያስፈልጉ የተለያዩ ድጋፎች ግን እንደተጠበቀ ነው። አዳዲስ የሕግና መመሪያ ማሻሻያዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም መንግሥት ከግሉ ዘርፍ ጋር ሆኖ ይሠራል።

በዘርፉ ላይ ክልሎችም ኃላፊነት ወስደው መሥራት ይኖርባቸዋል። ሁሉ ነገር ፌዴራል ላይ ብቻ የሚመጣ ከሆነ በዘርፉ ላይ የሚፈለገው ለውጥ ላይመጣ ይችላል። ዋና ዋና የሚባሉ የቱሪስት መዳረሻዎች በክልሎችና በከተማ አስተዳደር እጅ ናቸው። ለምሳሌ ከቅርስና ከብሄራዊ ፓርኮች ጥበቃ ጋር ተያይዘው ያሉ ሥራዎች ማህበረሰቡን በማንቀሳቀስ ለውጥ ማምጣት የሚቻልበት እድል አለ። ብዙ የገንዘብ ወጪ ሳያስፈልግ የሰው ሀብትን በማስተባበር ለውጥ ማምጣት ይቻላል። በአካባቢው የሚገኙትን ዩኒቨርሲቲዎችን አቅም ለሥልጠና፣ ለጥናትና ምርምር በመጠቀም ዘርፉን ማሳደግ ስለሚቻል መረባረቡ የተሻለ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

**አዲስ ዘመን፡- በዚህ ወቅት በኢንዱስትሪው ዘርፍ እንደስጋትና መልካም ጎን የሚጠቀሱ ምንድን ናቸው?**

**አቶ ስለሺ፡-** በዘርፉ እንደመልካም የምወስዳቸው መንግሥት ቱሪዝም እንዲያድግ በቁርጠኝነት እየሠራ መሆኑ በመልካም ይወሰዳል። በተለይ ከመዳረሻ ልማት አንጻር በተለያዩ የመዳረሻ ቦታዎች ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ ሀብት በማሰባሰብ ረገድ እየተሠራ ያለው ሥራ አበረታችና የሚመሰገን ነው።

ከዚህ ቀደም ቱሪዝም ላይ የአደረጃጀት ክፍተቶች ይስተዋሉ ነበር። አሁን ላይ አንድ ጠንካራ የሆነ የቱሪዝም ሚኒስቴር አለ። ስለዚህ በዚህ ጠንካራ ሚኒስቴር መሪነት ጠንካራ የሆነ አንድ ወጥ ሀገራዊ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ይፈጥራል ብዬ አምናለሁ። ሌላው የፖሊሲ የሕግ ማሻሻያዎች ተደርገዋል። ለምሳሌ የአዋጅ ማሻሻያ ተደርጓል። በዚህ አዋጅም የቱሪዝም ፈንድ እንድናቋቁም ተፈቅዷል። ይህ የቱሪዝም ፈንድ ከቱሪዝም አንጻር፤ በተለያዩ የዓለም ገበያዎች በመሄድ ቱሪዝሙን እንዳናስተዋውቅ ወደ ኋላ ያስቀረን የነበረው የሀብት ማነስ ነው።

አሁን ይህን ሀብት ከቱሪስት ታክስ በመሰብሰብ፣ በኢንዱስትሪው ላይ ካሉ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ከሚያገኙት ገቢ የተወሰነ አበርክቶ እንዲያደርጉ ማድረግ ስጦታዎችን መቀበል፣ በዘርፉ የሚመጡ እድሎችን ተወዳድሮ የማሸነፍ አቅም መፍጠር፣ እነዚህን ሰብስቦ ቱሪዝም ፈንድ አቋቁሞ ለምንፈልገው ቱሪዝም መዳረሻ ልማት፣ ዘርፉን ለማስተዋወቅና ለአቅም ግንባታ መጠቀም የምንችልበት ዕድል አለ።የአዋጅ ማሻሻያው፣ የተቋሙ ምሥረታ፣ና የመንግሥት ቁርጠኝነት ለቱሪዝም ዘርፉ ከፍተኛ ፋይዳ ያላቸው ናቸው።

ሌላው የግሉ ዘርፍ የቱሪዝም ኢንዱስትሪውን ከችግር ፈጥኖ መውጣት (Resilient) የተረዳ ነው። ይህ ማለት በኮቪድም ሆነ በጦርነት በማንኛውም ፈተና አልፎ የቱሪዝም ዘርፉ መኖር እንደሚችል፣ ቱሪስቶችም መምጣት እንደሚችሉ ትምህርት የወሰድንበት ነው። የዘርፉ ከችግር መውጣት ባህሪ ከምንም በላይ በሆነ ነገር ጠፍቶ የሚቀር እንዳልሆነ ነው።

እንደ ቻይና እና አፍሪካ ያሉ አዳዲስ ገበያዎች ትኩረት ያደርግንባቸው መዳረሻዎች አሉ። እነዚህ ለዘርፉ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል። የሀገር ውስጥ የቱሪዝም እንቅስቃሴ፣ ማይስ ቱሪዝም፣ እነዚህ አዳዲስ ትኩረት ያደረግንባቸው፣ የአፍሪካና የኤሺያ ገበያ፣ የሀገር ውስጥ ገበያ፣ ከምርት አንጻር ደግሞ እንደ ማይስ ቱሪዝም ትልቅ እንቅስቃሴ ለመፍጠር ተስፋ ሰጪ እድል መኖሩን ያሳያል።

ከስጋት አንፃር ለተነሳው፤ ትልቅ ችግር ይሆናል ብዬ የማምነው ዓለምአቀፍ ሁኔታው በምንፈለገው ልክ እንዳንቀሳቀስ ሊያደርገን ይችላል። የኢኮኖሚ ጉዳይ የኢትዮጵያ ብቻ አይደለም። የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት አለ። ዓለምአቀፍ ገበያው በዚህ ሁኔታ የሚቀጥል ከሆነ ሰዎች ከቦታ ቦታ ላይንቀሳቀሱ ይችላሉ።ወይም ደግሞ የሚኖራቸው የጊዜ ቆይታ ሊቀንስ ይችላል። በዚህ ምክንያት የምንፈልገውን ያህል ተጠቃሚነት ላይኖር ይችላል።

ሌላው ሰላምና ፀጥታ ከሌለ የቱሪዝም ጉዳይ አይታሰብም። ቱሪስቶች ጊዜ ገድበው አይመጡም። የቱሪዝም ባህሉ ተቀይሯል። አንድ ቱሪስት ወደ አንድ አካባቢ ከሄደ መመለስ የሚፈልገው በአጭር ጊዜ ሁለትና ሶስት ሀገሮችን ጎብኝቶ ነው። የሚጎበኘው ቀጣናውን ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ ቀጣናው ሰላም መሆን ይኖርበታል። ሱዳን ላይ ያለው ችግር በኢትዮጵያ የቱሪዝም እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንደማያመጣ ተደርጎ ሊታሰብ ይችላል።

ነገር ግን ከውስጣዊ ችግር ባላነሰ በዙሪያው ወይም በቀጣናው ባለው ችግር የተነሳ ቱሪስቶች ሰላማዊ በረራ አይኖርምና በሰላምም ጎብኝተን አንመጣም የሚል ስጋት ያድርባቸዋል። ለሰላም ቅድሚያ ስለሚሰጡ አማራጮችን ይፈልጋሉ።

**አዲስ ዘመን፡- የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ተፈጥሮአዊ የሆኑ ሀብቶችን በማስጎብኘት ሳይ የተመሠረተ እንደሆነ ይነገራል። ከእነዚህ ተጨማሪ ዘርፉ የሚፈስገው ወይም የሚጠይቀው ነገር አስ?**

**አቶ ስለሺ፡-** የቱሪዝም ሥራ በጣም ሰፊ ነው። የቱሪስት ሀብት ገና ተለይቶ አላበቃም። አጠቃላይ በኢትዮጵያ በቱሪዝም ሀብትነት ሊያዙ የሚገቡትን የመለየት ሥራ ይጠበቃል። ከዚህ በፊት ከሚታወቁት በተጨማሪ አዳዲስ መልማት ያለባቸው አሉ። ብዙዎች የማያውቋቸው የዱር እንስሳት፣ የተፈጥሮ ሀብት፣ባህልና ታሪክ ያሏቸው ቦታዎች አሉ። እነዚህን ሀብቶች ወይንም የቱሪዝም ፀጋዎች የመለየት ሥራ ጊዜ ይወስዳል። ከፍተኛ ወጭም ይጠይቃል። ሆኖም ግን ሥራዎች ተጀምረዋል። በዘርፉ ያለውን ሀብት ወይም የሀሴት ማፕ የማዘጋጀት ሥራ ተጀምሯል።

በሁለተኛ ደረጃ የቱሪዝም መሠረተ ልማት ሥራን ማጠናከር ነው። ለአብነትም የቡና መስመር ተብሎ በተለየው አካባቢ የለማ መሠረተ ልማት የለም። በመሆኑም ወደእነዚህ አካባቢዎች መሠረተ ልማቶችን ማልማት፣ መረጃ ማዕከሎችንና ማረፊያ ቦታዎች እንዲሟሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው።

ሶስተኛው ለዘርፉ የሚያስፈልገው መረጃ መስጠትና ዘርፉን በማስተዋወቅ የገጽታ ግንባታ ሥራ ነው።አራተኛው በጣም ወሳኝ የሚሆነው፤ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን አቅም በመገንባት የአገልግሎት ጥራት ማስጠበቅ ነው። በዚህ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ውስጥ ሆቴሎች ይጠቀሳሉ። የአገልግሎት ጥራትን ማላቅ ወሳኝ በመሆኑ ሆቴሎቹ በሚኖራቸው ንጽህናና ሌሎችም ማሟላት የሚጠበቅባቸውን መስፈርቶች ካሟሉ ከአንድ ኮከብ እስከ አምስት ኮከብ ደረጃ ያገኛሉ።

አምስተኛው ተግባርና መሠረታዊ ጉዳይ አገልግሎት የሚሰጡትን ሰዎችንም ተቋማቸውንም በእውቀት፣በክህሎት፣ በሥነምግባር፣ በአመለካከት አቅም መገንባት ነው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ ዘርፉ ለኢኮኖሚ፣ለማህበራዊ ትስስር ያለውን አተዋጽኦ፣ ዘርፉ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ሲወዳደር ያለው ልዩነትን መሠረት አድርጎ በጥናትና ምርምር ማሳየት የሚሉ ሥራዎች ተካትተዋል።

የዘርፉን አጠቃላይ እድገት ጥናት ማድረግ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞችን ያስገኛል። ምን ያህል ጎብኒዎች መጡ? የት ጎበኙ? ምን ያህል ገቢ ተገኘ? ዘርፉ ለኢኮኖሚው ያበረከተው አስተዋጽኦና ችግሮች ካሉም ለይቶ እንዴት መፍታት ይቻላል የሚለውን ሁሉ ለይቶ ለማወቅ ያስችላል።

ይህን ታሳቢ በማድረግ ደግሞ ከባለድርሻ አካላት ጋር ከክልሎች፣ ከግሉ ዘርፍ፣ ከሲቪል ማህበረሰቡ፣ከዲፕሎማቲክ ኮሙኒቲው ጋር የቱሪዝም ዘርፉን ለመደገፍ የሚደረገው እንቅስቃሴ የበለጠ ያጠናክረዋል።በቱሪዝም ሚኒስቴር በኩል የሚሠሩ በርካታ ሥራዎች አሉ። መረጃ መስጠት፣ ባህል፣ ቅርስና የዱር እንስሳ መጠበቅ የኛ ሥራ ነው።

የግሉን ዘርፍ ወደ ኢንዱስትሪው ማምጣት፣ በተለያዩ የቱሪዝም መዳረሻዎች የማህበረሰብ ኢንተርፕራይዞች ተመሥርተው የአካባቢ ሎጅ ኖሯቸው፣ በአስጎብኝነትና መሰል ሥራዎች ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ሰፊ ሥራ ይጠይቃል። እንዲህ ያለው ተግባር ደግሞ የክልሎችን ትብብር ይጠይቃል።

የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ዋና ተልእኮ ፖሊሲ፣ ስትራቴጅዎችንና የሕግ ማእቀፎችን መቅረጽ፣ እንዲሁም እነዚህ ማስተዋወቅና መተግበራቸውን ማረጋገጥ ቢሆንም ከላይ የጠቀስኳቸውን ተልእኮዎችንም ይወጣል።

**አዲስ ዘመን፡- ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አዲስ አበባ ከተማን ጨምሮ በተለያዩ አካባቢዎች ፓርኮችን ጨምሮ ለቱሪዝም መዳረሻ የሚሆኑ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። ትኩረቱ ወደ አዳዲሶቹ እንዳይሆን ነባር ከሚባሉ የቱሪዝም መዳረሻዎች ጋር ተጣጥመው እንዲሄዱ ምን እየተሠራ ነው?**

**አቶ ስለሺ፡-** ነባር የቱሪስት መዳረሻ የምንላቸው ለኢትዮጵያ የቱሪዝም እንቅስቃሴ መለያ (አይከን) ናቸው። ነባር ከሚባሉት፣ ላልይበላ፣ አክሱም፣ ጎንደር፣ ደቡብ ኦሞ፣ ጅንካ፣ አፋር ፣ ዶርዜ፣ አዲስ አበባ ከተማ ላይም ለቱሪስት መዳረሻ የሚሆኑ የተወሰኑ ሙዝየሞችና አብያተክርስቲያናት ይጠቀሳሉ። አሁንም ወደፊትም ለኢትዮጵያ ቱሪዝም መሠረት ሆነው የሚቀጥሉ ናቸው። ያላቸው ታሪክ፣ መስህብ እንዲመሩ ያደርጋቸዋል።

አሁን ላይ የተሰሩና በመሠራት ላይ ያሉት የቱሪዝም መዳረሻዎች ቀደም ሲል የተሠሩትን ነባሮች ብለን እንደምንጠራቸው ሁሉ የአሁኖቹን ደግሞ የዚህ ዘመን ቅርሶች አድርገን እንወስዳቸዋለን። እንደ ቀድሞዎቹ ሁሉ ለቱሪዝም ገበያ በማዋል እንጠቀምባቸዋለን።

ለምሳሌ ጎርጎራ ሐይቅ ላይ እየተሠራ ያለው ሥራ መሠረተ ልማት እና ሌሎችንም ሥራዎች በማሟላትና ከመስህብነት ወደ መዳረሻ የማሳደግ ሥራ ነው። ቱሪስት መሳብ የሚቻለው እንዲህ ያሉ ሥራዎችን በመሥራት ነው ። ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ የመስህብ ሥፍራ ያላቸው አካባቢዎች አሉ።

ለቱሪስት መስህብ የሆኑ ምንም አይነት መሠረተ ልማት የሌላቸው በሁሉም የሀገሪቱ አካባቢዎች አሉ።ለአብነትም ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የደን ሀብት፣ ሰሜን ኢትዮጵያ አልጣሽ አካባቢ ከሱዳን ጋር የሚያገናኝ ትልቅ ብሄራዊ ፓርክን መጥቀስ ይቻላል። ከዚህ አንጻር አዳዲስ ልማቶች መኖራቸው ተወዳዳሪነትን ይጨምራል። እንደውም የሚያስፈልገው የጉዞ ትስስር በመፍጠር ተጠቃሚነትን ማሳደግ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- በ10 ዓመቱ መሪ እቅድ ውስጥ ከተካተቱት ዘርፎች አንዱ ቱሪዝም ኢንዱስትሪው ነው።በእቅዱ መሠረት የተከናወነው ሥራ እንዴት ይገለጻል?**

**አቶ ስለሺ፡-** ከአስር ዓመት መሪ እቅድ ሶስት አመት ተጠናቅቋል። በዚህ ጊዜ ውስጥ ከፀጥታና ከፍተኛ ገንዘብ ከሚፈልጉ ሥራዎች ጋር በተያያዘ ያልተሳኩ ቢኖሩም ከመዳረሻ ልማት፣ ከአቅም ግንባታ፣የአግልግሎት ሰጪ ተቋማትን ጥራት ከማረጋገጥ፣ ከቅርስና ፓርክ ጥበቃ ሥራዎች አኳያ እንዲሁም ኢትዮጵያ ከዓለም እይታ ውጭ እንዳትሆን ችግሮችን ተቋቁሞ በመንቀሳቀስ ጥሩ አፈጻጸም ተመዝግቧል።በቀሪው ዓመታት የበለጠ በመንቀሳቀስ እቅዱን ለማሳካት ርብርብ ይደረጋል።

**አዲስ ዘመን፡- የዓለም ቱሪዝም ቀንን አስመልከቶ ስላለው ዝግጅት ቢገልጹልን**

**አቶ ስለሺ፡-** አዲስ ዓመትን ተከትሎ የሚመጡት የመስቀልና እሬቻ በዓላት አሉ። በአጠቃላይ መስከረም ወር የቱሪዝም ወር ነው። የቱሪዝም ኢንዱስትሪው ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ይነቃቃል። ከውጭ ብቻ ሳይሆን የሀገር ውስጥ ቱሪስት ፍሰቱ የሚጨምርበት ጊዜ ነው። መልክአምድሩ ሁሉ የሚደምቅበት ጊዜ በመሆኑ መስህብነቱ ይጨምራል። ታህሳስና ጥር ደግሞ የውጭ ቱሪስቶች በስፋት ወደ ሀገራችን የሚመጡበት ወራት በመሆናቸው ዛሬ መስከረም 17 የሚከበረው የዓለም ቱሪዝም ቀን ትልቅ መነቃቃትን ይፈጥራል።

የዓለም ቱሪዝም ቀን በየዓመቱ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ማክበር ነው የተለመደው። ዘንድሮም ዝግጅት የተደረገው በደቡብ ምእራብ ክልል ለማክበር ነው። ክልሉ ባህላዊ፣ታሪካዊና የተፈጥሮ መስህብ ሀብቶች ያሉት በመሆኑ ጥሩ በዓል እንደሚሆን ይጠበቃል። ክልሉም አጋጣሚውን ተጠቅሞ ያለውን ፀጋ ያስተዋውቃል።

**አዲስ ዘመን፡- በዘርፉ ስተሰማራውና ስማህበረሰቡ መልእክት ካስዎት።**

**አቶ ስለሺ፡-** ቱሪዝም በአንድ ተቋም ብቻ የሚሠራ አይደለም። ሥራው ሰፊ ነው። የቱሪዝም ሥራ በመልካም ሥም ላይ የተመሠረተ ሥራ ነው። መልካም ሥም የሚመጣው ደግሞ በሚሠሩ የገጽታ ግንባታ ሥራዎችና በሚሰጡ መረጃዎች ላይ ይመሰረታል። ሁሉም ሰው ባገኘው አጋጣሚ አካባቢውን በማስተዋወቅ፣ መረጃ በመስጠት፣ በገጽታ ግንባታ ላይም በመሥራት፣ የኢትዮጵያ መገለጫ በሆኑ የእንግዳ አቀባበል እንግዶችን ለማስተናገድ ዝግጁ መሆን ያስፈልጋል። በዘርፉ ላይ ያለውም ሆነ እያንዳንዱ ዜጋ ለሀገሩ አምባሳደር ሆኖ ዘርፉን በማገዝ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ጥሪ አስተላልፋለሁ።

**አዲስዘመን፡- አመሰግናስሁ።**

**አቶ ስለሺ፡-** እኔም አመሰግናለሁ።

ኢኮኖሚ

# ኢንቨስትመንት

## ስኬታማውና ለተሻለ ውጤት የሚተጋው የድሬዳዋ ኢንቨስትመንት

አንተነህ ቸሬ

በኢንዱስትሪ መነኸሪያነታቸው ከሚታወቁት የኢትዮጵያ ከተሞች መካከል አንዷ የሆነችው ‹‹የበረሃዋ ገነት›› ድሬዳዋ፣ የነዋሪዎቿ እንግዳ ተቀባይነትና አስደናቂ ኅብር ለኢንቨስትመንት ሥራ ምቹና ተመራጭ ያደርጋታል።ድሬዳዋ በማምረቻ ዘርፍ (Manufacturing Sector) የተሻለ የኢንቨስትመንት አቅምና ምቹ ሁኔታ አላት።የኢትዮ-ጅቡቲ የባቡር መስመርን ተከትላ የተቆረቆረችውና ‹‹የኢንዱስትሪ ኮሪደር›› በመባል የምትታወቀው ድሬዳዋ፣ በንግድ ማሳለጫነቷ ተጠቃሽ ከተማ የነበረች ቢሆንም፣ ይህ የንግድ መነኸሪያነቷ ተቀዛቅዞ ቆይቷል።

የድሬዳዋ የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፣ ከተማዋ ቀደም ሲል ወደምትታወቅበት የንግድ መነኸሪያነቷ ለመመለስ ጥረት እያደረገች ትገኛለች።የዚህ ጥረቷ ማሳያ ከሆኑ ተግባራት መካከል አንዱ ደግሞ በኢንቨስትመንት ዘርፍ እያደረገችው ያለው እንቅስቃሴ ነው።ይህ እንቅስቃሴዋም ሰምሮላት ውጤት እያገኘችበት ነው።የከተማዋን የኢንቨስትመንት ዘርፍ ችግሮችን በመፍታት የኢንቨስትመንት ፍሰትን ለመጨመር ዘርፉ በቦርድ እንዲመራ ተደርጓል።ይህም ሁሉም የኢንቨስትመንት ዘርፍ ጉዳዮች በቦርዱ እየታዩ የዘርፉ ችግሮችም ሆኑ የባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች ፈጣንና የተደራጀ ምላሽ እንዲያገኙ ለማድረግ ታስቦ የተወሰደ ርምጃ ነው።

በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር የንግድ፣ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ የኢንቨስትመንት ጥናትና ፕሮሞሽን ቡድን መሪ አቶ አበራ መንግሥቱ፣ በድሬዳዋ ከተማ ያለው የኢንቨስትመንት ዘርፍ እንቅስቃሴ አበረታች ለውጦች እየተመዘገቡበት እንደሚገኝ ያስረዳሉ።ከተማዋ ባለፈው የበጀት ዓመት በኢንቨስትመንት ዘርፍ ጥሩ አፈፃፀም አሳይታለች።አቶ አበራ እንደሚሉት፣ በ2015 የበጀት ዓመት በዘርፉ እንዲከናወኑ ታቅደው ከነበሩ ተግባራት መካከል አንዱ ለአዳዲስ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት ነበር።በዚህም መሠረት በ2015 የበጀት ዓመት ለ450 የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ መስጠት ታቅዶ፣ 347 ባለሀብቶች (በአገልግሎት 206፣ በማምረቻ 104፣ በኮንስትራክሽን 22፣ በግብርና 15) ፈቃድ ወስደዋል።ባለሀብቶቹ ያስመዘገቡት የካፒታል መጠን ከ34 ቢሊዮን ብር በላይ ሲሆን፣ ፕሮጀክቶቹ ከ21ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የሥራ እድሎችን የመፍጠር አቅም አላቸው፡፡

የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰዱት ባለሀብቶች መካከል ለሦስት ሺ952 ዜጎች የሥራ እድሎችን መፍጠር የቻሉ ስምንት ፋብሪካዎች እና አራት የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ፕሮጀክቶች ሥራ ጀምረዋል።ይህም ከበጀት ዓመቱ የዘርፉ ስኬቶች መካከል በግንባር ቀደምነት የሚጠቀስ አፈፃፀም ነው።ባለሀብቶች ወደ ከተማ አስተዳደሩ እስከሚመጡ በመጠበቅ ሳይሆን ወደ ባለሀብቶች በመሄድ ሥራዎቻቸውን ለመመልከትና ለችግሮቻቸው መፍትሄ ለመስጠት ያስቻሉ ተግባራትም ተከናውነዋል፡፡

የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ካሏቸው ፋይዳዎች መካከል አንዱ ፕሮጀክቶቹ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ በሚከናወኑባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የማኅበረሰብ ክፍሎችን ተጠቃሚ ማድረጋቸው ነው።የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርም ባለሀብቶችን ወደ ከተማዋ ሲያስገባ ባለሀብቶች በተለያዩ መንገዶች የአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ እንዲያደርጉ በማሰብ ነው።ማኅበረሰቡ ከኢንቨስትመንት ሥራዎች በሥራ እድል ፈጠራ፣ በምርትና አገልግሎት አቅርቦት፣ በቴክኖሎጂ ሽግግርና በገበያ እድል ተጠቃሚ እንዲሆን ይጠበቃል።በዚህ ረገድ በከተማዋ የሚከናወኑ የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ለከተማዋና አካባቢው ህብረተሰብ ዘርፈ ብዙ ፋይዳዎች እንዳሏቸው አቶ አበራ ይገልፃሉ።

‹‹በከተማዋ የሚገኙ ባለሀብቶች በሚያከናውኗቸው የኢንቨስትመንት ተግባራት አማካኝነት የሥራ እድል ከመፍጠር በተጨማሪ፣ ልዩ ልዩ ድጋፎችን በማድረግ ማኅበራዊ ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ይገኛሉ።ለተማሪዎች የትምህርት ቁሳቁሶች ድጋፍ የማድረግና አቅመ ደካሞችን የማገዝ ተግባራት የዚህ ማሳያ ናቸው።የአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ የሚያደርጉ የልማት ሥራዎችንም ይሠራሉ።ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ሥራዎቻቸውን በሚሠሩባቸው አካባቢዎች የመሠረተ ልማት ዝርጋታ ተግባራትን ስለሚያከናውኑ የአካባቢው ኅብረተሰብ በዚህ ተግባር በኩል ተጠቃሚ ይሆናል።ይህ የማኅበረሰቡ ተጠቃሚነት ማኅበረሰቡ ለኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች አዎንታዊ አመለካከት እንዲኖረው አድርጓል›› ይላሉ።

ባለፈው የበጀት ዓመት ድሬዳዋ በኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ መልካም አፈፃፀም ማስመዝገቧ ባይካድም በዚህ አፈፃፀሟ ላይ መሰናክል የሚፈጥሩ ተግዳሮቶች እንደነበሩ አቶ አበራ ይገልፃሉ።የኢንቨስትመንት ፈቃድና መሬት ወስደው በገቡት ውል መሠረት ሥራቸውን ማከናወን ያልቻሉ ባለሀብቶች ለሚያቀርቧቸው ጥያቄዎች ፈጣን ምላሾችን በመስጠት እና ርምጃዎችን በመውሰድ ረገድ የነበሩ የአፈፃፀም ክፍተቶች ከችግሮቹ መካከል ተጠቃሽ ናቸው።

ሀገራት የወጪና ገቢ ንግዳቸውን ለማቀላጠፍና የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ፍሰታቸውን ለማሳደግ ብሎም አጠቃላይ ምጣኔ ሀብታዊ እድገታቸውን ለማሻሻል ከሚተገብሯቸው አሠራሮች መካከል አንዱ ነፃ የንግድ ቀጣናዎችን (Free Trade Zones) ማቋቋም ነው።ነፃ የንግድ ቀጣና ‹‹ልዩ የኢኮኖሚ ቀጣና›› (Special Economic Zones) የሚባሉት የንግድና ኢንቨስትመንት መከወኛ ሥፍራዎች አካል ሲሆን እሴት የሚጨምሩ የምርት፣ የሎጂስቲክስ፣ የፋይናንስ አቅርቦትና መሰል ተግባራትና አገልግሎቶች የሚከናወንበት ቦታ ነው።በዚህ ስፍራ ምርቶችን ከማምረት በተጨማሪ አስመጪና ላኪዎች ዕቃዎችን ወደ ሀገር ውስጥ በማምጣት በቀጣናው ውስጥ የሚያከማቹበት፣ የሚያቀነባብሩበት እንዲሁም መልሰው ለውጭ ገበያዎች የሚያቀርቡበት እንዲሁም ሒደቱን ለማሳለጥ ቀልጣፋ የሆነ የሎጂስቲክስ አገልግሎት የሚቀርብበትም ነው።የተቀናጁ የፋይናንስና የምክር አገልግሎቶችም ይሰጥበታል።

ይህን ታሳቢ በማድረግም የኢትዮጵያን የወጪና ገቢ ንግድ በማቀላጠፍና የኢንቨስትመንት ፍሰቱን በመጨመር ለሀገራዊ ምጣኔ ሀብት እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ተስፋ የተጣለበት የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና (Dire Dawa Free Trade Zone)፣ ነሐሴ 8 ቀን 2014 ዓ.ም በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተመርቆ ሥራ እንደጀመረ ይታወሳል።

አቶ አበራ እንደሚሉት፣ ድሬዳዋ በንግድና ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ የላቀ አፈፃፀም እንድታስመዘግብ ከሚያስችሏት መልካም እድሎችና ግብዓቶች መካከል አንዱና ዋናው የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣና ነው።በአሁኑ ወቅት በርካታ ባለሀብቶች በነፃ የንግድ ቀጣናው ለመሰማራት ፍላጎት እያሳዩ ነው።ከዚህ ቀደም ከነበረው የተሻለ የባለሀብቶች ፍሰት እየታየ ነው።ነፃ የንግድ ቀጣናው ወደ ከተማዋ የሚገባውን የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር ትልቅ አስተዋፅኦ እያበረከተ ይገኛል።

‹‹ከውጭ የሚገቡ ባለሀብቶች ቀዳሚ ፍላጎታቸው ወደ ነፃ የንግድ ቀጣናው ገብተው ለመሰማራት ነው።ባለፈው ዓመት በተካሄደው ‹‹ኢንቨስት ኢትዮጵያ›› የኢንቨስትመንት ፎረም ላይ የተሳተፉ 27 የውጭ ባለሀብቶች የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣናን ጎብኝተዋል።ነፃ የንግድ ቀጣናው የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር ትልቅ እገዛ ያደርጋል›› በማለት የንግድ ቀጣናው ለድሬዳዋ ኢንቨስትመንት ትልቅ አቅም እንደሚፈጥር ይናገራሉ።

ባለፈው የበጀት ዓመት ስኬታማ አፈፃፀም ያሳየው የድሬዳዋ ኢንቨስትመንት፣ በ2016 የበጀት ዓመትም የተሻለ ስኬት እንዲያስመዘግብ ታቅዶ እየተሠራ እንደሚገኝ አቶ አበራ ያስረዳሉ።በ2016 የበጀት ዓመት ለ500 ባለሀብቶች የኢንቨስትመንት ፈቃድ ለመስጠት ታቅዷል።ባለሀብቶቹ ከ42 ቢሊዮን ብር በላይ ካፒታል ያስመዘግባሉ ተብሎ ይጠበቃል።ከእነዚህ ባለሀብቶች መካከል 35 ፕሮጀክቶች ግንባታዎቻቸውን አጠናቅቀው ምርት ማምረት እንዲጀምሩ ለማድረግም እቅድ ተይዟል።የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ከከተማዋ የኢንቨስትመንት አቅምና ራዕይ አንፃር ብዙ ባለሀብቶች በማምረቻ ዘርፍ እንዲሰማሩ ፍላጎት አለው።ይሁን እንጂ ባለሀብቶቹ የእውቀት ደረጃቸው፣ የገንዘብ አቅማቸውና የሥራ ልምዳቸው ውጤታማ ሊያደርጓቸው በሚችሉት ዘርፎች የመሰማራት ምርጫቸው የተጠበቀ ይሆናል።የዳያስፖራ ማኅበረሰብ አባላት በድሬዳዋ የኢንቨስትመንት ዘርፎች ለመሰማራት ከፍተኛ ፍላጎት እያሳዩ ነው።

> **የኢንቨስትመንት ፈቃድ ከወሰዱት ባለሀብቶች መካከል ለሦስት ሺ952 ዜጎች የሥራ እድሎችን መፍጠር የቻሉ ስምንት ፋብሪካዎች እና አራት የሆቴልና ቱሪዝም ዘርፍ ፕሮጀክቶች ሥራ ጀምረዋል። ይህም ከበጀት ዓመቱ የዘርፉ ስኬቶች መካከል በግንባር ቀደምነት የሚጠቀስ አፈፃፀም ነው**

ከሥራ እድል ፈጠራና ከአካባቢ ልማት በተጨማሪ፣ ኢንቨስትመንት ከሚፈለግባቸው ምክንያቶች አንዱ የቴክኖሎጂ ሽግግርን ለማሳደግ ነው።በዚህ ረገድ የድሬዳዋና አካባቢው ተወላጅ የዳያስፖራ ማኅበረሰብ አባላት ከተለያዩ የዓለም ክፍሎች ወደ ድሬዳዋ በመምጣት የቴክኖሎጂ ሥልጠናዎችን ሰጥተዋል።ይህ ተግባር በተያዘው የበጀት ዓመትም ተጠናክሮ ይቀጥላል።ባለሀብቶች ከውጭ በሚያመጧቸው ባለሙያዎች የሚያከናውኗቸውን ሥራዎች ኢትዮጵያውያን በአጭር ጊዜ የተግባር ልምምድ የውጭ ዜጎችን ተክተው እንዲሰሩና የቴክኖሎጂ ሽግግሩ እውን እንዲሆን በማድረግ ረገድ አበረታች ውጤቶች እየተመዘገቡ ይገኛሉ፤ በርካታ አምራቾች ይህን አሠራር ተከትለው የኢንቨስትመንት ሥራዎቻቸውን እያከናወኑም ይገኛሉ፡፡

የአገልግሎት አሰጣጥ ጥራትን ለማሻሻል በተደረጉ ጥረቶች አንዳንድ የኢንቨስትመንት ዘርፍ አገልግሎቶችን በኦንላይን (Online) መስጠት ተጀምሯል።የኢንቨስትመንት ፈቃድንም በኦንላይን ለመስጠት ጥረት ይደረጋል። እንደአቶ አበራ ገለፃ፣ ለባለሀብቶች የሚሰጠው የአንድ መስኮት አገልግሎት ባለሀብቶች ለፕሮጀክቶቻቸው አስፈላጊ የሆኑ የግብዓቶቻቸውን ጥያቄዎች በቀላሉ እንዲያቀርቡና በፍጥነት ምላሽ እንዲያገኙ የሚያስችል ነው።ይህ አሠራር ቀደም ሲል የሀብት (የጊዜና የገንዘብ) ብክነት ያስከትል የነበረውን የሥራ ሂደት የለወጠና ፈጣን አገልግሎት ለመስጠት ያስቻለ ነው፡፡

በመሠረተ ልማት አቅርቦት ረገድ ደግሞ ከተማዋ ከዚህ ቀደም የተሻለ የመሠረተ ልማት አቅርቦትን እውን በማድረግ የባለሀብቶችን ፍሰት ለመጨመር ጥረት ማድረጓን አቶ አበራ ያስታውሳሉ።202 ሄክታር ስፋት ያለው የድሬዳዋ ኢንዱስትሪ መንደር የራሱ የኃይል ማከፋፈያ አለው።ከከተማው የኃይል አቅርቦት ጋር የሚገናኝ ባለመሆኑ የኃይል መቆራረጥ ስጋት የለበትም።ባለሀብቶችም ለዚህ አበረታች የመሠረተ ልማት አቅርቦት ጥሩ እይታ እንዳላቸው ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል።የኢንዱስትሪ መንደሩ የኃይል ማከፋፈያ ጣቢያ ግንባታ ቀደም ሲል በተደጋጋሚ እየተቆራረጠ በኢንቨስትመንት ተቋማት ምርታማነት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሲያሳድር ለነበረው የኃይል አቅርቦት ችግር አስተማማኝ መፍትሄ የሰጠ የመሠረተ ልማት አቅርቦት ነው።በ2016 የበጀት ዓመት የአነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪ ልማትን ከሚመራው መሥሪያ ቤት ጋር በመተባበር የኢንዱስትሪ መንደሩን የውስጥ ለውስጥ መንገድ ደረጃውን ለማሻሻል ታቅዷል።

ባለሀብቶችን ለማበረታታት የሚተገበረው የአሠራር ሥርዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ የተዘጋጀ ሕጋዊ ማዕቀፍ እንዳለው ይታወቃል።በዚህ ረገድ የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደርም ሕጋዊ ማዕቀፎቹን መሠረት በማድረግ ወደ ከተማዋ የሚገቡ ባለሀብቶችን ለማበረታታት የሚያስችሉ አሠራሮችን ተግባራዊ ያደርጋል።በሀገር አቀፍ ደረጃ በሚተገበረው የማበረታቻ መመሪያ መሠረት የሚፈፀሙት መሬት ከሊዝ ነፃ የማቅረብ፣ ቀልጣፋ አሠራሮችን የማመቻቸትና ሌሎች ተግባራት ባለሀብቶችን የማበረታቻ ርምጃዎች አካል ናቸው።

የበጀትእጥረትበኢንቨስትመንትተግባራት፣በተለይም በመሬት ዝግጅት፣ ላይ ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደሚችል አቶ አበራ ስጋታቸውን ይገልፃሉ።የኢንቨስትመንት ባለድርሻ አካላት ለኢንቨስትመንት ስኬት ግብዓት የሆኑ ተግባራትን በእኩል ፍጥነትና ብቃት የመፈፀም ጉዳይም ሌላው በበጀት ዓመቱ በኢንቨስትመንት ዘርፍ ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብለው ከተለዩት ችግሮች መካከል ይጠቀሳል።‹‹የኢንቨስትመንት ዘርፍ ባለድርሻ ሆነው የሚንቀሳቀሱ 12 ተቋማት አሉ።እነዚህ ተቋማት በእኩል አፈፃፀም ፍጥነትና ብቃት የመራመዳቸው ነገር ትልቅ ትኩረት ይፈልጋል።እቅድን ከማስተዋወቅ ጀምሮ እየተናበብን ለመሄድ ጥረት አድርገናል።ይህ ጥረት ዘላቂ እንዲሆን አስተማማኝ ዋስትና የሚሰጥ የሥራ ፍጥነትና ብቃት ያስፈልጋል›› በማለት ይናገራሉ፡፡

# ጎሜ

# ፈንጂ ወረዳ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

"ከቡራትና ከቡራን እንደማመጥ! .. ያለነው እኮ የስብሰባ አዳራሽ እንጂ የገበያ አዳራሽ አይደለም። ጥያቄ ካላችሁ እጃችሁን አውጡ። በዚህ የደቦ ሕዝበ ዝማሬ የማናችሁን ድምጽ ከማን እንለየው? ይብዛም ይነስም እዚህ ያለን አብዛኛዎቻችን አንድም ትሁን ሁለት ነጭ ሽብት አብቅለናል አይደል?!...ታዲያ ምነው አዳራሹን የሕጻናቱ መማሪያ ክፍል ማስመሰላችን!... በሉ አሁን ባለሙያው የጀመረውን ሪፖርት ያጠናቅቅና ጥያቄ ካላችሁም ከዚያ ኋላ የምናደምጣችሁ ይሆናል።

ስለዚህች የ21 ዓመት ኮረዳ ወረዳችን፤ ሁላችንም ያየን የሰማነውንና የተሰማንን ተራ በተራ እናወራለን" ሲሉ የወረዳዋ ምክትል አስተዳዳሪ፤ በአዳራሹ ሞልቶ ለፈሰሰው ለወረዳው ነዋሪ ቀጭን ትዕዛዛቸውን ከማሳሰቢያ ጋር አስተላለፉ። ጸጥታው ሰፍኖ በሁካታው የተቋረጠው ሪፖርት ቀጠለ።

"በእኛ ሴክተር መሥሪያ ቤት በዘንድሮው በጀት ዓመት በርካታ የተዘጉ መንገዶችን አስከፍተናል፤የተከፈቱትንም ቢሆን ወደ አገልግሎት አስገብተናል። ካሳካናቸው ግዙፍ ተግባራት መካከል አንደኛው አዳዲስ መንገዶችን መክፈታችን ነው። በቀበሌ `ሀ፣ ለ እና `መ በሦስቱ ቀበሌዎች በድምሩ የ21 ኪሎ ሜትር ሰፊ የመንገድ ዝርጋታ ያካሄድን ሲሆን፣ በቀበሌ `መ` የተሰራው የ 17 ኪሎ ሜትር የመንገድ ዝርጋታ ዋነኛው ነው..."

በአዳራሹ ከተሰበሰቡት የወረዳዋ ነዋሪዎች መካከል አንድ አዛውንት ለመናገር ሲቁነጠነጡ ቆይተው ጥያቄ ያላችሁ ሲባል አምስት ጊዜ እጃቸውን አውጥተው አምስቱንም ጊዜ ከዓይን እይታ ውጭ ሆነው ታለፉ። በስድስተኛውም ሳይታዩ ቀሩ። በሰባተኛው ግን እራሳቸው ለራሳቸው ዕድሉን በመስጠት ንድድ ብሏቸው "ጥያቄ አለኝ!" ሲሉ ጮክ ብለው ቆመው ድምጻቸውን አሰሙ። ሁሉም ዞር ብሎ በዓይኑ ገርመም አደረጋቸው። "ረጋ ይበሉ እንጂ አቶ ቸኮል! ጥያቄው ወዴት ይሄድብዎታል.. እኛም ብንሆን አንበርር ነገር...ኋላ እረሳው እንደሆን ብለው ሰግተው ከሆነ ደግሞ፤ እስከዚያ በወረቀት ጫር ጫር እንዲያደርጉት ብዕራችንን እናውስዎታለን። እንዲህ መሆኑ የስብሰባውም ሆነ የትልቅ ሰው ወጉም አይደለም። በሉ አረፍ ይበሉ። ቀጣዩን ዕድል ሰጥተንዎታል" ተባሉ

አዛውንቱም፣ በለሆሳስ "ዲስኩራም ሁላ! እናንተ ስትደሰኩሩብን መቼ ተራና ወረፋ አልናችሁ" በማለት በዓይናቸው ዙሪያ ገባውን አየት አድርገው ውስጣዊ ስሜታቸውን እያቀዘቀዙ ተመልሰው ወደ መቀመጫው ወረዱ። የማይደርስ የለም ተራው ደረሳቸውና ንግግራቸውንም ጀመሩ። "የዛሬ አምስት ዓመት የጠጠር መንገድ ይሠራላችሁኋል ገንዘብ አዋጡ ብትሉን ጊዜ ደ..ግ ሊያልፍልን ነው ብለን ከሌለን ላይ ተሯሩጠን አዋጣን። እሰይ! ማድረጋችን መልካም..ነገር ግን ይሠራላችኋል የተባለው የጠጠር መንገድ ተሠርቶ ካለቀ በኋላ፤ ሦስቴ እንኳን ተመላልሰን ሳንረግጠው ይሄው በክረምቱ ዝናብ መንገዱ ብልሽት ብሏል። ያለመታደል ሆኖ ጠጠሩም ሟምቷል። ምናልባት ጠጠሩ የተሰራው ከድንጋይ ሳይሆን ከበረዶ ግግር ይሆናል።

መንገዱም ከመንገድነት ወደሚያሰጋ ስምጥ ሸለቆነት ተቀይሯል። እስከ ጥግ ድረስ የተንጣለለው ጎርፍም ለእግረኛም ሆነ ለጀልባ የማይበጅ ሆኗል። ይሁን እንግዲ.... እሱንስ ማን አየበት?!... እቺን ብቻ ግን ልጠይቅ፤ በቀበሌ `መ` የተሠራልን መንገድ 14 ኪሎ ሜትር ሆኖ ሳለ አስራ ሰባት ኪሎ ሜትር ነው የሠራንላችሁ የምትሉን ለመሆኑ ሦስቶቹ ኪሎ ሜትሮች ከኛ ተሰውረው ወዴት ገብተው ነው? ወይንስ ቁጥሩም እንደኑሮ ውድነቱ ከቀን ወደ ቀን ያሻቅብ ጀምሯል..." ሲሉ ጊዜ በልብ ያለ ሲነገር ስሜቱ የተኮረኮሩ ያህል ነውና አዳራሹ በሳቅና በሹክሹክታ ተጥለቀለቀ።

እንግዲህ ብዙ ሰማን መድረኩን ፍትሃዊ ለማድረግ አንድ ያለችውን ዕድል ለሴቶች እንስጥ። ወንዶች እስቲ ትንሽ እረፍት አድርጉ። እህሳ... ከአዳራሹ ሴቶች የላችሁም? እያ ምክትል አስተዳዳሪው በዓይናቸው አዳራሹን ከጥግ እስከጥግ ቃኙት። "እኛስ አለን ... እንዲያው የቱን ከየቱ እናስቀድመው እያልን ስናስብ እንጂ የምንለውስ መች ጠፍቶ ብለው ነው" በማለት እማማ ትርንጎ ከመቀመጫቸው ብድግ አሉ። "እንግዲህ ኖሮ ኖሮ ተቤት ዞሮ ዞሮ ተመሬት መሆኑ ተዚህ ላለን ለማናችንም ግልጥ ነው። ነገሩ ዛሬ ላይ ተቤታችን ውስጥ ታለን ሁናቴ የተነሳ ኑሮ ቢለያየንም ነገ ሁላችንም ያለመሪና ተመሪ፣ ያለ ሀብትና ድህነት ሁላችንም ተእኩል የምንገናኘው ተያው ተመሬቱ ላይ፤ ተአፈሩ ውስጥ ነው።

ተቀበሌያችን አቅራቢያ መካነ መቃብር ባለመኖሩ በየ ጊዜው ተሊቀመንበራችን ደጅ እየጠናን ስንጮህ ስንማጠን እሄው እኛም አረጀን። በሕይወት ሳለን የተንከራተትን አልበቃ ብሎ ስንሞትም መቃብር ፍለጋ ሀገር ቂጥ እንኳትናለን። የክረምቱስ አይነገር...ዝናቡ ቲዘንብ ወንዙ ተአፍ እስከ ገደፉ ጢፊፍ ብሎ ይሞላል። የቀዬው ሰው እንደሆን ህዳር ህዳር ለሥርግ፤ ክረምቱ ቲገባ ደግሞ ለሞት ይሯሯጣል።

እንግዲህ ጠደይ እስኪትገባ ጠብቀህ ሙት አይባል ነገር ሰው የሚሞተው ወዶና መርጦ አይደለም። ታዲያ የክረምቱ የወንዝ ሙላት ባየለ ጊዜ፤ ወዲያ ማዶ ለመሻገር የሞላው እስቲጎድል አስክሬን ይዘን ተወንዙ ዳር ቁጭ ብለን ስናለቅስ ስንላቀስ እንቆያለን። እንባችን ቲደርቅ ጊዜም አፉችንን ከፍተን ስላቦ እያልን እግዜሩንም አየሩንም እንማጠናለን። የኛ ቀዬ ሰውስ እንደሆን ሞቶም አያርፍ፤ ይህቺ ገፊ ይበላት የከፋቷ ዋጋ ነው...እሄ መተተኛ መቼስ ጉዞው ወደ ሲኦል ቢሆን ነው እንጂ ገና አፈሩንም ታይለብስ ስቃዩ ተዚሁ የጀመረው...እያለ ለቀስተኛው ተየስርቻው ቁጭ ብሎ አስክሬኑን ይራገማል።

እንዲያው እግዜሩም እራርቶ ወንዙን ተሻገርን ስንል ወሳንሳ ተሸካሚው ተየመንገዱ ላይ ጭቃው እያዳለጠው ተነአስክሬኑ ባፍ ጢሙ ይደፋል። እሱስ ላንድ ነብሱ አንደኛውን ሞቷል፤ እኛ ግን እስተመቼ ነው ተአስክሬን ጋር ፍዳችንን ስንበላ የምንሰነብተው?" ብለው ፊታቸውን በጥያቄ ቅጭም ሲያደርጉ ልክ ነው በማለት ሕዝቡ በጭብጨባ ድጋፉን አሳያቸው። እማማ ትርንጎ ንግግራቸውን በዚሁ እንደማይቋጩ የተረዳውና ከአወያዮቹ መካከል አንዱ የሆነው የወረዳው የአስተዳደር ጽህፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ፤ እንደምንም ጭብጨባውን ታክኮ ገባና "እማማ ትርንጎ ያሉት ነገር በደንብ ገብቶናል። ከሚመለከተው አካል ጋር ተነጋግረን ችግሩንም በቅርቡ የምንፈታው ይሆናል" በማለት የጥያቄ እሩጫቸውን በምላሹ ገታው።

ይህችው የፈንጂ ወረዳ፤ ወደ ወረዳነት አድጋ በአዲስ መልክ ከተወለደች ድፍን 21 ዓመታትን ብታስቆጥርም አሁንም ግን የምትኖረው ገና አይኑን እንዳልከፈተ ሕጻን ልጅ ነው። ከመሠረተ ልማት ይልቅ መሠረታዊ ጥፋቶች ገዝፈው ይታያሉ። በወረዳነት በተያዘችበት ወቅትም በሥሯ ከነበሩ በርካታ ጎስቋላ ከተሞች መካከል ለሁሉም ይበጃል የተባለው አንደኛው ጎስቋላ ተመርጦ ዋና ከተማ እንዲሆን ተወሰነ። ከዚያን ጊዜ አንስቶም የወረዳዋ መቀመጫ ለኔ ነው የሚገባኝ በሚል ውዥንብር በሁለት የተለያዩ ቀበሌዎች መካከል ለአምስት ተከታታይ ዓመታት ያህል የእርስ በርስ ጦርነት ተካሄደ። ጦርነቱ የድንጋይና የዱላ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚም ጭምር ነበር።

አርሶ አደሩንና ነጋዴውን በዚህ የጦርነት ቀለበት ውስጥ አስገብቶ በመዘወር ጦርነቱን የሚያፋፍሙት ደግሞ ወጣቶቹ ናቸው። በቀበሌ ሀ የሚገኝ አርሶ አደር ምርቱን ለመሸጥ ወደ ቀበሌ ለ ገበያ መግባትም ሆነ ድንበር አቋርጦ ማለፍ አይችልም። ነጋዴውም ከብቶችንና የሸቀጥ እቃዎቹን ይዞ እንዲገባም ሆነ እንዲወጣ አይፈቀድለትም። ሁለቱም የሚታውቁበት የራሳቸው የሆነ ምርት ስልነበራቸው የኢኮኖሚው ጦርነት ተፋፍሞ የራሺያና የአሜሪካንን ጦርነት የሚያስንቅ ነበር።

ትኩሳቱ ሲጨምር ደግሞ ሀገር አቆራርጠው የሚመጡ የሕዝብ ትራንስፖርቶችም ሆኑ መንደር ለመንደር ውር ውር የሚሉ ባለ ሁለትና ሦስት እግር ተሽከርካሪዎች ወደየትም ውልፍት እንዳይሉ ማቀብ ይጣልባቸዋል። በሁለቱም ወገን የሚገኙ ሞገደኞቹ የውስጥ ቆስቋሾች በየጊዜው የማጥቂያ ስልታቸውን እየነደፉ በስሜት የጋለውን የመንደር አርበኛ እየመለመሉ የክተት አዋጅ ያውጃሉ። ሰበብ አስባብ ፈልጎ ማታ ማታ እያደቡ ወደ ሌላው ቀበሌ ሰርጎ በመግባት ቤት አቃጥሎ የሌላውን ሀብት ንብረት መዝረፍ ለሌባው ያመቸ ግርግርና የዘረፋ እንኪያ ሰላምታቸው አደረጉት።

አፈ ጉባዔው ያሉትን ካሉ በኋላ ማይክራፎኑን በተራ ለአስተዳዳሪው ሰጥተውት ንግግር በማድረግ ላይ ነበሩ። ከንግግራቸው መሃልም "በአዲስ መንፈስ ወደ ሥራ የገባንበት የመጀመሪያው ዓመት የአንደኛ ዕሩብ ዓመታችን የሥራ አፈጻጸም ከአምናው የግማሽ ዓመት የተሻለ ሆኖ ተግኝቷል" በማለት ለጭብጨባዊ ምላሽ ሕዝቡን በዝምታ ሲመለከቱት አንዳንዱ በልቡ፤ የምናጨበጭበው ለአምናው ውድቀት ነው ለዘንድሮው ስኬት እያለ ቀርቶ እንዳይቀርበት ሲል ሞቅ አድርጎ አጨበጨበ፡፡

**በልማቱ እንደምንደሰት ሁሉ ችግሮችም ሲያጋጥሙ ከመወነጃጀልና አንዳችን አንዳችን ላይ ጣት ከመቀሰር ጉድለቶቻችንን በጋራ ለማስተካከል መነሳት ይገባናል**

በዚሁ መሃል ድንገት በአካባቢው ከተደባዳቢነቱ የተነሳ ካራቲስቱ እየተባለ የሚጠራው ታዋቂው እብድ፤ ምንጩ የተባለውን የኔ ቢጤ ከኋላው አስከትሎ ሰተት ብሎ ያለፍርሃት ወደ አዳራሹ ዘልቆ ገባ። ሁሉም ጭብጨባውን ገታ አድርጎ ፊቱን ወደ በሩ አዞረ። "ምን ፈልጋችሁ ነው ውጡ" አለ አንደኛው አስተናባሪ ለመጠጋት ፈራ ተባ እያለ።

እብዱ አይኑን አጉረጥርጦ "ከዳቦውም... ከቡናውም እንድትሰጡን እንፈልጋለን!" አለ፤ በማይወላውል አቋም። ያውቁታልና ከአንዱ ጥግ ተቀምጠው እንዲበሉ ተደረገ። አስተዳዳሪው ንግግራቸውን ቀጥለው አፍታም ሳይቆዩ እብዱ በአንደኛው እጅ ዳቦውን በሌላኛው እጅ ሲኒውን እንደያዘ ብድግ ብሎ ቆመ። እሺ አሁን ደግሞ ምን ፈለግህ? አሉት አስተዳዳሪው በንዴት ማይክራፎኑን እንደጨበጡ ድምጻቸው የማጉያውን ስፒከር እያንቀጠቀጠ። የኔ ቢጤው በድንጋጤ ሹልክ ብሎ እግሬ አውጪኝ ሲል ዘሎ ቢወጣም፤ እብዱ ግን ምንም ሳይመስለው ጅንን ብሎ "አበል እፈልጋለሁ...እኔ አበል እንድትስጡኝ ነው የምፈልገው..እንኩ ዳቧችሁን እናንተው ብሉት..." እየፈረፈረ ወለሉ ላይ በተነው።

ፈንጂ ወረዳ ግራና ቀኝ ፊትና ኋላ ከተኮለኮሉት ቤቶች የተነሳ የ21 ዓመት ዕድሜ ያለው ከተማ ሳይሆን የስደተኛ ካምፕ ነው የሚመስለው። "እኔ ምለው!" አሉ ሃምሳ አለቃ በአንደኛው የስብሰባ ዕለት ምርር እያሉ" እኔ ምለው ግን...ከተማችን የወረዳው ንኡስ ከተማ የሚል ማዕረግ ሳይለጠፍበት በፊት ሌላው ቢቀር በውሃ አንቸገርም ነበር። ከአምስት ዓመታት በፊትም ቢሆን ከታንከሩ በጀኔሬተር ሃይል እየተሳበ በሳምንት አራትም ሦስትም ቀን ከቧንቧችን ይፈስ ነበር። አሁን ታዲያ ሌላው ያደረገው አይቅርብን ብላችሁ ውሃውንም ለአምፖል እንኳን በናፈቀን የሙብራት ሃይል ማድረጋችሁ ምን የሚሉት ፌዝ ነው? ከውሃ እጦት የተነሳ ላንቃችን ደርቆ ቧንቧዎቻችንም የሸረሪት ድር ማድሪያ ሆነዋል..." ከማለታቸው የውሃ ቢሮው ሃላፊ ብድግ ብሎ "ሃምሳ አለቃ ይህን ያደረግነው እኮ እኛም ተቸግረን ነው።

የማንቀሳቀሻ ጄኔሬተሩ ስለተበላሸ ቤንዚን ሞልተነው ገና ዞር ከማለታችን ምጥጥ አድርጎ አላየሁም አልሰማሁም በማለት ዓይኔን ግንባር ያድርገው ይላል። ያፈስስ እንደሆን እያልን መሬቱን ብንመለከትም ሊፈስስበት ቀርቶ ለዓይን የሚታይ ጠብታም አይገኝበትም" እያለ ሲመልስ ሃምሳ አልቃም "ታዲይ ማሽኑን ከዓይናችን ሰውራችሁ? ከወዴት አኖራችሁት?..." ብሎ ለመጠየቅ ዳዳቸውና መፍትሔ ላይገኝ የምን ምላስ ማንቀዝ ነው ብለው ቁጭ አሉ።

ሌላኛው የማይድን እራስ ምታትዋ፤ ከዞኑ ዋና ከተማ የሚያገናኛት የአስፋልት መንገድ ነው። ከተጀመረ ዘመናት ቢያልፉትም ፍጻሜው ግን የህልም እንጀራና እንደምጽአት ቀን የራቀ ነው። ይህን መንገድ ተራ በተራ እየተፈራረቀ ያልቦጫጨረው ስካቫተርና ዶዘር፣ ያልነካካው የመንገድ ሥራ ተቋራጭ አልነበረም። ነገር ግን ሁሉም የድርሻቸውን ተቆራጭ እያደረጉ እብስ ከማለት ውጪ የፈየዱላት አንዳችም ነገር የለም።

በጀቱ ተበዘበዘ፤ ወጣቱም ተመረዘ። ነገሩን ቢያይ ቢያይ ምንም ጠብ የሚል ነገር ያጣው የወረዳው ወጣት፤ አንዳንዱ በገዛ ዳቦዬስ ልብ ልቡን ስለምን አጣለሁ...አንዳንዱ የአባትህ ቤት ሲዘረፍ አብረህ ዝረፍ ...ሌላኛውም እኔ ባልበላውም መበላቱ እንደሆን አይቀር፤ እያለ የተባብረን እንብላ ዘመቻውን ከፈተ። እየተመሳጠሩ ሙብላት እየጠረጠሩ መቆርጠም... ይሄኔ ነው።

የፈንጂ ወረዳ ነዋሪዎች ስብሰባቸውን ከመጨረሳቸው በፊት አንድ ጉምቱ መምህር ተነስተው የሚከተለውን ሃሳብ ሰጡ፡፡ ወዳጆቼ ስነወቃቀስ ብንውል ፋይዳ የለውም፡፡ አንዳችን አንዳችንን ስንከስ ብንውል ማናችንም ከጥፋተኝነት አንድንም፡፡ ጥፋቱ የሁላችንም ነው፡፡ በመንግሥት ኃላፊዎች ላይ ጣታችንን ብንቀስርም እነርሱም ከእኛ ጉያ የወጡ ናቸውና በተለየ ዓይን ልናያቸው አንችልም፡፡ ደግሞም ጥፋታችው ብቻ ሳይሆን ልማታቸውም ሊታየን ይገባል፡፡ ያው ፍላጎታችን ብዙ ስለሆነ እንጂ የተሰራውን ነገር እንደቀላል ማየት አይገባንም፡፡ በልማቱ እንደምንደስት ሁሉ ችግሮችም ሲያጋጥሙ ከመወነጃጀልና አንዳችን አንዳችን ላይ ጣት ከመቀሰር ጉድለቶቻችንን በጋራ ለማስተካከል መነሳት ይገባናል፡፡ይህ ሲሆን እኛ ከችግሮች በላይ ሆነን ከራሳችን አልፈን ለሌሎችም ምሳሌ መሆን እንችላለን›› ብለው ሃሳባቸውን ገቱ፡፡የወረዳው ህዝብም አጨብጭቦ ስብሰባው አበቃ፡፡

ስፖርትና መዝናኛ

# የዘመን ጥበብ

# ደካማው ማን ነው፤ ጥበብ ወይስ ጠቢቡ?

**ገርማ መንግሥቴ**

ዛሬ ዛሬ “ጥበብ ሞቷል”፣ “ሙዚቃ ድሮ ቀረ”፣ “ሥነጽሑፍ ተዳክሟል”፣ “ፊልም ወርዷል”፣ “ትያትር ‘ለመሆኑ አለ እንዴ?’” ወዘተ አይነት አስተያየቶች ሲዘወተሩ ይሰማል።

“ታሪክን አወላግዶ ስለ ጻፈ የከሸፈው ጸሐፊው እንጂ ታሪክ አይደለም” የሚል አገላለፅም የበርካታ ብዕረኞችን ድጋፍ አግኝቶ ለአደባባይ ሲበቃ ተመልክተናል። “የአንድ ጥበብ ክዋኔ ደካማ መሆን የ‘ጠቢቡ’ን እንጂ የጥበብን ድክመት አያመለክትም” የሚለውም እንደዛው።

በዚህ ሳያነቡ የሚጽፉ፣ ሳያጣሩ የሚያወሩ... በበዙበት ዳፍንት ዓለም “ጥበብ ሞቷል” ባዮች ቢበዙ ምን ይደንቃል፤ እራሱ ጥበብ ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ በማይታወቅበት በዚህ ዘመን “አርት ድሮ” ቀረ ባዮች ቢደመጡ ምን ይገርማል ባዮች ደግሞ “የሞተው ጠቢብ ተብየው እንጂ ጥበብ አይደለችም” ነው የሚሉት።

ጥበብ በተፈጥሮዋ ደካማ ሆና አታውቅም። ደካማ የሚያስመስላት ተጠበብኩ ባዩ ያለ ሙያው ገብቶ ሲያተራምስ፤ ሲያጎሳቁላት ነው። ጥበብ እውነተኛ ጠቢብ ካገኘች እያበበች፤ እየፈካች፤ እየደነደነች ... ከመሄድ ወዲያ ሌላ ጠባይ የላትም።

እውቁ ዜመኛ አብዱ ኪያር በ“የኔ ማር” ዜማው (ብዙ ሰው የልጅቷን ውበት ከማድነቅ ባለፈ ሌላኛውን፣ የተሸፋፈነውን መልእክት የተረዳለት አይመስልም) “ቃላት ላይ / ፊደል ላይ ሥልጣን የሌለው ሰው፤ አይችልም አይችልም ውበትሽን ሊገልፀው” እንዳለው (አፅንኦቱን ልብ ይሏል) እማይችሉትን እንደ ማይችሉት አውቆ ወደ እሚችሉት ማቅናቱ ነው የሚመከረው።

**አብዱ፤**
**ውበት ቁንጅናሽን በቃል ለማስረዳት፣**
**የቋንቋ እውቀት ያለው ያስፈልጋል ረዳት።**

ሲልም (ከሰማሁት ቆየት ስላለ ዝንፈት ካለ ይቅርታ እጠይቃለሁ) ጉዳዩን ከፍ ከማድረግም በላይ በ“እውቀት” መሠረት ያሲዘዋል።

እዚህ ላይ “ውበት”ን ብቻ እንኳን ብንወስድና ከ“ቢዩቲ” ከፍ አድርገን የዓለም ድንቅ ፈላስፎች ጊዜና እውቀታቸውን ያፈሰሱበትን “ሥነውበት” (ኤስተቲክስ)ን ብንመረምር “የቋንቋ እውቀት ያለው ያስፈልጋል ረዳት።” የሚለው ተገቢ ሆኖ እናገኘዋለን። ምክንያቱ ደግሞ ውበትን ለመግለፅ ኮልታፋ አንደበትና ዱልዱም ብዕር ምንም ፋይዳ የሌላቸውና ጉዳዩ እጅጉን የባለሙያን የተባ አእምሮና ብዕር መፈለጉ ነው። የመፈለጉ ጉዳይ ደግሞ ውበት እጅጉን ረቂቅና እንዲህ በቀላሉ ሊንፈላሰሱበት የማይቻል መሆኑ ሲሆን፤ ይህንን ማድረግ ያልቻለና ውበትን ያህል ነገር የሚያርመጠምጥ ከመጣ የተርመጠመጠው እሱ እንጂ ጥበብ አይደለችም ማለት ይሆናል።

ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን በ“መትፋት ያስነውራል” ዘለግ ያለ ግጥሙ፤

**—እፍ አንቺ መብራት ጥፊ፣**
**እፍ አንቺ መብራት ክሰሚ፣**
**ጥፊ፣ ጨልሚ፣ ውደሚ“ . . .**
**አስ አሱ ሼክስፒር ቂሱ፣**
**መቸም አያልቅበት እሱ።**
**መድረክ ላይ ኩስ ከሚተፋ**
**አዎን ሕይወት ረሷ ትጥፋ . . . (ሙሉ ግጥሙን ይመለከቷል።)**

እንዳለው ሁሉ፤ የጥበብን ገበታ ከማበላሸት አርፎ መቀመጥ በራሱ ጠቢብነት ነው። (ፀጋዬ መድረክ ሲረክስ ከማየት ሕይወት ራሷ ብትጠፋ የሚሻለው መሆኑን ልብ ይሏል።)

ብዙዎች እንደደረሱበት፤ ደርሰውበትም እንድንደርስበት እንዳደረጉት ሁሉ ጥበብ የሕይወት ጥሪ እንጂ የነሸጠው ሁሉ የሚገባባት መዋኛ ገንዳ አይደለችም። ነፍሱን ይማረውና ባለቅኔው ጎሞራው (ኃይሉ ገብረዮሃንስ) በአንድ ወቅት በወቅቱ ስለነበሩት የሥዕል ሥራዎች አስተያየቱን እንዲሰጥ ተጠይቆ “አንድ ገረወይና ቀለም ይደፋና ‘ምንድን ነው?’ ሲሉት ‘አብስትራክት ነው’ ይላል። [. . .] ውበት ከእነ እንቶኔ ብብት ስር የሚወጣ አይደለም።” ያለውንም ባናብራራው እንኳን እዚህ አስፍረነው ለማለፍ እውነቱ ግድ ይለናል።

ከላይ ያነሳናቸው ልሂቃን አስተያየት የሚነግረን በርእሳችን ያነሳነው ሃሳብ ትክክል መሆኑን ብቻ ሳሆን፤ ከዛም በላይ በመሄድ ጥበብ መነገጃ አለመሆኗን፤ የጠቢባን የፍሬ ውጤት መሆኗን ጭምር ነው።

ነገሮችን ከእውነታው ጋር እያሰባጠርን እንያቸው ካልን ጥበብ የጠቢባን ተግባር እንጂ የማንም ሆና አታውቅም። “ጥበብ አስተማሪ ነች” ካልን የጠቢባን ሥራ ስለመሆኗ ማረጋገጫ ነው። “ጥበብ የሕይወት ነፀብራቅ ነች” ካልን የትጉሀን ተግባር ስለ መሆኗ ሌላው ማረጋገጫ ነው። በመሆኑም አብዱ ኪያር አፅንኦት ሰጥቶ “አይችልም አይችልም” እንዳለው ማንም እየተነሳ፣ ጥበብ የሕይወቱ ጥሪ ያልሆነው ሁሉ፤ በጥበብ ጀሮ ላይ ስሙን ማንጠልጠል የናፈቀው ሁሉ፤... ሁሉ ብድግ እያለ የጥበብን አይን ይደነቁል ዘንድ አልተፈቀደለትም። ወይም፣ አብዱ እንዳለው አይችልም።

ሰለሞን በስሙ ላይ “ጠቢብ” የሚለውን ማእረግ የደረበው ስለፈለገ፤ ወይም ስለተመኘው አይደለም። ጠቢቡ ሰለሞን የተባለው ሆኖ ስለተገኘ ነው። ሎሬት ፀጋዬ ገብረመድህን ሎሬትነትን የተጎናፀፈው ስለፈለገው ወይም ስለተመኘው ሳይሆን ሆኖ ስለተገኘ ነው። ሌሎችም እንደዚሁ።

“ገና በልጅነቴ ይህንን የግጥም መጽሐፍ በማሳተሜ የተሰማኝ ደስታ” . . . በማለትና ራስን ማንቆለጳጰስ፤ እንዲሁም፣ “በዚህ እድሜህ ይህንን የመሰለ መጽሐፍ በማሳተምህ እንኳን ደስ አለህ” በማለት ከንቱ ውዳሴን ማዝነብ ጥበብን ምንም የሚጎዳት ነገር የለውም - “ጥበበኛ”ውን ከማሳቀል በስተቀር። በስመ ስፖንሰር በፈጠራ ሥራዎች ውስጥ ማስታወቂያዎችን ማጎር ጥበበኛው ከደረጃ በታች መጫወቱን ብቻ ሳይሆን አላዋቂ ሳሚ . . . መሆኑን ከማሳየት በስተቀር የጥበብ ክብር በጭራሽ ዝቅ አይልም። ጉዳዩን ወደ ታሪክም መውሰድ እንችላለን።

አሁን አሁን የኢትዮጵያ ታሪክ ባለሙያ ያልሆነ ሰው ማግኘት እየከበደ ሁሉ ያለ ይመስላል። “ሁሉም” በሚመስል ደረጃ የታሪክ ጸሐፊ ሆኗል። ሁሉም በፈለገው አይነትና መጠን ሲመነዝረው ይታያል። እንደፈለገ ያድርገው እንጂ የኢትዮጵያ ታሪክ እንደ ሆነ ያው የኢትዮጵያ ታሪክ ከመሆን ከፍም ዝቅም ሊል አይችልም። በመሆኑም፣ ጉድ የሆነው የኢትዮጵያ ታሪክ ሳይሆን የኢትዮጵያን ታሪክ አጠናሁ፣ ጻፍኩ ... ያለው ብቻ ነው።

በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት ፖርቹጋላዊው ሮማን ፕሮቻዝካ የተሰማራበት የስለላ ተግባር ተነቅቶበት ተይዞ ወደ ሀገሩ በመላኩ ምክንያት ሀገሩ ከገባ በኋላ ደበበ እሸቱ “የባሩዱ በርሜል” በሚል ርእስ የተረጎመለትን አሳፋሪ መጽሐፍ አሳትሟል። የሚገርመው መጽሐፍ ማሳተሙ አይደለም። የሚገርመው መባረሩን እንደ ቂም በመያዝ ለኢትዮጵያንና ኢዮጵያውያን ያለ ስማቸው ስም መስጠቱ፤ ያለ ባህርያቸው ባህሪን ማላበሱ፤ ያለውሏቸው ማዋሉ ነው።

የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ደመኛ ጠላት የሆነው ይህ ሰውዬ (በኋላ የገዛ ሀገሩን ሁሉ በመክዳት ለቅጣት ተዳርጓል) እኛን በዛ መልክ ይግለፀን እንጂ ሳይውል ሳያድር ከማንነት ሚዛን ላይ የወደቀው እሱ እንጂ እኛ አይደለንም። ወይም፣ አይከስሩ ክስረት የከሰረው እሱ እንጂ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ታሪክ አይደለም። (እዚህ ላይ ጋሽ ደበበ እሸቱ አንድ ነገር የሳተ ሲሆን፣ እሱም ቢያንስ ሰውየው ልክ መጽሐፉን እንዳሳተመ ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክረስት ስለ ማንነቱ የሀገሪቱን አምባሳደር ሁሉ ሳይቀር በማናገር ለእማኝነት ያበቁትን ጽሑፍ በ“መቅድም” ወይም ሌላ መልክ በትርጉም ሥራው አለማካተቱ ነው። ሰውየው በሀገሩ መንግሥት ሁሉ ሲሳደድ እንደነበረ፤ በኋላም ሀገሩን ሁሉ ለባእድ አሳልፎ እንደሰጠ በፓንክረስት ጽሑፍ በዝርዝር ሰፍሯል።) ይህ የሚያሳየን፣ ልክ እንደ ጥበብ ሁሉ፣ የተዛባ ታሪክ ጸሐፊው እንጂ ታሪክ ራሱ ሊወድቅ እንደማይችል ነው።

እንደምናውቀው የጥበብ መመዘኛ እራሱ ጥበብ ነው። ጥበብን የታጠቀ ጠቢብ ጥበብን፣ “እንደ በሬ ሻኛ” (እንዳለችው ትእግሥት) ከላይ ያውላታል። ከእነ ማእረጓ ከፍ አድርጎ ያውለበልባታል፤ እንደ ቀሲሱ ሼክስፒር፣ እንደ ሎሬቱ ፀጋዬ ያነግሳታል እንጂ ያዋረዳት መስሎት አይዋረድባትም። ያንኳሰሳት መስሎት አይንኳሰስባትም። ምን እያልን ነው፣ ጥበበኛ ተብዬው እንጂ ጥበብ አትወድቅም።

ጥበብ ያው ጥበብ እንጂ ሌላ ልትሆን አትችልም። ማለትም፣ ከፍም ዝቅም ማለት አይሆንላትም። ያው የተፈጥሮ ባህርይዋን ይዛ ከመዝለቅ ውጪ ከነፈሰው ጋር ልትነፍስ፣ ከወደቀው ጋር ሁሉ ልትከሰከስ አትችልም። በመሆኑም፣ ችግሩ የጥበብ ሳይሆን የ“ጥበበኛ”ው ሆኖ ይቀራል ማለት ነው።

ችግሩ የተደራጊው ሳይሆን የአድራጊው ሆኖ የመቅረቱን ጉዳይ በላይኛው ምሳሌ (በጠቀስነው ፖርቹጋላዊ ሰላይ) ልናየው እንችላለን። ወደ ጥበባችን እንምጣ።

ማንም “ግስ ግሳንግሱን ይዞ፣ ብዕሩን ቀስሮ ወረቀት ተመቸኝ ብሎ ስለ ቸከቸከ ብቻ ጠቢብ ሊሆን አይችልም። አንድ ገረወይና ቀለም ስለ ደፋ ብቻ የተዋጣለት ሠዐሊ ሊሆን፤ ወይም፣ ሊባል አቅሙ አይፈቅድለትም። የጥበብ ሰው፤ ወይም፣ እንደ ሠለሞን “ጠቢቡ ...” ለመባል ጥበብ “የሕይወት ጥሪ” ልትሆን ይገባል። ካልሆነ ደካማው እሱ እንጂ ጥበብ (አርት) አይደለችም።



እዚህ ላይ ከአሁኑ ዘመን አንድ የቅርብ ምሳሌ እንውሰድና ማን እንደወደቀ እንመልከት።

እውነቱን ስንናገር ያለንበት ዘመን መፍጠር በመገልበጥ የተተካበት፤ የፊደል ዘርን ያልለየ ሁሉ የደራሲና ባለቅኔዎችን ጎራ የተቀላቀለበት ጊዜ ነው። ለዚህ ደግሞ ሙዚቃችንን የሚያክል ማሳያ የለም። እንደው፣ እስቲ አንድ በመንደር ጎረምሳ ያልተገለበጠና ዳግም ያልተዜመ ምርጥ የቀድሞው፣ የወርቃማው ዘመን ዜማ አለ? ከጥላሁን ገሠሠ ዘመን ተሻጋሪ ሥራዎች ምን ቀረ፤ የመሀሙድ ቁንጮ ቁንጮ ሥራዎች ተፌዘባቸዋል። ሙሉቀን፣ ሂሩትና ብዙነሽ በቀለ፤ አስቴር ከበደ ... ምናቸው ነው ያልተዘረፈው? በዋናው ድምፃዊና በሥራዎቹ መካከል ግድግዳ በመሆን የሰውን ሁሉ ዜማ እያስነኩት አይደለምን?

ወደ መጽሐፍም ብንመጣ ያው ነው። “የሚያቃጥል ፍቅር”ን እንዳለ በቁሙ ዘርፎ፣ በሕግ ተጠያቂ እንኳን ላለመሆን ማተሚያ ቤቱን በሀገር የሌለ፣ “ጠጅ ሳር ማተሚያ ቤት” ብሎ በአደባባይ መቸብቸብን ምን ይሉታል? በጥበብና ፈጠራ ላይ ይህ ሁሉ በደል ቢፈፀምም ዞሮ ዞሮ የወደቀው፣ በታሪክም ተጠያቂው ዘራፊው ቡድን እንጂ ጥበብ አይደለችም።

ሎሬት ፀጋዬ በ“እሳት ወይ አበባ“ው “ሥነግጥም የፈጠራ ሁሉ፣ የሥነጽሑፍ ሁሉ የደም ጠብታ ነው።” ካለ የቆየ ቢሆንም፣ የሚሰማ ጠፍቶ በእነ “የቀንድ አውጣ ኑሮ” መድበል ውስጥ እንደነ “ባጃጅ” አይነት ግጥሞችን እናነብ ዘንድ የተፈረደብን ጉዶች ከመሆን አላመለጥንም። እኛ አናምልጥ እንጂ የወደቅነው እኛ ሳንሆን ባለ “ባጃጁ” መሆኑን ግን ሁሉም ያውቃል። ዛሬ ላይ ሆኖ ሲያስበው እራሱ ገጣሚው ከጥበብ ማማ ላይ መንከባለሉን በሚገባ ስለ መረዳቱ መጠራጠር አይቻልም። (ልክ ሚሌኒየሙ መግቢያ አካባቢ “የድሮ ገጣሚያን ጨለምተኞች ናቸው። እኛም ጨለምተኝነትን ከእነሱ ነው የተማርነው።” ያለው የያኔው ጎረምሳ በቅርቡ “የድሮዎቹ በከፈቱልን መንገድ ነው እኛ እየሄድን ያለነው። የእነሱ ሥራዎች ባይኖሩ ኖሮ እኛ ሥራዎቻችንን ለመሥራት እንቸገር ነበር። ባለውለታዎቻችን ናቸው።” እንዳለው ገጣሚ ማለት ነው።)

ኢትዮጵያ በደንና ጫካ ሀብቷ አትታማም። ይሁን እንጂ ፊልሞቻችን (አንዳንዶቹ በሞባይል ቪዲዮ የተቀረፁ ናቸው ተብለው ይታማሉ) በሁለት ባህርዛፎች መካከል እየሮጡ ጫካ ለማስመሰል ሲደክሙ ማየት ብርቅ አይደለም። የልጅቷ አስፈላጊነት ምን እንደ ሆነ ግልፅ ባልሆነበት ሁኔታ አንዲት ቆንጆ መጥታ ፈገግታዋን ስትረጨው ማሳየት፣ ከንዱ ላይ ስትዝለፈለፍና አይኗን ስታንከባልል መመልከት የዘፈንና ዘፋኞቻችን “ሁሉ” የጋራ ባህርይ ነው። በሥነጽሑፍ ሥራዎቻችን ውስጥ የሥርዓተ ፆታ ፍልሚያን ማንበብ በጣም ከተለመዱት ዘመን አመጣሽ ጭብጦች መካከል ቀዳሚው ነው። ይህ ሁሉ ሲሆን ጥበብ ሞቷል፤ ጥበብ ወርዷል ... የሚሉ መኖራቸው እየታየ ነው። ይህ ስህተት ነው። የወረደው፣ የወደቀው፣ የሞተው ያ ሥራና ሠሪው እንጂ ጥበብ አይደለችም። እድሜ ለጥበብ አምላክ ጥበብ አትሞትም - በትጉሃን አማካኝነት እያበበች ትሄዳለች እንጂ። እስቲ ወደ ሥነቃላችን ደግሞ እንሂድና “አንድ” እንበል።

የማህበረሰቡን ማህበረ-ባህላዊ እሴት መናድ ላይ ወገባቸውን አስረው የተሰማሩ ወገኖች እያደረጉት እንዳለው ከሆነ የሥነቃል ሀብታችን ሁሉ እየተከረከመና በእነሱ ልክ እየተሰፋ ይገኛል። ለዚህ ማስረጃ ይሆነን ዘንድ ደግሞ “የእነ ቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ብሎኬት” እና ሌሎችንም ማስታወሱ ብቻ በቂ ነው። ይህ ሁሉ ወንጀል ይፈፀም እንጂ ከጠቢብና ጥበብ ማማ ላይ የወደቀው ማን እንደ ሆነ ሁሉም ያውቀዋል። በተወለጋገደ ብዕር ሥነቃላችንን ለማወላገድ መሞከር ደግሞ ውጤቱ ከዚህ ውጪ ሌላ ምንም ሊሆን አይችልም።

በመጨረሻም፣ ኢትዮጵያ ጥበብ ሞልቶ የተረፈባት፣ ታፍሶ ያልተጨረሰባት ሀገር ነች። ከፊደላቷ ጀምሮ የራሷ የሆኑቱ ቁጥራቸው ከቁጥር በላይ ነው። አያልነህ ሙላት እንደሚለው የድራማ ጥበብ ከማንም በፊት እኛ ነበረን። ሙላቱ አስታጥቄ እንደደረሰበት የፖሊስ ማርሽን የሚመራው ፊት መሪ “ዘንግ” ነጮቹ ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ወስደውና አዘምነው መልሰው ለኛ የሰጡን ነው። ፕሮፌሰር ፓንክረስት እንዳሉት ኢትዮጵያ በሀገር በቀል እውቀት የሚደርስባት የለም፤ ታዲያ ምን ያደርጋል ... ። ፕሮፌሰር ክላውድ ሰምነር እንደሚሉት ለመካከለኛው ዘመን የዓለም ፍልስፍና ፈር ቀዳጇ (በፈላስፋው ዘርዓያዕቆብ አማካኝነት) ኢትዮጵያ (አፍሪካ) ነች። የኦፐን ዩኒቨርሲቲዋ ዶ/ር (ስማቸው ተዘነጋኝ) “Ancient African Mathematics from Ethiopia” በሚል ርእስ እንደለቀቁት ዘጋቢ ፊልም ለአሁኑ ዘመን ኮምፒውተር መሠረቶቹ ያለ ፍራክሽን የሂሳብ ስሌትን ይጠቀሙ የነበሩት የጥንት ኢትዮጵያውያን ሲራራ ነጋዴዎች ናቸው። በርካቶች እንዳረጋገጡት ንግሥተ ሳባን የሚያክል በዓለም ታሪክና ሥነጽሑፍ ውስጥ ስሙ የተጠቀሰ ታላቅ ሰው በዓለም የለም (በእውቀቱ በ“ከአሜን ባሻገር” ቢያዋርዳትም)። እንደ ድሩሲላ (Drusilla Dunjee Houston. Wonderful Ethiopians of The Ancient Cushite Empire; 1926) ከሆነ የሁሉም ነገር ምንጭ ኢትዮጵያ ነች። ዘርዝረን አንጨርሰውም። በእነዚህ ሁሉ ውስጥ የኢትዮጵያ ጥበብ ነበር፤ አለ፤ ይኖራልም። በመሆኑም መውደቅ ካለ የሚወድቀው ጥበባችን ሳይሆን ያጎደፋት ነው።

ማህበራዊ

# ልዩ ልዩ

## ‹‹እናት ለእናት››

አስናቀ ፀጋዬ

ወይዘሮ ውድነሽ ኤደር በአዲስ አበባ የጎዳና ፅዳት ሥራ ከተሰማራች አስራ አምስት ዓመት አልፏታል። በነዚህ ዓመታት ውስጥ ኑሮ በብርቱ ፈትኗታል። ከእለት ጉርስ በማታልፈው የ500 ብር ደሞዟ የላስቲክ ቤት ተከራይታ አስከፊ የድህነት ሕይወትን አሳልፋለች። የምተበላው አጥታ ፆሟን ያደረችባቸው ቀናትም ጥቂት አይደሉም። ልጇን ለማሳደግ የማትችልበት ደረጃ ላይም ደርሳ ነበር። ከወር እስከ ወር የማያደርሰው ደሞዟ ሁሌም ብድር ውስጥ እየከተታት የተብቃቃ ሕይወት እንዳትመራ አድርጓት ቆይቷል።

አሁን ግን እናት ባንክ እና ‹‹እንደዜጋ ማህበራዊ እንደራሴ›› የተሰኘ ሀገር በቀል ድርጅት ከአንድ ዓመት በፊት በጋራ ባዘጋጁት ‹‹የእናት ለእናት›› ሥልጠና መርሀ ግብር ተጠቃሚ ከሆኑ 60 እናቶች ውስጥ አንዷ በመሆኗ ሕይወቷ ተቀይሯል። በዚሁ መርሃ ግብር ሶስት አይነት ሥልጠናዎችን ወስዳለች። በወሰደችው ሥልጠና መሠረት በእናት ባንክ ከሃያ ብር ጀምሮ በመቆጠብ ከዋና ሥራዋ በተጨማሪ ሁለትና ሶስት ተጨማሪ ሥራዎችን እንድትሠራ አጋጣሚ ተፈጥሮላታል። በዚህም ከዚህ ቀደም የነበረውን ኑሮዋን በእጅጉ ማሻሻል ችላለች።

ዛሬ ላይ ወይዘሮ ውድነሽ ሥልጠናው ከምታገኘው ገቢ ላይ የቤቷን ወጪ ሸፍና የሚተርፋትን በመቆጠብ ገንዘብ በሚያስፈልጋት ጊዜ አውጥታ ለመጠቀምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ ተጨማሪ ገንዘብ እንድትበደር አስችሏል። ከዋና ሥራዋ በተጨማሪ በትርፍ ሰአቷ ቆሎ በመሸጥ ተጨማሪ ገቢም ማግኘት ችላለች። በተጨማሪም መንግሥት የቀበሌ ቤት ሰጥቷት ከቤት ኪራይ ተገላግላለች። የሚከፈላት ደመወዝም ቢሆን ከበፊቱ ተሻሽሏል። ከሁሉ በላይ ደግሞ ሥልጠናው ሕይወቷን በብዙ መልኩ ቀይሮታል። የሌሎቹም እናቶች እንደዚሁ።

**በሥልጠናው እናቶቹ ገንዘብ በመቆጠብ ከሚሠሩት ዋና ሥራ በተጨማሪ ሌላ ሥራ በመሥራት እንዴት ገቢያቸውን ማሳደግ እንደሚችሉ እውቀት አገኝተዋል። እንደየአቅማቸው ከሃያ ብር ጀምሮ በመቆጠብና በቆጠቡት ገንዘብ ከችርቻሮ ንግድ ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎችን መሥራት ገቢያቸውን ማሳደግ ችለዋል**

የእናት ባንክ ምክትል ፕሬዚዳንት ወይዘሮ ገነት ሀጎስ እንደሚናገሩት ባንኩ ‹‹እንደዜጋ ማህበራዊ እንደራሴ›› ከተሰኘ ሀገር በቀል ድርጅት ጋር በመሆን በአዲስ አበባ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ወረዳ ስምንት በጎዳና ፅዳት ለተሰማሩ እናቶች ሥልጠናዎችን በመስጠትና በማደራጀት በኢኮኖሚ ራሳቸውን እንዲችሉ፣ ራሳቸውንና ቤተሰባቸውን እንዲያግዙ የሚያስችል ‹‹እናት ለእናት›› የተሰኘ ፕሮጀክት ነድፎ ለሶስት ወራት ሲንቀሳቀስ ቆይቷል። በዚህም በጎዳና ፅዳት የተሰማሩ 60 እናቶች በሥልጠናው ተጠቃሚ ሆነዋል።

በሥልጠናው እናቶቹ ገንዘብ በመቆጠብ ከሚሠሩት ዋና ሥራ በተጨማሪ ሌላ ሥራ በመሥራት እንዴት ገቢያቸውን ማሳደግ እንደሚችሉ እውቀት አገኝተዋል። እንደየአቅማቸው ከሃያ ብር ጀምሮ በመቆጠብና በቆጠቡት ገንዘብ ከችርቻሮ ንግድ ጀምሮ የተለያዩ ሥራዎችን መሥራት ገቢያቸውን ማሳደግ ችለዋል። በዚህም ኑሯቸውን ማሻሻል ችለዋል። በዚሁ ፕሮጀክት ተሳታፊ ለሆኑ ሁሉም እናቶችም ባንኩ ቤተሰባዊ የበዓል ስጦታ አበርክቶላቸዋል።

በሥልጠናው ሂደት የወረዳው ድጋፍም ጠንካራ የነበረ ሲሆን እናት ባንክና እንደዜጋ ማህበራዊ እንደራሴ በጋራ በመሆን የእናቶችን የፅዳት ሥራ በጋራ ሞክረዋል። ሥራው ምን ያህል አድካሚና ምስጋና የሚቸረው እንደሆነም ለመረዳት ችለዋል።

እንደ ዜጋ ማህራዊ እንደራሴ ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ እዩኤል ካሳሁን በበኩላቸው እንደሚሉት፣ ድርጅቱ ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊት ከመንግሥት ፍቃድ ወስዶ ተመሥርቷል። ላለፉት አምስት ዓመታት ደግሞ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር የተለያዩ ሥራዎችን ሲሠራ ቆይቷል። በአራት ዓመታት ውስጥ 20 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን እንደ ዜጋ ለሀገራቸው የተሻለ ነገር ማበርከት የሚችሉባቸው መድረኮችን ለማምጣት እየሠራ ይገኛል።

የኢትዮጵያ ሁለንተናዊ እጣፈንታ በዜጎቿ እንደመሆኑና ዜጎቿ ደግሞ መፍትሄ ያላቸው በመሆኑ ብሎም የራሳቸው ታሪክ፣ ባህልና እውቀት ያላቸው በመሆኑ ድርጅቱ ይህን አቅም በማስተባበር አንድ ርምጃ ወደፊት ለማራመድ አበክሮ ይሠራል። ይህንንም ‹‹የእናት ለእናት›› ፕሮጀክት ድርጅቱ ሲጀምር በሁለት ዓመት ውስጥ 5 ሺ እናቶችን በኢኮኖሚ፣ ራስን በማስቻልና ሥልጠና በመስጠትና በማገዝ እንዲሁም ብድርን በማመቻቸት በተለይ በጎዳና ፅዳት የሚተዳደሩ እናቶች ባላቸው ትርፍ ጊዜ ተጨማሪ ሥራ መሥራት የሚችሉበትን ሁኔታ ለመፍጠር ነው።

በ60 እናቶች ላይ ተግባራዊ የሚሆን የሙከራ ፕሮጀክት በማዘጋጀት የሶስት ወር ሥልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል። በዚህም ውጤታማ ሥልጠና በመስጠት እናቶች ተጨማሪ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ በመሰማራት ሕይወታቸውን የሚያሻሽሉበትን ሁኔታ መፍጠር ተችሏል። በቀጣይም ተጨማሪ እናቶችን በማካተት ይህ ፕሮጀክት ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል። የድርጅቱ ዋና ዓላማም ዜጎች በሀገራቸው ሊጠቀሙ የሚገባቸውን ያህል ተጠቃሚ እንዲሆኑና እንደዜጋ በማሰብ ደግመው ሀገራቸውን እንዲጠቅሙ ማድረግ ነው።

የቂርቆስ ክፍለ ከተማ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ አብዱልሃዲ ረሺድ እንደሚገልፁት እናትና ባንክና እንደዜጋ ማህበራዊ እንደራሴ በጋራ የጀመሩት ፕሮጀክት በክፍለከተማው የሚደገፍና የሚበረታታ ነው። በተለይ ደግሞ ፕሮጀክቱ ትኩረት ያደረገባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እናቶች እንደመሆኑና እናቶች ደግሞ በቤተሰብ ያላቸው ድርሻ ከፍተኛ እንደመሆኑ ይህ ተግባር በክፍለ ከተማው በደንብ ይደገፋል።

በአዲስ አበባ ከተማም ቢሆን እናቶች እያበረከቱት ያለው አስተዋፅኦ በተለይ አዲስ አበባ ከተማ በዓለም አቀፍ ደረጃ ሶስተኛዋ የዲፕሎማሲ መቀመጫ እንደመሆኗ ፅዳቷንና ውበቷን በየቀኑ በመጠበቅ ረገድ እናቶች ከፍተኛውን አስተዋፅኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። ከዚህ አንፃር ለእናቶቹ የተደረገው ድጋፍና ምስጋና የሚያንስ እንጂ የሚበዛ አይደለም። ከዚህ አንፃር ፕሮጀክቱ ይዞ የተነሳው ዓላማም ትልቅና ለተሻለች ሀገር ግንባታ እንደዜጋ መኖርን እሴት ያደረገ ማህበረሰብን መፍጠር ዓላማ ያደረገ ነው። በተለይ ኢትዮጵያ ትልቅ አቅምና ተስፋ ያላት ሀገር እንደመሆኗ ያሉትን አቅሞች በአግባቡና በትብብር መጠቀም ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ደግሞ ሴቶችን ማሳተፍ የግድ ይላል። ክፍከተማውም የፕሮጀክቱ ቤተሰብ ሆኖ ይቀጥላል።

# ዓለም አቀፍ



## የዘር ማጽዳት እንዳይፈጸምባቸው የፈሩ አርመናውያን የካራባክን ግዛት ለቀው ሸሹ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዘርባጃን አወዛጋቢዋን የናጎሮኖ ካራባክን ግዛት መቆጣጠሯን ተከትሎ በሥፍራው የሚኖሩ አርመናውያን የዘር ማጽዳት ይፈጸምብናል በሚል ስጋት እየሸሹ ነው።

ወደ ስድስት ሺህ 500 የሚጠጉ አርመናውያንም ድንበር በመሻገር ወደ አርሜንያ እየገቡ ይገኛሉ። በሥፍራዋ ከ120 ሺህ የሚበልጡ አርመናውያን ይኖሩባታል።

የአርመን መንግሥት በግጭቱ ምክንያት ቤት አልባ የሆኑትን ለመውሰድ ማወጁን ተከትሎ ነው ነዋሪዎቹ እየሸሹ ያሉት። የአርሜኒያ ድንበር መንገዶችም በከፍተኛ ሁኔታ በትራፊክ ተጨናንቀዋል። የአርሜኒያ ጠቅላይ ሚኒስትር በዚህች ግዛት የዘር ማጽዳት ተጀምሯል ሲሉም አስጠንቅቀዋል።

አዘርባጃን በአሁኑ ወቅት ሙሉ በሙሉ በተቆጣጠረቻት ግዛት የሚኖሩ አርመናውያንን ከሌሎች ዜጎቿ ጋር በእኩልነት ማዋሃድ እንደምትፈልግ ተናግራለች።

የካራባክ ግዛት የኔ ናት በሚል የሚወዛገቡት የአርሜኒያ እና የአዘርባጃን ልዑካን በአውሮፓ ኅብረት በሚደገፈው ውይይት ማክሰኞ ብራስልስ ላይ ይቀመጣሉ።

አዘርባጃን የናጎርኖ ካራባክን ግዛት ተቆጣጥሬያለሁ ካለች በኋላም የሚደረግ የመጀመሪያ ንግግር ነው። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃለ አቀባይ ማቲው ሚለር ሁለቱ ወገኖች ዘላቂ የሰላም ስምምነት ላይ እንዲደርሱ አሳስበዋል።

አዘርባጃን በአወዛጋቢዋ ናጎሮኖ ካራባክ ግዛት በሚገኙ የአርመን ኃይሎች ላይ ለ24 ሰዓታት የፈጀ ወታደራዊ ጥቃት ማድረጓን ተከትሎ የሀገሪቱ ሉዓላዊነት እንደተመለሰ ፕሬዚዳንቷ ከሰሞኑ አስታውቀዋል።

የራሳችንን ነጻ ሀገር መስርተናል ሲሉ የነበሩት የአርመን ኃይሎችም ትጥቅ ለመፍታት እና እጅ ለመስጠት ተስማምተዋል።

እስያንና አውሮፓን የምታገናኘው፣ የሩሲያ ዛሮችን ጨምሮ፣ ሮማ፣ ቱርክ፣ የቀድሞዋ ፋርስ ሌሎች ሌሎች መሪዎችም የገዟት ናጎሮኖ ካራባክ 120 ሺህ የሚሆኑ አርመናውያን እንዲሁም የአዘሪ ነገድ አባላት ይኖሩባታል።

ተራራማዋ እና ባህር በር አልባዋ ግዛት ናጎሮኖ ካራባካህ ከአዘርባጃን በስተደቡብ ምዕራብ ትገኛለች። ሁለቱ የቀድሞ የሶቪየት ኅብረት አባል ሀገራት አርሜኒያና አዘርባጃን ግዛቲቷ የኔ ነው በሚልም ጦርነት ተማዘውባታል። በርካቶች አልቀውባታል።

በአውሮፓውያኑ 2020 ለስድስት ሳምንታት የዘለቀው ጦርነት ለብዙ ሺህ ሰዎች ሞት ምክንያት ቢሆንም፤ አዘርባጃን በቱርክ በመደገፍ ግዛቲቷን እንድትቆጣጠር አድርጓታል። ይህም ሁኔታ በሥፍራው የሚኖሩ አርመናውያን እንዲነጠሉ አድርጓቸዋል።

በዓለም አቀፍ ደረጃ ምዕራባውያኑ ናጎሮኖ ካራባክን በአዘርባጃን ግዛትነት ዕውቅና ሰጥተዋታል። ነገር ግን በአርመን መንግሥት የሚደገፉት የካራባክ ኃይሎች ግዛቲቷን ከአዘርባጃን ገንጥለው ነጻ ሀገር መመስረታቸውን በተመለከተ ድጋፍም ሆነ ተቃውሞ አላሰሙም።

## ሩሲያ የተመድ የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት አባልነቷ እንዲመለስ ጥረት ማድረግ ጀመረች

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሩሲያ ከዩክሬን ጋር ወደጦርነት ከገባች በኋላ ከተባበሩት መንግሥት የሰብዓዊ መብት ምክር ቤት አባልነት ተሰርዛለች። አሁን ላይ ግን ሩሲያ አባልነቷን ለማደስ እየሞከረች ነው።

የሩሲያ የአባልነቱ ይመለስ ጥያቄም ለሰብዓዊ መብት ምክር ቤቱ አቋሙን የሚፈትሽ ይሆናል። የሩሲያ ዲፕሎማቶች ሀገራቸው ለሶስት ዓመታት በምክር ቤቱ አባልነት በድጋሚ እንድትመረጥም እየጣሩ ይገኛሉ ተብሏል።

ሩሲያ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አባላትም ድጋፍ እንዲሰጧት እየጠየቀችበት ያለውን የአቋም መግለጫ ቅጂም ቢቢሲ አግኝቷል። ምርጫው በሚቀጥለው ወር ይካሄዳል። በዚህ ሰነድ ላይ ሩሲያ ለሰብዓዊ መብት ጉዳዮች መፍትሄዎችን ለማበጀት ቃል ገብታለች።

ምክር ቤቱ ውስን ያሏቸውን ሀገራት የፖለቲካ ፍላጎት መጠቀሚያ መሣሪያ እንዳይሆን ለማድረግም ሩሲያ ትሰራለች ይላል። ሩሲያ በሰነዱ ላይ ውስን ብላ የጠቀሰቻቸው ሀገራት የምእራቡ ዓለምን ለማመላከት ነው።

በግዛቷም ውስጥ ሆነ በዩክሬን በሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እየተከሰሰች ያለችው ሩሲያ በአንዳንድ ዓለም አቀፍ ተቋማትም ተዓማኒነትን ለማግኘት ተስፋ እያደረገች ትገኛለች።

ሩሲያ እየፈጸመቻቸው ያሉ ጥሰቶችን በተመለከተ የዩክሬን አጣሪ ኮሚሽን በቅርቡ ያወጣው ሪፖርት ለምክር ቤቱ ቀርቧል።

ሰላማዊ ሰዎችን ማሰቃየት፣ መድፈር እና ጥቃቶችን ጨምሮ የጦር ወንጀሎች ስለመቀጠላቸው የሚያሳዩ ማስረጃዎች እንዳሉም የኮሚሽኑ ሊቀመንበር ኤሪክ ሞሴ ተናግረዋል።

የተባበሩት መንግሥታት የሩስያ ልዩ ራፓርተር ማሪያ ካትዛሮቫ ከሁለት ሳምንታት በፊት ባወጡት ሌላ ሪፖርት በሩሲያ ያለው የሰብዓዊ መብት ሁኔታ ከጊዜ ወደጊዜ እያሽቆለቆለ ነው ብለዋል።

ሩሲያ ከዩክሬን ጋር የገባችበትን ጦርነት በሚተቹ ሰዎች ላይ የዘፈቀደ እስራት፣ ማሰቃየት እና እንግልቶች እየተፈጸሙባቸውም እንደሆነም ሪፖርቱ ያስረዳል።

መቀመጫውን በጄኔቫ ያደረገው የተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብት ምክር ቤት 47 አባላት ያሉት ሲሆን እያንዳንዱ አባላትም ለሶስት ዓመታት የሚመረጡ ናቸው።

ከሁለት ሳምንታት በኋላ በሚደረገው ምርጫ ሩሲያ ለማዕከላዊ እና ምስራቃዊ አውሮፓ ሀገራት ተወካይነት በተዘጋጀው የምክር ቤቱ ሁለት መቀመጫም ከአልባኒያ እና ከቡልጋሪያ ጋር ትወዳደራለች።

# ስፖርት

## ቡናማዎቹን ከነብሮቹ ያገናኘው ተጠባቂ የፍፃሜ ፍልሚያ

ቦጋለ አበበ

ከአንድ ሳምንት በላይ በአበበ ቢቂላ ስቴድየም ሲካሄድ የቆየው 17ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ዛሬ ይጠናቀቃል፡፡ የፍፃሜ ተፋላሚዎቹ ባለፈው ሰኞ በተካሄዱ የግማሽ ፍፃሜ ጨዋታዎች ሲለዩ ኢትዮጵያ ቡናና ሃዲያ ሆሳዕና ዋንጫውን ለማንሳት ዛሬ የሚፋለሙ ይሆናል፡፡

ሁለቱ ክለቦች በግማሽ ፍፃሜው ፍልሚያ ተጋጣሚዎቻቸውን በመለያ ምት አሸንፈው ለፍፃሜ የቀረቡ ሲሆን ዛሬ የሚያደርጉት ፉክክርም ተጠባቂ ነው፡፡ የውድድሩ ተጋባዥ ክለብ ሃድያ ሆሳዕና በግማሽ ፍፃሜው ኢትዮጵያ መድንን በገጠመበት ጨዋታ ግብ ሳይቆጠር ወደ መለያ ምት አምርቶ ሃድያ ሆሳዕና 5 ለ 4 በማሸነፍ የፍፃሜ ተፋላሚ መሆኑን አረጋግጧል።

በተመሳሳይ ሁለቱን የአዲስ አበባ ተቀናቃኝ ክለቦች ያገናኘው የቅዱስ ጊዮርጊስና ኢትዮጵያ ቡና የግማሽ ፍፃሜ ጨዋታ በመጀመሪያው 45 በተቆጠሩ ግቦች ጥሩ ፉክክር ታይቶበታል። ፈረሰኞቹ አዳማ ከተማን አሸንፈው ወደ ግማሽ ፍፃሜ ሲያልፉ ሁለት ግቦችን ከመረብ በማሳረፍ የጨዋታው ኮከብ የነበረው ሀሮን አንተር በ13ኛው ደቂቃ ባስቆጠረው ግብ ፈረሰኞቹን መሪ ማድረግ ችሎ ነበር። የፈረሰኞቹ መሪነት የዘለቀው ግን ለአስራ ሶስት ደቂቃዎች ያህል ነበር፣ 26ኛው ደቂቃ ላይ ወልደአማኑኤል ጌቱ ለኢትዮጵያ ቡና የአቻነቷን ግብ አስቆጥሮ የመጀመሪያው አጋማሽ ተጠናቋል። በሁለተኛው አጋማሽም ግብ ሳይቆጠር ወደ መለያ ምት አምርቷል።

በዚህም ኢትዮጵያ ቡና በመለያ ምቱ 5 ለ 4 በማሸነፍ የከተማው ዋንጫ የፍፃሜ ተፋላሚነቱን ሲያረጋግጥ በወጣቶችና በተስፋው ቡድን በውድድሩ የተካፈለው ቅዱስ ጊዮርጊስ ለደረጃ ፍልሚያው ኢትዮጵያ መድህንን የሚገጥም ይሆናል።

አምና ወደ ፕሪሚየርሊግ ባደገበት ዓመት አስደናቂ ጊዜን ማሳለፍ የቻለው ኢትዮጵያ መድህን በአሠልጣኝ ገብረመድህን ሃይሌ እየተመራ በዚሁ የከተማ ዋንጫ የመጀመሪያ ጨዋታ ቅዱስ ጊዮርጊስን 3 ለ 1 ማሸነፉ ይታወሳል። ሁለቱ ክለቦች ዳግም በደረጃው ፍልሚያ የሚገናኙ ሲሆን ኢትዮጵያ ቡናም በፍፃሜው የሚገጥመውን ሃዲያ ሆሳዕና ከቀናት በፊት በምድቡ የመጨረሻ ጨዋታ 1 ለምንም ማሸነፉ ይታወቃል።

ሰባት ክለቦች በሁለት ምድብ ተደልድለው ሲፋለሙበት በሰነበተው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ ዛሬ በተካሄደው የግማሽ ፍጻሜ ጨዋታዎች ሃድያ ሆሳዕና ከኢትዮጵያ መድን ጋር ባደረጉት ጨዋታ 0 ለ 0 ተለያይተው በተሰጠ የመለያ ፍጹም ቅጣት ምት ሃድያ ሆሳዕና 5 ለ 3 በማሸነፍ ለዋንጫ ማለፉን አረጋግጧል።

ኢትዮጵያ ቡና በመጀመሪያው የምድብ ጨዋታ የውድድሩን ተጋባዥ ሻሸመኔ ከተማን ሁለት ለአንድ ያሸነፈ ሲሆን፣ በሁለተኛው የምድብ ጨዋታ ደግሞ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ጋር ሁለት ለሁለት ተለያይቷል፣ የመጨረሻውን የምድብ ጨዋታ ያደረገው ዛሬ በፍፃሜ የሚገጥመውን ሃዲያ ሆሳዕና የነበረ ሲሆን አንድ ለዜሮ በማሸነፍ ከምድቡ ቀዳሚ ሆኖ የግማሽ ፍፃሜውን ፍልሚያ ተቀላቅላል፡፡ ጠንካራ በነበረው የግማሽ ፍፃሜ ፍልሚያ የከተማ ተቀናቃኙ ቅዱስ ጊዮርጊስን በመለያ ምት አሸንፎም ለፍፃሜ መብቃቱ በዛሬው የዋንጫ ጨዋታ ለድል የተሻለ ግምት እንዲሰጠው አድርጓል፡፡ ቡናማዎች በውድድሩ እስከ ፍፃሜ ሲጓዙ በአጠቃላይ በአራቱ ጨዋታዎች ሰባት ግቦች ሲያስቆጥሩ አራት ተቆጥሮባቸዋል፡፡

የውድድሩ ተጋባዥ ሆነው አስደናቂ የዋንጫ ጉዞ ያደረጉት ነብሮቹ በበኩላቸው በመጀመሪያው የምድብ ጨዋታ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክን ሁለት ለአንድ፣



ኢትዮጵያ ቡና በሜዳውና በደጋፊው ፊት የከተማውን ዋንጫ ለማንሳት ትልቅ ግምት ተሰጥቶታል

በሁለተኛው ጨዋታ ደግሞ ሻሸመኔ ከተማን አንድ ለዜሮ አሸንፈው በሶስተኛው ጨዋታ ዛሬ በሚገጥሙት ኢትዮጵያ ቡና የአንድ ለዜሮ ሽንፈት አስተናግደዋል፡፡ በዚህም ከምድባቸው ኢትዮጵያ ቡናን ተከትለው የግማሽ ፍፃሜውን ፍልሚያ ተቀላቅለዋል፡፡ በግማሽ ፍፃሜው ፍልሚያም በፕሪሚየርሊጉ ጠንካራ የሆነውን ኢትዮጵያ መድህንን በመለያ ምት አሸንፈው ለዋንጫ መቅረባቸው ዛሬ ለቡናማዎቹ ቀላል እንደማይሆኑ ተገምቷል፡፡ ነብሮቹ በአራቱ ጨዋታዎች ሶስት ግብ ብቻ አስቆጥረው ለፍፃሜ ሲደርሱ ሁለት ግብ አስተናግደዋል፡፡

17ኛው የአዲስ አበባ ከተማ ዋንጫ በሁለት ምድብ የተካሄደ ሲሆን በምድብ ሀ ኢትዮጵያ ቡና፣ ኢትዮጵያ ንግድ ባንክ፣ ሃድያ ሆሳዕና እና ሻሸመኔ ከተማ ተደልድለዋል። በምድብ ለ ያለፉት ሁለት ተከታታይ የፕሪሚየርሊግ ዋንጫ አሸናፊው ቅዱስ ጊዮርጊስ፣ ተጋባዡ አዳማ ከተማ እና ኢትዮጵያ መድን መደልደላቸው ይታወሳል።


### የሀገር ውስጥ ጨረታ ማስታወቂያ
### የጨረታ ቁጥር 01/2016

ድርጅታችን ሆራይዘን አዲስ ጎማ ኃ/የተ.የግ.ማ. የተለያዩ ሳይዝ ያላቸውን የውስጥ ላስቲክ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል።

1. በመሆኑም በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ የዘመኑን ግብር የከፈሉበትን ማስረጃ (Tax clearance certificate) የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ያላቸው መሆን አለባቸው፣
2. የጨረታ ማስከበሪያ (Bid Bond) 200,000 (ሁለት መቶ ሺህ ብር) በሲፒኦ ወይም በባንክ ጋራንቲ ማስያዝ የሚችሉ፣
3. ዝርዝር የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 ቀናት ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ጠዋት ከ2፡00-6፡00 ሰዓት ከሰአት ከ7፡00 እስከ 10፡00 ሰዓት ከስር በተገለጸው አድራሻ ከድርጅቱ ፋይናንስ ክፍል የማይመለስ ብር 100.00 (አንድ መቶ ብር) በመክፈል ማግኘት ይቻላል።
4. ተጫራቾቹ የጨረታ ሰነዱን በታሸገ ፖስታ ጨረታው ከሚዘጋበት ሰአት በፊት ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል።
5. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት መስከረም 30 ቀን ጠዋት 4፡00 ሰዓት ተዘግቶ በዚያው ቀን በ4፡30 ሰዓት የሰራተኞች ክበብ ይከፈታል።
6. ድርጅቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**አድራሻ፡- ሳሪስ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ንፋስ ስልክ ቅርንጫፍ ወረድ ብሎ**

**ስልክ፡-0114421555**

**ሞባይል፡- 0929914933**

**ኢሜይል፡- shimelis.Hailmeskel@horizon-atc.com**

**አዲስ አበባ**

**ሆራይዘን አዲስ ጎማ ኃ.የተ.የግ.ማ.**



### የጨረታ ማስታወቂያ
### የጨረታ ቁጥር አዩ/ግ/አስ 002/2016

አምቦ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅና ሪፈራል ሆስፒታል በ2016 በጀት ዓመት ተኝተው ለሚታከሙት ህሙማን ለአንድ ዓመት በራሳቸው ሙሉ ወጪውን ሸፍነው በሆስፒታሉ ግቢ ወይም አቅራቢያ ምግብ አዘጋጅተው ከሚያቀርቡት በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል።

**በዚሁም መሠረት በጨረታው ለመካፈል የሚፈልጉ ተጫራቾች፡-**

1. በመስኩ ህጋዊ የታደሰ ንግድ ስራ ፈቃድ እና የTIN የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ መሆን አለባቸው።
2. በተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገቡበት ሰርተፊኬት በአንድ ላይ አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
3. የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 100.00 /አንድ መቶ ብር/ እየከፈሉ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በሥራ ሰዓት ከዩኒቨርሲቲው ሪፈራል ሆስፒታል ግዥ የሥራ ክፍል መውሰድ ይችላሉ።
4. ማንኛውም ተጫራች የጨረታው ውጤት እንደታወቀ ለተሸናፊዎች የሚመለስ የጨረታ ማስከበሪያ ብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) በሲፒኦ አሰርተው ወይም በጥሬ ገንዘብ ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዘው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. ተጫራቹ የምግቡን የማብሰያ ዕቃዎችንም ሆነ የሚያዘጋጅበትን ቦታ በራሱ ያዘጋጃል።
6. ተጫራቾች ሪፈራል ሆስፒታሉ ባዘጋጀው የጨረታ ሰነድ ላይ የተዘረዘሩትን ምግብ ጠቅላላ ሳይቀር የሚጫረቱበትን ጠቅላላ ዋጋ ስርዝ ድልዝ ሳይኖረው በጥንቃቄ መሙላት ይኖርባቸዋል።
7. ተጫራቾች ዋጋ የሚሞሉበትን የጨረታ ሰነድ ኦሪጅናል እና ኮፒ በሰም በታሸገ ፖስታ /ኤንቨሎፕ/ አድርገው ማቅረብ አለባቸው።
8. ማንኛውም ተጫራች በሌሎች ዋጋ ላይ ተንተርሶ ዋጋ መስጠት አይችልም።
9. ጨረታው ጥቅምት 06/2016 ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ተዘግቶ በ3፡45 ሰዓት ላይ ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በሪፈራል ሆስፒታሉ የስብሰባ አደራሽ ይከፈታል።
10. የተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው አለመገኘት ጨረታውን ከመክፈት አያስቀርም ።
11. ተጫራቾች ተጨማሪ ማብራሪያ ቢያስፈልጋቸው በስልክ ቁጥር 0112609979 ደውለው ማብራሪያ መጠየቅ ይችላሉ።
12. ሪፈራል ሆስፒታሉ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**አምቦ ዩኒቨርሲቲ ሪፈራል ሆስፒታል**